
# ሐመር

ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ

ሐመር ፱ኛ ዓመት ቁጥር 4 መስከረም-ጥቅምት 1994 ዓ.ም



# ከአንባብያን ለአንባብያን

## ሁሉም ቢለምደው

የኮንስትራክሽን ሠራተኛ ነኝ። በመሆኑም የመስክ ሥራ አዘውትራለሁ። በዚህ የመስክ ዝውውሬ በተለይ በሰሜን ወሎ ቆቦ፣አላማጣ፣ኮረም፣ማይጨው፣ በሐረር ጅጅጋና ፊቅ በሚባሉ ቦታዎች ያገኘኋቸው ኦርቶዶክሳውያን የሥራ ባልደረቦቼ ሁሌ ከሥራ መልስ ማታ ማታ በካምፓቸው እየተሰባሰቡ ቃለ እግዚአብሔር ይማማራሉ። ይህንን የሚያደርጉትም በአካባቢያቸው ያሉ ካህናት በመካከላቸው እንዲገኙ በመጋበዝ ነው። ከዚህም ባሻገር በሥራ በሄዱበት ሁሉ የሚያገኟቸውን አብያተ ክርስቲያናት በገንዘባቸው፣ በዕውቀታቸው ወዘተ ይረዳሉ። በእውነቱ ሥራቸው በግሌ መንፈሳዊ ቅንአት እንዲያድርብኝ አድርጎኛል። ሌላውም መንፈሳዊ ቅንአት አድሮበት ይህን መልካም ሥራ ቢለምደው መልካም ነው እላለሁ።

*አንዳርጋቸው ባዩ*
*ሱር ኮንስትራክሽን መተማ*

## ደገኛ ተግባር

በወናጐ ከተማ የሚገኙ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና ሌሎች በጐ አድራጊ ምእመናን ከከተማው 5 ኪሎ ሜትር ርቀት የሚገኘውን የሻሬ መድኃኔዓለም ቤተክርስቲያንን የዲያቆናቱንና የካህናቱን አበል እንዲሁም ልዩ ልዩ ወጪዎችን፣ በመሸፈን በየማምንቱ እሑድ እንዲቀደስ፣ ምእመናንም እየተሰበሰቡ ቃለ እግዚአብሔር እንዲማሩ እያደረጉ ነው። ይህ ጥሩ ሥራ በሌሎች ወንድሞችና እኅቶችም እንዲለመድ ቢሆን መልካም ነው እያልኩ ይህንን መልካም ሥራ እየሠሩ ያሉ ሁሉ እግዚአብሔር ዋጋውን እንዲሰጣቸው ጸሎቴ ነው።

*ዲ.ሀብታሙ አበበ*
*ወናጐ ቅ/ማርያም*
*ቤተክርስቲያን*

## እንደሥርዓቱ...

እግዚአብሔር ፈቅዶ ያሳለፍነውን ጾመ ፍልሰታ መሥሪያ ቤቴ የዓመት ፈቃድ ሰጥቶኝ አስቀድሼ ነበር። በእውነቱ ምእመናን ከሕፃን እስከ ሽማግሌ በቤተክርስቲያን ተሰብስበው ጸሎተ ቅዳሴውንና ሌላውን መርሐ ግብር ሲከታተሉ ሳይ በእጅጉ እደሰት ነበር። ነገር ግን አሐዱ ተብሎ ጸሎተ ቅዳሴው ከተጀመረ በኋላ የአንዳንድ ምእመናን ተግባር ቅር ያሰኘኛል። ተሰጥዎውን እንደታዘዘው በሚገባ የሚቀበሉ ምእመናን የመኖራቸውን ያህል ከሥርዓት ውጪ የሆኑ ምናልባት የግላቸውን ሥርዓት ደንግገው በጸሎተ ቅዳሴው የሚሳተፉ አሉ። ዲያቆኑ «ስግዱ» ሲል ቁጭ የሚሉ ወይም እንደ ቆሙ የሚቀሩ፣ይበል ሕዝብ በሚል በጸሎተ ቅዳሴው የሚሳተፉበት የዜማ ድርሻ እያለላቸው ከዲያቆኑ ወይም ከካህኑ ጋር የሚያዜሙ፣በማይሰገድበት ጊዜ በሚያስገርም ሁኔታ እየሰገዱ የሌላውን ትኩረት የሚስቡ ምእመናን አይቼአለሁ። ይህ ጉራማይሌ ሁኔታ ቤተክርስቲያንን ሥርዓት የሌላት ያስመስላታልና እንደ ሥርዓቱ እንሁን።

*ሉሊት መኮንን*
*ከአዲስ አበባ*

## ከሽሮ ሜዳ እስኪዳነ ምሕረት

/ሶረኔ/

ከሁሉ በፊት ባለፈው በወጣችው ሐመር መንገደኛው ኃ/ገብርኤል ዘሐና የለኩባችሁን ቀጠሮ ልብ ብላችሁ ጉልበታችሁን በማቀፍ ተቀምጣችሁ የምትጠብቁ ሁሉ ይቅር በሉኝ። ለእናንተ የሚሆነውን ለመውሰድ እኛ ሰንበት ት/ቤት ሲመጡ ተገናኘንና «በሞቴ» ብላቸው «እሺ ለአሁኑ ለቅቄልሃለሁ» ስላሉኝ ነው በእሳቸው ፈንታ የመጣሁት። እና ለዛሬው ከእኔ ጋር ከሽሮ ሜዳ እስከ ኪዳነምሕረት እንጓዝ። ቀኑ ረቡዕ የነሐሴ ኪዳነ ምሕረት ነው። ስለ ነሐሴ ኪዳነ ምሕረት ምንነት መቼም እናንተ የእመብርሃን ወዳጆች አስታዋሽ አትሹም። በተረዳ ነገር ታውቁታላችሁና። ምናልባት የማታውቁት ብትኖሩ ሽሮ ሜዳንና ኪዳነ ምሕረትን ነው። ሽሮ ሜዳ በአዲስ አበባ በስተሰሜን ምዕራብ በኩል የሚገኝ ሠፈር ሲሆን፣ ጥንታዊቷ የሐመረ ኖህ ኪዳነ ምሕረት ገዳም ቤተክርስቲያን ደግሞ ከዚህ ሠፈር በስተሰሜን በመኪና ከ5–10 ደቂቃ በእግር ከ25–30 ደቂቃ ተጉዞ የምትገኝ በረከተ ብዙ ገዳም ናት። ጾመ ማርያም ስታልፍ አጸዷ ሁሉ ጭር የሚለቱን ያህል በጾመ ፍልሰታ ሰሞን እያንዳንዱ የአዲስ አበባ ቤቶች ወኪል የላኩ እስኪመስላችሁ ድረስ የአካባቢው ጓዳ ጐድጓዳ ሁሉ ሰው ብቻ ይሆናል። ዕድል ገጥሞኝ እስከአሁን እዛ ሱባኤ ይዤ ባላውቅም በጾም ሰሞን የሚከራይ ቤት እንደከበረ ዕቃ ውድ ነው አሉ። ክፍሉ ሳሉንም ይሁን ዕቃ ቤት አንዲት ወርድና ቁመት የሌላት ፍራሽ ለ15 ቀናት ለማንጠፍ 200 ብር ቢመዙ አይገኝም አሉ።

በሰሙኑ ጾሙ ያን ያህል የተጣበበው ቦታ የበለጠ በዕለተ ኪዳነ ምሕረት በመላ አዲስ አበባ ሰው የሌለ እስኪመስል ሁሉም ግልብጥ ብሎ ወደ ንግሡ በዓል ይተማል። በዚህ ጊዜ እንኳን ኪዳነ ምሕረትና አካባቢዋ መንገዱ ከመጥበቡ የተነሣ ገና ከሽሮ ሜዳ ጀምሮ እንደልብ መራመድ አይቻልም። ታዲያ ሁልጊዜ በየዓመቱ እንደማደርገው ዘንድሮም ባልዝግስም ጠዋት ላይ ተነሥቼ ከሰፈሬ ሽሮ ሜዳ ስደርስ ያው የምእመናን እንደጉድ መትመም ነበር የጠበቀኝ። የእግር ጉዞዬን ጀመርኩ። እንኳን ልሂድ ብሎ እግሩን ያነሣ ሰው፣ ላለመሄድ ወስኖ የቆመ ሰው እንኳ ቢሆን ሳይወድ በግድ በሕዝቡ ጉርፍነት ታፍሶ እዛው ኪዳነ ምሕረት ይደላል። እኔም በምእመናን ትጋት እየተደሰትኩ ከሚስቀው ጋር እየሳኩ፣ከሚያኮርፈው ጋር እያኮረፍኩ፣ ከሚዘምረው ጋር እየዘመርኩ ወደ እንጦጦዋ ኪዳነ ምሕረት ጉዞዬን ጀመርኩ። ገና ብዙም ሳልራመድ አምናና ካች አምና በመጠኑ አስተውለው የነበረው ነገር ዘንድሮ አብጦና ገዝፎ ቆየኝ። በምእመናን ላይ ዐይኑን አፍጥጦ፣ ጥርሱን አግጥጦ፣ደረቱን ገልብጦ። ማን አባቱ ነው አትሉኝም'' ልመና።

መቼም ቅድስት ቤተክርስቲያናችን የራበው የሚበላባት፣የታረዘው የሚለብስባት፣ የታመመው ልጆቿ በሚለግሱት ችሮታ የሚፈወስባት ናት። በመሆኑም በቤተክርስቲያን ዙሪያ ነዳያን መሰብሰባቸው ጥንታዊ ነው። አንድም ቤተክርስቲያን እመ ኩሉነቷን የሚገልጥ ነው። ትዝብቴም ከዚህ በሚመደቡትና ዐይነ ፈራጣ፣እጅ እግር ቆራጣ ወዘተ ከሆኑት ወገኖቼ ላይ ያነጣጠረ አይደለም። በሚከተሉት ላይ እንጂ።

ከላይ ከተጠቀሰው የልመና ዓይነት ውጭ ያሉትን ልመናዎች መደቦቹን ሰፋ ሰፋ አድርገን በሁለት ልንከፍላቸው እንችላለን። አንደኛውን መደብ «የአክብሩኝ የአበልጥጉኝ ልመና» የሁለተኛውን መደብ ደግሞ «የቤተክርስቲያንን ሥሩ ልመና»። በየተራ እንያቸው።

መቼም ይህ ዘመን ጌታችን በአንደበቱ «ቤቴ የጸሎት ቤት ይሆናል ተብሎ ተጽፎአል፤ እናንተ ግን የወንበዴዎች ዋሻ አደረጋችሁት» /ሉቃ.19፥45/ ያለው እንዳልተባለ ተደርጐ የተቆጠረበት ዘመን ነው። በዚህ ጉዞዬ አቅመ ደካማ አረጋውያንና ሕፃናት ምንም እንኳን በረከት የሚያገኙበት ቢሆንም ካደከማቸው የሰው ግፊያና ጉሸማ የበለጠ የክብረቱና የቃሪያው የግዙኝ ጥያቄና ጆሮ ቀርዳጅ የመማለጃ ጩኸት እንዳጥፋፋቸው እየተመለከትኩ በእጅጉ አዝን ነበር። «አልሰማንም አላየንም እንዳትሉ»፣ «75 ብር የነበረው እንትን አምስት ብር» «ኪዳንዬን ምክንያት በማድረግ ታላቅ ቅናሽ» ወዘተ ወዘተ ወዘተ. ደግሞ የሚገርመው እነዚህ ተንቀሳቃሽ ነጋዴዎች ያንን የሚወተውቱት መንገዱ መሐል በመቆም ምእመናንን በሚያንሰፈስፋቸው የመንገድ ጥበት ቁስል እንጨት እየሰደዱ መሆኑ ነው። ግሩም። በዚህ ሁኔታ ከሽሮ ሜዳ ጫፍ እስከ ኪዳነ ምሕረት ቅጽር ጥግ ድረስ በሱቅ በደረቴና ሁኔታውን ዐይተው መሐል መንገድ ላይ «ሱቅ በከፈቱ» ነጋዴዎች ተሞልቷል። የሚደንቀው ጥቂት ወጣቶች ማስቲካና ሙዚቃ ሞቅ አድርገው ከከፈቱ ጊዜያዊ «ኬክ ቤቶች» ሳምቡሳ ሲገዙ ከማየቴ በስተቀር ማንም ምእመን ቆሞ ጫማም ሆነ አልበም ሲገዛ ያየሁት የለም። መጀመሪያ ዕቃ የሚገዛው ሰው ቆሞ መገበያየት ሲችልማይደል? ሁሉም በሌላው ጉርፍነት እየታጠበ ወደ ኪዳነ ምሕረት።

ሁለተኛው የልመና ዓይነት ደግሞ በእጅጉ መንፈሳዊ አድርገን ስንጠራው «የቤተክርስቲያንን ሥሩ ልመና» ልንለው እንችላለን። በስምዐ ጽድቅ መንፈሳዊት ጋዜጣ ሰባተኛ ዓመት ቁጥር አራት እትም ቤተክርስቲያን በወቅቱ የጠቅላይ ቤተክህነት ሥራ አስኪያጅ በኩል « ቤተክርስቲያንን ለማሠራት ስለሚለምኑ ሰዎች ቅዱስ ሲኖዶስ መመሪያ አውጥቷል። ከጠቅላይ ቤተክህነት ፈቃድ ሳይሰጥ በሌላ ሀ/ስብከት ሄዶ ርዳታ መሰብሰብ አይቻልም» ማለቷን አበክሬ ላስታውስ።

ዘወትር የማየው ቢሆንም የዛን ዕለት በተረዳ ነገር ያወኩት ይህ ዓይነቱ ልመና በሁለት መንገድ እንደሚቀርብ ነው። አሥሩት የተባለውን ቤተክርስቲያን ታሪክ የያዘ በራሪ ወረቀት ወይም ማኅተም ያረፈበት ኮብ ወይም አራት ማዕዘን ካርድ ገዝታችሁ ቤተክርስቲያኑን ሥሩት የሚል ልመናና ቃጭል እየተቃጨለ በመስቀል እየተገዘተ፣በተሞላ ተንቀሳቃሽ ድምጽ ማጉያ እየተለፈፈ የሚቀርብ ልመና። ሌላው ቅዱስ መልአክ እኩል የተራዳኢነት አገልግሎት እንደሚሰጥ ሁሉ የእኔ ያሉትን መልአክ ብቻ ስሙን እያስበለጡና እያቆላመጡ በመጥራት፣ በሰማዕትነት ያረፈው ለእነሱ ብቻ ይመስል አንዱን ሰማዕት እንደግል ሀብት በመቁጠር ስሙን እያበዙ እጃችሁን ዘርጉ ሲባል ካለፉ አባቶቻችን የሕይወት ታሪክ አላነበብንም ወይም አልሰማንም። ነገር ግን ዛሬ የሁሉም አጥቢያ ካህን ቀዬውን ለቆ እየመጣ ምእመናንን ሲያታክት በዓይናችን እናያለን፣በጆሮአችን እንሰማለን።

ከሁሉም የበለጠ ይህ ቤተክርስቲያን ድምጿን ከፍ አድርጋ የምትከለክለው ጉዳይ ከገጠር ከመጠና አልፎ አልፎ ከከተሜዎቹ የዕድሜ ባለጸጐች፣ ነገ የቤተክርስቲያንን ችግር በሚገባ ይቀርፋሉ ወደሚባሉ ወጣቶች ሲዛመት ሲታይ በእጅጉ ያስደነግጣል። ከላይ በጠቀስኩት ጉዞዬ ከ20 ቢበልጡ እንጂ የማያንሱ የወጣት ቡድኖች የሰንበት ት/ቤታቸውን ሙሉ አልባሳት፣ጸናጽል፣ከበሮ በመጠቀም በዜማ የእጃችሁን ዘርጉ ጥያቄ ሲያስተጋቡ በትክክል ተመልክቼአለሁ። የትናንት ማንነቷን ዞሮ የሚያይበት አጥቶ «ቤተክርስቲያን የልማት ፀር ናት» ለሚለው ሁሉ ትክክለኛ ምላሽ ይሰጣል የሚባለው ወጣት እሱም በልመና ሥራ ተሰማርቶ ሲታይ በእጅጉ ያሳዝናል።

ትዝብቴን ለማጠቃለል ሙሉ በሙሉ ዝም ብላለች ባይባልም ቤተክርስቲያን /አስተዳዳሯ/ ማንነቷን፣ክብሯን፣ዝናዋን ዝቅ የሚያደርገው ይህ ተግባር እንዲጠፋ የበኩሏን ጥረት ማድረግ አለባት እላለሁ። ምእመናንም የሚያደርጉትን ችሮታ መሥራት ለማይችል ብቻ በማድረግ የልመና ባህል ከቤተክርስቲያን አካባቢ እንዲጠፋ የበኩላቸውን ጥረት እንዲያደርጉ አደራ እላለሁ። እግዚአብሔር ቤተክርስቲያንን ይጠብቅልን።

ወደ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ልጆች ስንመለስ ደግሞ ምእመናን የክርስትና ሕይወታችን አዲስ ለውጥ እንዲያገኝ ማድረግ ይኖርብናል። ባለፈው ዓመት ካከናወንናቸው ተግባራት መካከል መልካም የሆኑትን አጠናክረን ለፍሬ ማብቃት አለብን። ስለ ንስሐ፣ስለ ቅዱስ ቁርባን በመማር ዓመቱን ያሳለፍን በአዲሱ ዓመት የተማርነውን በሥራ በመተርጐም ንስሐ የምንገባበት፣ ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን የምንቀበልበት መሆን ይገባዋል።

/የማኅበሩ መልእክት /

---

በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በድምቀት ከሚከበሩት በዓላት አንዱ የመስቀል በዓል ነው። በቤተ ክርስቲያን የበዓላት ቀኖና መሠረት የመስቀሉ በዓል ሁለት ጊዜ ይከበራል። የመጀመሪያው በንግሥት ዕሌኒ /255-335ዓ.ም/ ለ200 ዓመታት በአይሁድ ከተቀበረበት ይወጣ ዘንድ ቁፋሮ የተጀመረበት መስከረም 17 ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ተቆፍሮ የወጣበትና በፋርሶች ከተማረከ በኋላ በሮሙ ንጉሥ በሕርቃል በ628 ዓ.ም. ወደ ኢየሩሳሌም የተመለሰበት መጋቢት 10 ቀን ናቸው።

/ትምህርተ ሃይማኖት/

---

ከዚህ በኋላ ለሦስት ዓመት አፄ ገብረ መስቀል ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን ሲያሠሩ፣ ጻድቁ አባታችን አቡነ አረጋዊ ሕገ ቤተ ክርስቲያን እና ሥርዓተ ምን ኩስና ሲያስተምሩ፣ ቅዱስ ያሬድ ዝማሬ መዋሥዕትን በዜማ እየደረሰ ሲያስተምር ቆይተዋል።

/እናስተዋውቃችሁ/

---

በመጻሐፍ ቤት የሚገኙ ደቀ መዛሙርት በዚህ መልክ ተምረው ምሥጢር አደላድለው አብነት ሁነው ወጥተው የሚያስተምሩ ነበሩ። አንዳንድ ተማሪዎች ከአንድ መምህር ሲቀጽሉ ኖረው ወደ ሌላው ተዛውረው ያስፋፉሉ። ከአንዱ ቤተ ጉባኤ በአንድ ሞያ ቢመረቁ ም በዚያ ዘርፍ ብቻ ሳይገቱ፣የሚያስተምሩበት ጉባኤ ስፋት ሳይወስናቸው የጠፋውን በመፈለግ የደከመውን በማጽናት ከዕውቀት ወደ ዕውቀት ይራመዱ ስለነበር በርካታ አራት ዓይናዎች ነበሩን።

/ቤተክርስቲያንህን ዕወቅ/

---


ዋና አዘጋጅ - ዲ. ግርማ ወ/ሩፋኤል
ምዋና አዘጋጅ- ዲ. መርሻ አለኸኝ

ስልክ 556328
ፖስታ 80078
አዲስ አበባ

E -mail-EOC-M-KIDUSAN@ telecom.net.et.


«ማኅበረ ቅዱሳን»
እግዚአብሔር ያከበራቸው
የነቢያት፣የሐዋርያት፣የጻድቃን የሰማዕታት
በአጠቃላይ የቅዱሳን ገድል፣ትሩፋትና
አማላጅነት የሚዘከርበት በመሆኑ ይህን
ስያሜውን አግኝቷል።


ሐመር
9ኛ ዓመት ቁጥር 4
መስከረም/ጥቅምት 1994 ዓ.ም


# ይዘት


**የማኅበሩ መልእክት**

- አዲስ ዓመት ለአዲስ ሥራ........................2

**ደብዳቤዎች** ........................................ 4

**ትምህርተ ሃይማኖት**

- ጸሎተ ሃይማኖት ........................ 6
- መስቀል ........................................9

**ጥያቄዎቻችሁ**

- አለ ወይስ የለም ?........................12

**ኪነጥበብ**

- ዝንጉው ምሥጢረኛ........................ 13

**እናስተዋውቃችሁ**

- የርዕሰ አድባራት ዙር አባ አረጋዊ.............16
- ንጉሠ ነገሥት ቅዱስ ይምርሐነ ክርስቶስ.......19

**ዓምደ ወራዙት**

- የዘመኑ ወጣት እና የአብነት ..................21

**ክርስትና በማኅበራዊ ኑሮ**

- ክርስቲያናዊ የሕይወት ለውጥ ..................24

**ቤተክርስቲያንህን ዕወቅ**

- የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ሥርዓተ ትምህርት ........................ 27
- መጠይቅ ........................................31



በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ በማኅበረ ቅዱሳን የኀትመት ዝግጅት ማስተባበሪያ ክፍል የሚዘጋጅ ትምህርታዊ መጽሔት።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓትና ትውፊት ጠብቆ የሚወጣ።

ሽፋን ፎቶ መታፊሪያ /ቱሪዝም ኮሚሽን/

## የማኅበሩ መልእክት

# አዲስ ዓመት ለአዲስ ሥራ

### እንኳን ከዘመነ ማቴዎስ ወደ ዘመነ ማርቆስ በሰላም አሸጋገራችሁ::

ዓለም ከተፈጠረ ዘመን ከተቆጠረ ብዙ ሺ ዓመታት አልፈዋል:: ዓመት አልፎ ዓመት ሲተካ በየዘመናቱ ትውልድ እያለፈ ትውልድ ሲመጣ ቆይቷል:: እግዚአብሔር አምላክ እሥራኤላውያንን ከግብፅ ባርነት የወጡበትን ቀንና ወር እንዲያከብሩ በማዘዝ ዓውደ ዓመታቸው በመስከረም አንድ ቀን እንዲሆን አድርጐአል:: የዘመን መለወጫ ከግብፅ ከባርነትና ከስቃይ ኑሮ የወጡበትና አዲስ ሕይወት የጀመሩበት በመሆኑ በደስታ ያከብሯታል:: የቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ሊቃውንትም ምሳሌና ምሥጢርን በማስማማት የብሉይ ኪዳን መጨረሻ የሐዲስ ኪዳን መግቢያ የሆነውን መጥምቀ መለኰት ቅዱስ ዮሐንስን በዘመን መለወጫ በመስከረም ወር በማድረግ ከጨለማ ወደ ብርሃን፣ከብሉይ ወደ ሐዲስ፣ከዓመተ ኩነኔ ወደ ዓመተ ምሕረት የተሸጋገሩበትን እንድናስብ አድርገውናል:: በመሆኑም በየዓመቱ አዲስ ዓመት ስንቀበል በተለዩ ተስፋና ደስታ ነው::

በምድር ከተፈጠሩ ፍጥረታት መካከል ልዩ ኃላፊነትና ክብር ያለው የሰው ልጅ ዓመት አልፎ ዓመት ሲተካ ባለፈው ያልተሠራውን በማሰብ ለወደፊቱ ለመሥራት ዝግጁ መሆን ይጠበቅበታል:: በየዓመቱ ምንም መልካም ሥራ ካልተሠራ ዘመናትን መቁጠር ብቻ ትርጉም የለውም:: እግዚአብሔር ለሰው ዘመንና ጊዜን የሚሰጠው ለዘለዓለም የሚጠቅሙትን መልካም ሥራዎች ይሠራበት ዘንድ ነው:: እነዚህ መልካም ሥራዎች በምድርም ሆነ በሰማይ ዋጋን ያስጡታል:: መልካም የሠራ ሥጋው ባረፈበት በምድር ከመቃብር በላይ ስሙን ሲያስመሰግን ይኖራል:: በነፍሱ ደግሞ በአምላኩ ፊት ዋጋውን ያገኛል:: በአንጻሩ በምድር በተሰጠው ዘመን መልካም ሥራን ከመሥራት ይልቅ ክፉ ሥራን የመረጠ፣ከእውነት ይልቅ ውሸትን የወደደ፣በፍቅር ፋንታ ጥላቻን የያዘ፣በትጋት ቦታ ስንፍና የያዘው ወዘተ በምድርም በሰማይም አሳፋሪ ተግባራትን ሲያከናውን የቆየ በመሆኑ ሲወቀስ ሲቀጣ ይኖራል::

በቅዱሳት መጻሕፍትም ሆነ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ በምድር የተሰጣቸውን ዕድሜ በአግባቡ በሥራ የተረጐሙ ብዙ መልካም ሰዎችን እናገኛለን:: ዘመን አልፎ ዘመን ሲተካም መልካም ሥራቸው ከትውልድ ትውልድ እየተሸጋገረ እስከ ዘመናችን ደርሷል:: በዓለም ፍጻሜም የሠሩት መልካም ሥራ ከአምላካቸው ዘንድ የዘለዓለም ሕይወትን ያገኛሉ::

በመሆኑም አዲስ ዘመን በተቀበልን ቁጥር ማሰብ የሚገባን በአዲስ ዓመት የምንሠራውን መልካም ሥራ ነው:: እያንዳንዱ ሰው ሊሠራው የሚገባው የራሱ የሆነ ኃላፊነትና ተግባር አለው::

ለሀገሩ ልማት ለሕዝቡ ዕድገት ማሰብ የሚገባው መላው የሀገሪቱ ዜጋ በመሆኑ በዘመናችን በረሃብና በበሽታ የምትታወቀውን ሀገራችንን ለማልማት መነሣት ይኖርበታል:: ከሌላው ዓለም በተለየ ሁኔታ በሀገራችን ኤች.አይ.ቪ ኤድስ በመስፋፋት ላይ መሆኑ ይነገራል:: ይህንን ለመከላከል የሁሉም ተሳትፎ አስፈላጊ ነው:: ልባችንንና እምነታችንን አንድ አድርገን እግዚአብሔር መድኃኒቱን እንዲሰጠን ከመለመን ጀምሮ በርካታ ተግባራት ይጠበቁ ብናል:: ሕገ እግዚአብሔርን በመጠበቅ ከዝሙት መራቅ የሁሉም ግዴታ ነው:: ሥልጣን ያለው መልካም ሥራ ከመሥራት ይልቅ ሥልጣኑን የሕዝብ ማስፈራሪያ ካደረገው ምንም ሳይሠራ ዘመናት ባለፉ ቁጥር እርሱም ያልፋል:: የሠራው መጥፎ ሥራ ግን ቀጣዩን ትውልድ አሁን ካለንበት ችግር ወደ ባሰ ችግር ከመክተቱም በላይ በታሪክ ፊት በመጥፎ ተግባር ሲወቀስ ይኖራል:: በእግዚአብሔር ዘንድም ፍርድ ይጠብቀዋል:: ስለዚህ እያንዳንዳችን በአዲሱ ዓ መት ከመጥፎ ተግባራችን ተመልሰን ለመልካም ሥራና ለልማት መዘጋጀት ይኖርብናል::

ወደ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ልጆች ስንመለስ ደግሞ ምእመናን የክርስትና ሕይወታችን አዲስ ለውጥ እንዲያገኝ ማድረግ ይኖርብናል:: ባለፈው ዓመት ካከናወንናቸው ተግባራት መካከል መልካም የሆኑትን አጠናክረን ለፍሬ ማብቃት አለብን:: ስለ ንስሐ፣ስለ ቅዱስ ቁርባን በመማር ዓመቱን ያሳለፍን በአዲሱ ዓመት የተማርነውን በሥራ በመተርጐም ንስሐ የምንገባበት፣ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን የምንቀበልበት መሆን ይገባዋል:: በሰበካ ጉባኤያት በንቃት በመሳተፍ ለቤተ ክርስቲያናችን ዕድገት የሚጠቅሙ የልማት ሥራዎችን ለመሥራት መዘጋጀት ይኖርብናል::

እያንዳንንዱ አጥቢያ የሕፃናት ማሳደጊያ፣የአዛውንት መጦርያ፣የችግረኞች መርጃ፣የወጣቶች መማሪያ ት/ቤት ወዘተ ያስፈልገዋል:: በየዓመቱ ጥቂት በጥቂት ለመሥራት ማቀድ አስፈላጊ ነው::

ሰንበት ት/ቤቶች ሃይማኖትንና ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን በማስተማር ረገድ በርካታ ተግባራትን ባለፉት ዓ መታት አከናውነዋል:: ብዙ ሰንበት ት/ቤቶች ሕፃናትንና ወጣቶችን በመለየት ተገቢውን ትምህርት በመስጠት ላይ ይገኛሉ:: አንድ ወጥ በሆነ ሥርዓተ ትምህርት ከመሥራት ጀምሮ በአጥቢያ ውስጥ የሚገኙትን ወጣቶች በሙሉ ለ ማስተማር ብዙ መሠራት አለበት:: የሕፃናትንና የወጣቶችን ክፍለ ጊዜ ለያይተው የሚያስተምሩ ሰንበት ት/ቤቶች ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ ሌሎችንም በትምህርት ደረጃና በዕድሜ የመለየቱን ሁኔታ ይበልጥ ከፍ ለማድረግ ለከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች፣ትምህርታቸውን ጨርሰው በሥራ ላይ ለሚገኙ ጎልማሶች ወዘተ ከፍ ያለ ደረጃ ያለው የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት ለማስተማር ማቀድ ይኖርባቸዋል::

የቤተክርስቲያናችን ሰባክያነ ወንጌል ምእመናንን በማስተማርና በመጠበቅ በኩል ተጠናክረው በነፃ ያገኙትን በነፃ በመስጠት ተግባር ሊጸኑ ይገባቸዋል:: እርስ በርስ መጠላላትንና መገፋፋትን ትተው በእርዳታና በተለያዩ ምክንያቶች ወደ ሀገራችን የገቡ መናፍቃንና ከሐዲያን ምእመናንን በማታለል ከዘለዓለም ሕይወት ከክርስቶስ እንዳይለዩ ሰባክያን ከመቼውም ጊዜ በላይ ሊተጉ ያስፈልጋል:: መንፈሳዊ ዕውቀቷና ትምህርቷ ሰፊ የሆነችው ቤተ ክርስቲያን መጻሕፍትና ሊቃውንትን በመጠየቅ የጐደለባቸውን በማሟላት በየትኛውም ቦታ ለሚነሣው ጥያቄ አጥጋቢ መልስ ለመስጠት መዘጋጀት አለባቸው:: በሀገራችን በጥምቀት ሀብተ ወልድ ስመ ክርስትና ያልተሰጣቸው ብዙ ወገኖቻችን ስላሉ ያሉትን በሃይማኖት አጽንተን ለእነዚህም ወንጌልን ለመስበክ መነሣት አለብን::

ካህናት አባቶቻችን አዲሱን ዓመት ሲቀበሉ ለልጆቻቸው ምን እንደሚያስተምሩና ልጆቻቸውን እንዴት እንደሚጠብቁ ማሰብ አለባቸው:: የምእመናን ሕይወት ከቅድስት ቤተ ክርስቲያን እንዳይለይ፣ምእመናን ለመልካም ሥ ራ እንዲነሡ ለማድረግ የንስሐ አባቶች ኃላፊነት ታላቅ ነው:: በመሆኑም ከእግዚአብሔር የተመረጡ እረኞች መንጋውን ለመጠበቅ ዘመናት በተለወጡ ቁጥር ኃላፊነታቸው እየከበደ የሚመጣ በመሆኑ ከዘመኑ ጥያቄ አንጻር ራ ሳቸውን አዘጋጅተው በመልካም ተግባር ላይ መልካም ተግባርን በመጨመር መጓዝ አለባቸው:: ሌባ መንጋውን እየነጠ ቀ እያዩ ዝም ብለው የሚተኙ መሆን የለባቸውም:: የእነርሱ ኃላፊነት ከሌላው ሁሉ የከበደ ነውና:: ይህንን ሳይወጡ ቢያልፉ በምድርም ሆነ በሰማይ ለምእመናን ሕይወት ተጠያቂ ይሆናሉ::

የማኅበረ ቅዱሳን አባላትም ከላይ የተዘረዘሩት ተግባራት ሁላችንንም የሚመለከት ነው:: ወደዚህ ማኅበር የተሰበሰብነው በገንዘባችን፣በዕውቀታችንና በጉልበታችን ቤተ ክርስቲያንን ለማገልገል በመሆኑ ይህንን አገልግሎታችንን በአዲስ ዓመት አጠናክረን ለማበርከት መነሣት አለብን:: እስከ ዛሬ በርካታ ተግባራት የተከናወኑ ቢሆንም ወደፊት ገና ብዙ ይቀረናልና በየተገኘንበት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ክህነት ያለን በክህነታችን፣ሰባክያን በማስተማር፣ የተለያየ ሙያ ያለን በሙያችን፣በሰንበት ት/ቤቶችና በሰበካ ጉባኤያት ማገልገል ይኖርብናል:: በአዲሱ ዓመት ባለፈው ያልሠራ ነውን ለመሥራት፣ የጀመርነውን ለማጠናከር መወሰን አለብን እንጂ ከአገልግሎታችን በመቀነስ ደክመናል እንረፍ ማለት አይገባም::

በአጠቃላይ በቅድስት ቤተ ክርስቲያን ዙሪያ የተሰበሰበ ትልቁም ሆነ ትንሹ፣ወንዱም ሆነ ሴቱ፣አዋቂውም ሆነ ልጁ፣እረኛውም ሆነ መንጋው አሮጌው ዓመት አልፎ አዲሱ ሲተካ በዓሉን ብቻ አክብሮ ቁጭ የሚል ከሆነ የተጣለበትን ሃይማኖቱን የመጠበቅ አደራ አልተረዳም ማለት ነው:: ባሳለፍነው ዓመት የቤተ ክርስቲያን ጠላቶች መ ሠሪ ተግባራቸውን ለመፈጸም ሲሯሯጡ አይተናል፣በስብከተ ወንጌል ሥራ በጠቅላይ ቤተ ክህነት በ120ው ቤተሰብ ጥሩ ሥራ የተሠራ ቢሆንም በሀገረ ስብከትና በአጥቢያ የተዋቀረው ገና ሥራ አልጀመረም:: አንዳንድ ጥንታውያን ገዳ ማት፣አድባራትና የአብነት ት/ቤቶች አሁንም ችግር አለባቸው:: ቅርሶቻችንን ከዘራፊዎች ለመጠበቅ ብዙ ቢሠራም ዘ ራፊዎቹ ግን አልተኙም:: ደጋፊ የሌላቸው የገጠር አብያተ ክርስቲያናት ተዳክመዋል፤ የአረማውያን ሰለባ የሆኑትም ጥቂቶች አይደሉም:: ስለዚህ አዲሱን ዓመት ስንቀበል የቤተክርስቲያን ኃላፊነት ያለብን ሁሉ ቆም ብለን ልናስብ ይገባል:: ካልሆነ በታሪክና በእግዚአብሔር ፊት ስንወቀስ እንኖራለን:: ሁላችንም በአዲስ ዓመት ለአዲስ ሥራ እንድንነሳ የእግዚአብሔር ቸርነት የቅድስት ድንግል ማርያም አማላጅነት አይለየን አሜን::

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር*

# ደብዳቤዎች

## ዛሬም አየሁት

ተሳክቶልኝ መጽሔታችሁን ሁልጊዜ እየገዛሁ ባላነብም ንቁ ተሳታፊያችሁ ከሆነው አብሮ አደግ ጓደኛዬ እየተዋስኩ አነባታለሁ:: ታዲያ መጽሔቷን መከታተል ከጀመርኩበት 1987 ዓ.ም. ጀምሮ ኀሊናዬን በሃምሳ አምስት ዓመታት ወደኋላ የወሰደችኝ ብቸኛ መጽሔት ባለፈው ሐምሌ/ነሐሴ ያወጣችኋት የ9ኛ ዓመት ቁጥር 3 እትም ናት ስል በእርግጠኝነት ነው:: ለምን? ብትሉኝ ያኔ የነበረኝን የተማሪነት ሕይወት ሁኔታ ሊያስታውስ የሚችል ሥዕል በፊት ለፊት ሽፋኗ ይዛ ወጥታለችና:: በሥዕል ከሚታዩት ደሳሳ ጐጆዎች የሚፈላውን ምሥጢር፣የተማሪ አስተማሪን ግንኙነት፣ ፍቅርን፣ መተሳሰብን ወዘተ... ዛሬም በምናቤ ወደኋላ ሄጄ እንዳይ አድርጋኛለች:: እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንን ይጠብቅ::

*ኮሎኔል ዘውገ ሽባባው*
*አ/አ*

## ከአንደበታችሁ ሥራችሁ

በጉጉት የምጠብቃትን መጽሔታችሁን እንደገዛሁ በፍጥነት የማነበው የማኅበራችሁን መልእክት ነው:: ምክንያቱ ከመልእክታችሁ ስለወቅቱ የቤተ ክርስቲያን አጠቃላይ ሁኔታ በሚገባ እረዳለሁና:: ባለፈው እትም ያስተላለፋችሁልን መልእክት ግን ስለ እናንተ ነው:: «ማኅበራችን መቼም ቢሆን ዓላማው አንድ ነው» በሚል:: አውቆ የተኛን ቢቀሰቅሱት ወይ አይልም እንደተባለ ወሳኙና በዚህ ጊዜ ሊሆን የሚገባውን መልካም ሥራችሁን በዓይኑ እያየ በጆሮው እየሰማ የለም እናንተ አጥፊዎች ናችሁ የሚል ሊኖር ይችላልና ያንን ማለታችሁ መልካም ነው:: የሆነ ሆኖ የእናንተን ማንነት ከአንደበታችሁ የበለጠ ሥራችሁ ይመሰክራልና ሥራችሁን ዐይቶ ለመረዳት ሳይፈልግ ስማችሁን ላጥፋ ቢል አትደነቁ::

*አቶ ሐጐስ ሀለፎም*
*አ/አ*

## ስሁሉም ይድረሰው

በሐመር 9ኛ ዓመት ቁጥር 2 እትም በአምደ ወራዙት ሥር «ይድረስ ለወጣቱ ሰባኪ»በሚል ርዕስ የተጻፈውን ጽሑፍ እስከዛሬ ድረስ አንብቤው አልጠገብኩትም:: ወቅታዊ፣ አስተማሪና ጠንካራ ጽሑፍ በመሆኑ:: እንደእኔ እንደእኔ ያ ጽሑፍ ተባዝቶና ታትሞ ለእያንዳንዱ ሰባኪ እና ለየአድባራቱ ስብከተ ወንጌል ክፍል ቢታደልና ቢጠቀሙበት እጅግ ጠቃሚ ነው::

*አንዳርጋቸው ባዩ*
*መተማ*

## ምን እንበላቸው?

እኔ ባለሁበት አካባቢ ሳይማሩ ምሁራን ሳይላኩ ልዑካን በመሆን ራሳቸውን «ሐዋርያት» ያደረጉ ሰዎች ተነሥተዋል:: እነዚህ ሰዎች ቀሚስ ለብሰው፣ በአንገታቸው ትልቅ መስቀል አንጠልጥለው በየሰው ቤት ሱባኤ ገብተናል በማለት በሽተኛ እንፈውሳለን አጋንንት እናስወጣለን በሚል ለእምነታቸው ቀናእያን የሆኑ ምእመናንን በማወናበድ ላይ ይገኛሉ:: ሥልጣነ ክህነት የላቸውም:: ድርጊታቸው ሁሉ ከሥርዓተ ቤተክርስቲያን ውጪ ነው:: እነዚህን ሰዎች ምን እንበላቸው?

*ዲ/ን ወንድማገኝ ታደሠ*
*ቦንጋ*

<u>ከአዘጋጁ:-</u> በሀገረ ስብከቱ በተዋረድ ከሚገኙ የቤተክርስቲያኒቱ ባለሥልጣናት ጋር በመተባበር ማንነታቸው ተገልጦ መፍትሄ የሚገኝበትን መንገድ ፈልጉ::

## ማንነትን ማጥቆር

የፖስታ አገልግሎት ድርጅት ሐምሌ 19/1993 ዓ.ም. ላወጣው የመጀመሪያ ቀን ቴምብር መግለጫነት ባሳተመው በራሪ ጽሑፍ ላይ አንዳንድ ምእመናን በዘልማድ የሚሉትን እንደ መላው ምእመንና እንደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አቋም በመቁጠር «ዓሣ በጾም ወቅት ይበላል» በሚል አትሞ አስራጭቷል:: በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር የሚኖሩ፣ የታሪክ ተመራማሪዎች፣ ቴምብር ሰብሳቢዎች ወዘተ... በሚደርሰው በራሪ ጽሑፍ እንደዚህ ዓይነት የተሣሣተ መረጃ መስጠት ቤተክርስቲያናችን በዓለም መድረክ ያላትን አቋም የሚያዛባ ነውና የሚመለከተው ሁሉ ተገቢውን እርምት እንዲያስወስድ ስል አደራ እላለሁ::

*ገዛኸኝ ሥራ ብዙ*
*ከፋርሚ*
*አ.አ.*

<u>ከአዘጋጁ:-</u> አንባብያችን ስለጥቆማዎ እናመሰግንዎታለን:: በአባሪነት በላኩልን በወረቀት ላይ እንዳገኘነው «...እንደልምድ ሆኖ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት እምነት ተከታዮች ዘንድ በጾም ወቅት በምግብነት ይዘወተራል:: »ይላል:: የጽሑፉ አዘጋጆች እንደዚህ ሲሉ ምእመናን በጾም ወቅት ዓሣ እንዲመገቡ ቤተ ክርስቲያን ታዛለች ከሆነ እርስዎ እንዳሉት ቤተ ክርስቲያን ያላለችውን ማለትና ወንጀልም ነው:: በጾም ዓሣ መብላት ጾምን እንደ መግደፍ እንደሚቆጠርና ክልክል እንደሆነ በሲኖዶስ ደንግጋለችና:: በዚህ ዙሪያ ስለሚነሱ ክርክሮችና ስለተሰጡ ውሳኔዎች በሐመር መጽሔት 5ኛ ዓመት ቁጥር 3 እትም በዝርዝር አቅርበናልና ሁሉም ያንን እንዲያነብ እንጋብዛለን::

## ግሩም ምሥጢር

ባለፈው 9ኛ ዓመት ቁጥር 3 እትም በዲያቆን ያሬድ ገ/መድኅን ደብረ ታቦር በሚል ርዕስ የቀረበው ትምህርት ብዙ ያላነበብነውንና ያልሰማነውን ትምህርት አስጨብጦናል:: እግዚአብሐር ለወንድማችን ፀጋውን ያብዛለት::

*ስርጉተ ሥላሴ*
*አዋሳ*

## ሴሳውም ይለመደው

በፊት በፊት ልጆቼን ይዤ ወደቅዳሴ ስሄድ የሚያሳቅቀኝ የሕጻናት ልጆቼ ረብሻ ነበር:: ሕጻናት በእጣኑ ሽታ፣ በከበሮው ድምድምታ፣ በጸናጽሉ ኮሽታ፣ በደወሉ ኪውታ ወዘተ...እየተቃኙ ማደጋቸው አስደሳች ቢሆንም በአንጻሩ የሕጻን አዕምሮ አቸው ስለማይነግራቸው በጸሎተ ቅዳሴው መሀል ሲጫጩሁ፣ ሲሯሯጡ አስቀዳሾችን ይረብሻሉና:: ባሳለፍናት ጾመ ማርያም ግን ይህ ሁሉ መሳቀቄ ቀርቶ በጽሙና በማስቀደሴ በእጅጉ ተደስቼአለሁ:: ምክንያቱም የአጥቢያዬ ጴጥሮስ ወጳውሎስ /አ.አ./ ሰንበት ት/ቤት በቅዳሴ ሰዓት ሕጻናትን በአዳራሹ ሰብስቦ የሚገባቸውን ትምህርት እየሰጠ እስከ ቅዱስ ቁርባኑ ድርገት ድረስ ስለሚያቆያቸው ነው:: በቅዱስ ቁርባኑ ጊዜም እንደድሮው ሕጻናት አይጋፉም፣ አይተረማመሱም:: የሴት የወንድ በሚል ፕሮግራም ሕጻናቱ እንደአዋቂዎች አደብ ገዝተው በሰልፍ ይቆርባሉ:: በእውነቱ ይህንን መልካም ተግባር በሌሎች አጥቢያዎች የሚገኙ የሰንበት ት/ቤቶችም ቢለምዱት መልካም ነው እያልኩ በዚሁ አጋጣሚ የጴጥሮስ ወጳውሎስ ሰንበት ት/ቤትን አመሰግናለሁ::

*ወ/ሮ ፍቅርተ ጐሣዬ*
*እና ሕጻን ቃልኪዳን ጃቢር*
*አ.አ.*

## ደስ አለኝ

በሐመር 9ኛ ዓመት ቁጥር 2 እትም ባወጣችሁት የደብረ ዘመዳ ማርያም ገዳም ታሪክ በእጅጉ ደስ አለኝ:: የአባቶችን ጽናት በሚገባ አሳይቶኛልና:: አሁንም ደስ እንዲለኝ የሰማዕቷን የቅድስት አርሴማን ታሪክ አውጡት:: ይህንን ያልኩበት ምክንያትም በዛው በሰሜን ወሎ ሀገረ ስብከት ከሲሪንቃ እልፍ ብሎ የሰማዕቷ ደብር ስላለ ነው::

*ሔዋን ለማ*
*ለንደን*

<u>ከአዘጋጁ</u>– እህታችን እንኳን ደስ አለዎት:: የቅድስት አርሴማን ታሪክ በሚመለከት የሚያገኙ ከሆነ በ2ኛ ዓመት ቁጥር 3 እትማችን ያወጣነው በመሆኑ ይፈልጉና ያንብቡት::

## እስኪ ጠይቁልን?

የግዕዝን ቋንቋ ማትሪክ ለመውሰድ በ1992 ዓ.ም. ተመዝግቤ ነበር:: ነገር ግን ባላወኩት ምክንያት ፈተናውን እንድወስድ የሚያደርገኝ ካርድ/ admission card / ሳይመጣልኝ ቀረ:: በ1993 ዓ.ም. ደግሞ በነገረ ሃይማኖት የተመረቀ አንድ ዲያቆን ወንድሜን ጨምሮ ተመዘገብን:: ነገር ግን እንዳለፈው አልመጣላችሁም ተብለን ሳንፈተን ቀረን:: በሌላም ቦታ ስንሰማ ያልተፈተኑ ብዙ ሰዎች አሉ:: ለምን? እባካችሁ መልሱን የሚመለከተውን ጠይቁና ንገሩን::

*ወለተ ኢየሱስ*
*ከሰቆጣ*

ከአዘጋጁ–ይህ ጥያቄ የብዙዎቻችሁ እንደሆነ ከሚደርሱን የደብዳቤ፣ የስልክና የአካል መልእክቶች እንረዳለን:: በመሆኑም ወደ ሀገር አቀፍ ፈተናዎች ድርጅት ጐራ ብለን ጠይቀናል:: የሰጡንም መልስ «አንድ ሰው የግእዝን ቋንቋ መፈተን የሚችለው ቋንቋውን በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት /ከ9–12/ በትምህርት ዓይነትነት ስለመውሰዱ ማሥረጃ ማቅረብ የሚችል ሲሆን ነው» የሚል ነው::

## ድንቅ ፍጻሜ

ከገባችበት ገብቼ መጽሔቷን አነባታለሁ:: በዲ/ን ኤፍሬም እሼቴ ሲቀርብ የነበረውን «ከባቢሎን ወንዞች አጠገብ» ጽሑፍ መጨረሻውን በጉጉት ስጠብቀው ነበር:: ሆኖም በ9ኛ ዓመት ቁጥር 3 እትም እዚሁ አዲስ አበባ ለሥራ መጥቼ ያለምንም ውጣ ውረድ መጽሔቷን አግኝቼ አነበብኳት:: እናም የአይሻን መጨረሻ ተረዳሁ:: በእውነቱ በዲ.ኤፍሬም የቀረበው ይህ ጽሑፍ ለሁላችንም በተለይ በውጭ ላሉ ወንድሞችና እህቶቻችን ጽናትን፣ ተጋድሎን የሚያስተምር ነው:: ወንድማችን ፀጋውን እንዲያባዛለት ጸሎቴ ነው::

*ዲ/ን ገ/እግዚአብሔር*
*ጉራጌ ዞን–ጉንችሬ*

## ሴሳውንም ያስብ

ሐመር 9ኛ ዓመት ቁጥር 3 እትም የወጣች ለት እንደልማዷ እጄ ገባችና ተስገብግቤ እንደረሃብተኛ አነበብኳት:: በይበልጥ የአይሻንና የሰሚራን ታሪክ ማንበብ አይበለው በአንድ ጊዜ ፋት አልኳት:: ይህ አልበቃት ብሎ ይቺ ስንዱ እመቤት የሆነች መጽሔት ሌላ ድንቅ ጉዳይም ሰንቃልን ኖሯል:: ይኸውም የሁበርት ጐርደንን /ዲ/ን ሰይፈ ሥላሴን/ ታሪክ:: በእውነቱ በጽሑፉም እንደተባለ የዚህ አሜሪካዊ ወንድማችን ታሪክ ለሁላችን ትምህርት ነው:: አይሻን ከምድረ አረብ፣ ሁበርትን /ዲ/ን ሰይፈ ሥላሴን/ ከምድረ አሜሪካ ወደቅድስት ሀገር ኢትዮጵያ /ወደ ተዋሕዶ/ ያመጣ እግዚአብሔር ሌላውንም እንዲሁ ያስብልን:: እናንተንም ቃለ ሕይወት ያሰማልን::

*ዘሪሁን ገብሩ*
*አ.አ.*

የሐመር መጽሔትና ስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ባወጣው የአጭር ልቦለድ ውድድር ከቀረቡት 18 ያህል ጽሑፎች ከአንደኛ እስከ አራተኛ የወጡት ዝርዝር

| ተ.ቁ | ርዕስ | ደራሲ | አድራሻ |
|---|---|---|---|
| 1 | ዝንጉው ምሥጢረኛ | ትዕግሥት አበበ | ደብረ ብርሃን /ሰሜን ሸዋ/ |
| 2 | ጌርጌ ሰኖን | ሞገስ ሰይፉ | ደብረ ማርቆስ |
| 3 | የዕድሜ ልክ ስጦታ | ስንታየው ሞገስ | ቅ/ዮሐንስ ወልደ ነጐድጓድ አዲስ አበባ |
| 4 | ይዲድያማራና ይዲድያ | ይዲድያ አሉን ባኩት | ናዝሬት |

የሽልማቱን ዝርዝር በሚቀጥለው ጋዜጣና መጽሔት ስለምናወጣ አሸናፊዎች ዝግጅት ክፍላችንን በስልክ ወይም በአካል በመቅረብ አንድትነጋግሩት ቢሆን::

# ጸሎተ ሃይማኖት

ባለፈው እትም በዚህ ርዕስ «ወበእንተ መድኃኒትነ ወረደ እምሰ ማያት» በሚለው የጸሎተ ሃይማኖት አንቀጽ ተነሥተን እግዚ አብሔር ለምን ሰው ሆነ? ለሚለው ጥያቄ ስድስት ነጥቦችን ተመልክተናል::: በዚህ እትም ደግሞ «ወረደ እምሰማያት፤ ተሰብአ ወተ ሠገወ እመንፈስ ቅዱስ ወእማርያም እምቅድስት ድንግል» በሚለው አንቀጽ ላይ ሰፋ ያለ ትንታኔ እናቀርባለን::

**«... ወረደ እምስማያት:: ተሰብአ ወተሠገወ እመንፈስ ቅዱስ ወእማርያም እምቅድስት ድንግል::»**

እጅግ በጣም ምጡቅ እና ረቂቅ የሆነው የአምላክ ሰው መሆን ምሥጢር እንዴት ዕፁብና ድንቅ እንደሆነ ቀደም ብለን አይተናል:: ነገር ግን ዕፁብነቱ እንዳይዘነጋ በየአንቀጹ ማስታወሱም ተገቢ ነው:: ሆኖም አእምሯችን በሚረዳው መጠን በመጻሕፍት እና በሊቃውንት የተገለጠልንን ያኽል እንመለከታለን::

## ወረደ እምሰማያት –ከሰማያት ወረደ

በመንፈስ ቅዱስ ግብር ሰው ሆነ ከሚለው በፊት ወረደ እምሰማያት የሚለውን መመልከት ይገባል:: ሰው የሆነው ማን ነው? ለሚለው መልስ ይሆናልና:: ወረደ እምሰማያት የሚለው ሐረግ በጸሎተ ሃይማኖት የሚነገረው በእግዚአብሔር መውረድ እና መውጣት ኖሮበት አይደለም:: እርሱ በባሕርይው ምሉዕ በኩለሄ ነውና:: መዝ 138÷7–10::

ከሰማያት ወረደ ማለት የ ማይታይ መለኰት ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም በነሣው ሥጋ በአጭር ቁመት በጠባብ ደረት ተወስኖ በትኅትና ታየ፣ ተገለጠ ማለት ነው:: ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ «እግዚአብሔርን የመምሰል ምሥጢር ያለጥርጥር ታላቅ ነው፤ በሥጋ የተገለጠ፣ በመንፈስ የጸደቀ፣ በመላእክት የታየ፣ በአሕዛብ የተሰበከ፣ በዓለም የታመነ፣ በክብር ያረገ::» በ ማለት እንደተናገረ:: 1ጢሞ 3÷16::

ቅዱሳት መጻሕፍት የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ከሰማያት መውረድ በሚገባ ገልጠ ውልናል:: ወደ ዝርዝሩ ከመግባታችን በፊት ሰማያት ማለት እነማን ናቸው? የሚለውን መረዳት ይገባል:: ምክንያተ-ም «ሰማያት» በሚል የሚጠሩ የተለያዩ ሰማያት አሉና::

በሥነ ፍጥረት ትምህርት ሰባት ሰማያት አሉ:: እነዚህም በሦስት ዓይነት ይታያሉ:: ከእነዚህም ሌላ ጠፈሩ ሰማይ እየተባለም ይጠራል:: እነዚህን አራት «ሰማያት» በሚል የተጠሩትን ማወቅ ከሰማያት ወረደ የሚለውን ሐሳብ የበለጠ ያብራራ ልናልና አስቀድሞ ማየቱ ይገባል::

1. ጠፈር:– ከምድር በላይ የሚታየው ዓይናችንን ሽቅብ አቅንተን ስንመለከት የሚታየን የዓይናችን ማረፊያ ሰማይ ይባላል:: ወንጌል «ወደ ሰማይ ወፎች ተመልከቱ» ሲል ይህንን ያመለክታል:: ማቴ 6÷26:: ከምድር ከፍ ብለው የሚበሩ ናቸውና::

«ወደ ሰማይ ተመልከት÷ ከዋክብትንም ልትቆጥራቸው ትችል እንደሆነ ቁጠር» በሚለው ኃይለ ቃልም ውስጥ ሰማይ የሚለው ይኸንኑ ያመለክታል:: ዘፍ 15÷5:: «ሰማይና ምድር ያልፋል ቃሌ ግን አያልፍም» የተባለውም ለዚህኛው ሰማይ ነው:: ሉቃ 21÷33፣ ራእይ 20÷11:: ሆኖም ግን ከሰባቱ ሰማያት አይቆጠርም::

2. ዓለመ መላእክት:– ቅዱሳን መላእክት በየነገዳቸው የሚኖሩባቸው ከሰባቱ ሰማያት የሚቆጠሩ ሦስት ሰ ማያት አሉ:: እነርሱም ኢዮር፣ ራማ እና ኤረር በመባል ይታወቃሉ::

«ከእነዚህ ከታናናሾች አንዱን እን ዳትንቁ ተጠንቀቁ፤ መላእክቶቻቸው በሰማያት ዘወትር በሰማያት ያለውን የአባቴን ፊት ያያሉ እላችኋለሁና::» ባለው ውስጥ «መላእክቶቻቸው በሰ ማያት» ሲል መኖሪያቸውን ያመለክ ታል:: ማቴ 18÷10:: «ሰማያት» ብሎ ማብዛቱም ሦስት መሆናቸውን ወይም ከአንድ በላይ የመላእክት መኖሪያ ሰ ማያት እንዳሉ ያሳያል:: «ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት ወሰላም በምድር ሥምረቱ ለሰብእ–በሰማያት ለእግዚአብሔር ምስጋና፣ በምድርም ሰላም ለሰው ልጆችም በጐ ፈቃድ» በሚለው የመላእክት ዝማሬ ውስጥም በሰማያት ምስጋና ሆነ ማለት በዓለመ መላእክት የሚፈጸመውን ለእግዚአብሔር የማቀርበውን የማያልቅ ውዳሴ ፣ ቅዳሴ ያስረዳል:: ሉቃ1÷14::

ቅዱስ ጳውሎስም «እኛ ብንሆን ወይም ከሰማይ መልአክ፣ ከሰበክንላችሁ ወንጌል የሚለይ ወንጌልን ቢሰብክላችሁ፣ የተረገመ ይሁን:: «ብሎ በተናገረው ውስጥ የሰማይ መልአክ ማለቱ ያንኑ ያጠይቃል:: ገላ 1÷8:: እንዲሁም መጽሐፍ «የሰማይ መላእክት» ሲል የመላእክት መኖሪያቸው ሰማይ እንደሆነ መናገር ነው:: ማር13÷32:: የጌታ መልአክ ከሰማይ ስለወረደ የሚለውም በተመሳሳይ የመላእክትን መኖሪያ ያሳያል:: ማቴ 28÷2:: ጌታ ከሰማያት ወረደ ሲባል ከእነዚህኞቹ ሰማያት ማለት አይደለም:: እርሱ መልአክ አይደለምና:: ዕብ 1÷4 ፣ 2÷16::

3. መንግሥተ ሰማያት:– ቅዱስ ጳውሎስ «...አገራችን በሰማይ ነው::» ሲል መንግሥተ ሰማያትን ያመለክታል:: ፊል 3÷20:: እርሷም ሰማያዊት ኢየሩሳሌም በመባል ትታወቃለች:: ዕብ 12÷22:: «ጽድቅ የሚኖርባትን አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር እንደተስፋ ቃሉ እንጠ ብቃለን» የተባለላት ይህች ናት:: 2ጴጥ 3÷13፣ ራእይ 21÷1፣ ማቴ 5÷10:: እግዚአብሔር የፈቀደላቸው ጻድቃን ወደዚህች ሰማይ የሚገቡት በዳግም ምጽአት ሲሆን እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ግን ገብታበታለች:: ጌታችን ከሰማያት ወረደ ስንል ግን ከዚ ህም አይደለም::

4 <u>መንግሥተ እግዚአብሔር</u>:– ከኢዮር፣ ራማ፣ ኤረር እና መንግሥተ ሰማያት በላይ ሦስት ሰማያት አሉ:: እነርሱም ሰ ማይ ውዱድ ፣ መንበረ መንግሥት እና መንበረ ጸባዖት /ጽርሐ አርያም/ በመባል ይታወቃሉ:: ሰማየ ሰማያትም ይባላሉ:: እግዚአብሔር ምሉዕ በኩለሄ ነው ብንልም ልዕልናውን ለማሳየት በሰማያት የምትኖር ብለን እንድንጠራው ታዘናል:: ማቴ 6÷9፣5÷16:: «ከቅዱስ ማደሪያህ ከሰማይ ጐብኝ» ተብሎ የተጻፈውም ይህንን ያመለክታል:: ዘዳ 26÷15:: በነቢዩ በቅዱስ ዳዊት «እግዚአብሔር ዙፋኑን በሰማይ አዘጋጀ፣ መንግሥቱም ሁሉን ትገዛለች» ተብሎ የተጻፈውም እግዚ አብሔር ስለ ልዕልናው መንግሥቱን በሰ ማይ ማድረጉን ይናገራል:: መዝ 102÷19::

ከላይ ከተጠቀሱት አራት ዓይነት ሰማያት አንፃር ወልደ አብ ከሰማያት ወረደ የተባለው መንግሥተ እግዚአብሔርን ይጠቅሳል:: ስለሆነም ከሰማያት ወረደ ማለት ቅድመ ሥጋዌ ቃል ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በአንድነት በሦስትነት ሲሠለስ ሲቀደስ ከነበረበት ሰማያዊ መንበሩ መምጣቱን ለማስረዳት ነው::

በወንጌል «ከሰማይም ከወረደው በቀር ወደ ሰማይ የወጣ ማንም የለም÷ እርሱም በሰማይ የሚኖረው የሰው ልጅ ነው:: » በማለት ጌታችን የተናገረውን ቃል ፍቁረ እግዚእ ቅዱስ ዮሐንስ ጽፏል:: ዮሐ 3÷13:: ከቃሉ እንደምንረዳው ይህንን የተናገረው ራሱ ወልደ አብ ወልደ ማርያም ሲሆን ራሱን በዚህ ሁኔታ ሲገልጥ ከእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የነሣውን ሥጋ ተዋሕዶ ነው::

በዚህ የመጽሐፍ ክፍል «ከሰማይ የወረደው» የሚለው ቃል በቀጥታ የሚያመለክተው ወልድ ከመንግሥተ እግዚአብሔር የመጣ ፍጹም አምላክ መሆኑን ነው:: ከሰማይ መውረድ ማለት ለተልዕኮ ከሰማይ ወደ ምድር እንደሚመጡት እንደ መላእክት ሳይሆን በተዋሐደው ሥጋ መገለጡን ያሳያል:: ምክንያቱም ከሰዎች ጋር በተዋሐደው ሥጋ በምድር እየተመላለሰ በነበረበት በዚያ ጊዜ በሰማያትም ያለ መሆኑን ሲገልጥ «እርሱም በሰማይ የሚኖረው የሰው ልጅ ነው» ብሏል::

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ምንም እንኳ በአጭር ቁመት በጠባብ ደረት ተወስኖ በምድር ከሚኖሩት ሰዎች ጋር እየተነጋገረ፣ እያስተማረ፣ እየተመላለሰ ባጠቃላይም እየኖረ ሳለ ምንም ዓይነት የጊዜ ልዩነት ሳያስፈልገው በዚያው ሰዓት ከባሕርይ አባቱ ከአብ ከባሕርይ ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በመለኮታዊ ክብሩ በኪሩቤል መንበሩ ያለ መሆኑን አስረዳን:: ሥጋን በተዋሐደ ጊዜ ጀምሮ ከየማነ አብ ከዘባነ ኪሩብ አልተለየም ከተባለ «ከሰማይ የወረደው መባል ለምን አስፈለገ?» ሊባል ይችላል::

1. አምላክነቱን ለማስረዳት:- ጌታችን እንደ ሰዎች ልማድ ሳይሆን በመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ ሰው በመሆኑ የብዙዎች ጥያቄ ይህ ማን ነው? የሚል ነበር:: በዚህም የተነሣ «አንዳንዶች የዮሴፍ ልጅ፣ ሌሎች መጥምቁ ዮሐንስ፣ ሌሎችም ኤልያስ፣ ሌሎችም ኤርምያስ፣ ሌሎችም ከነቢያት አንዱ » እያሉ ተሰናክለውበታል:: ማቴ 13÷55፣ 16÷14:: ሰዎች እንዲህ በተሳሳተ ጐዳና ሲነጉዱ ጌታችን ግን ከሰማያት የወረድሁ ነኝ በማለት ሰማያዊ አምላክ መሆኑን ገለጠልን::

2. ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ያለውን ትክክልነት ለማጠየቅ:- ቀደም ሲል እንደገለጥነው ከሰማያት ወረደ በሚለው ውስጥ ሰማያት የተባሉት መንግሥተ እግዚአብሔርን ያመለክታሉ:: በዚህ ሰማይ ላይ ከፈጣሪ በቀር ፍጡር አይኖርባቸውም:: ስለሆነም ራሱ ጌታችን «ከሰማይ ከወረደው በቀር ወደ ሰማይ የወጣ ማንም የለም» በማለት ተናገረ:: የመጣው ከመለኮታዊ ዙፋን ነውና በዚያ ዙፋኑ ላይ ከአምላክ በስተቀር ማንም ሊያድርበት ሊኖርበት ሊጠጋውም ከቶውኑ አይችልም:: ነቢያት ስለሰው ልጆች ድኅነት ወደ እግዚአብሔር ሲጮኹ «እጅህን ከአርያም /ከሰማይ/ ላክ አድነንም:: » ብለው ነበር:: መዝ 143÷7:: እጅ የተባለ ወልድ ሲሆን የሚመጣው ከሰማይ ከአባቱ ጋር በትክክልነት ከተቀመጠበት ዙፋን ነው::

ቀዳሜ ሰማዕታት ቅዱስ እስጢፋኖስ መከራ ሲቀበል «እነሆ ሰማያት ተከፍተው የሰው ልጅም በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ አያለሁ::» በማለት አምላክ ወልደ አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም የነሣውን ሥጋ እንደ ተዋሐደ በአብ ቀኝ በሰማያዊ ዙፋኑ መቀመጡን አስረድቷል:: የሐ. ሥራ 7÷56:: ሊቀ ሐዋርያት ቅዱስ ጴጥሮስም « እርሱም መላእክትና ሥልጣናት ኃይላትም ከተገዙለት በኋላ ወደ ሰማይ ሄዶ በእግዚአብሔር ቀኝ አለ:: » ብሏል:: 1ጴጥ 3÷22::

በዚህም ምክንያት «ከአብ ወጥቼ ወደ ዓለም መጥቻለሁ፤ ደግሞ ዓለምን እተወዋለሁ ወደ አብም እሄዳለሁ»:: ሲል ጌታችን ተናግሯል:: ዮሐ 16÷28:: የሚሄደውም /የሚያርገውም/ አስቀድሞ ወደ ነበረበት ለቅጽበት እንኳን ወዳልተለየው ሰማያዊ ዙፋኑ ነውና «እንግዲህ የሰው ልጅ አስቀድሞ ወደ ነበረበት ሲወጣ ብታዩ እንዴት ይሆናል?» ብሏል:: ዮሐ 6÷62::

እግዚአብሔር ምሉዕ በኩለሄ ነውና መውጣት መውረድ የለበትም:: ነገር ግን ለሰዎች እየታየ የሚያርግ ስለሆነ « ወደ አብ እሄዳለሁ» ፣«ወደ ነበረበት ሲወጣ» በሚሉ ቃላት ተገልጧል:: ከተዋሕዶ በኋላ ሥጋ የመለኮትን ገንዘብ ገንዘቡ ስላደረገ መለኮቱም የሥጋን ገንዘብ ገንዘቡ ስላደረገ ለያይቶ መናገር አይገባም:: በዚህም ሁኔታ ጌታችን «አስቀድሞ ወደ ነበረበት ሲወጣ ብታዩ» ሲል ተናገረ:: ሥጋ አስቀድሞ በመንግሥተ እግዚአብሔር የነበረ ሆኖ አይደለም:: ነገር ግን ከተዋሕዶ በኋላ ዘመን የሚቆጠርለት ሥጋ ዘመን የማይቆጠርለትን የመለኮትን ገንዘብ የራሱ በማድረጉ በተዋሐደው መለኮት ባገኘው ክብር «አስቀድሞ ወደ ነበረበት» ተብሎለታል::

ከሰማይ የወረደው አካላዊ ቃል ይሁን እንጂ ሥግው ቃል ኢየሱስ ክርስቶስ «ከሰማይ የወረደ ሕያው እንጀራ እኔ ነኝ» በማለት ከተዋሕዶ በኋላ ይህ የሥጋ ይህ የመለኮት ብሎ መነጣጠል፣ መለያየት እንደማይገባ አስረዳ:: ዮሐ 6÷41፣51:: ጌታችን ባረገ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ወደ ሰማይ በትኩረትና በአድናቆት ተገርመው እየተመለከቱ ሳለ ሁለት ነጫጭ የለበሱ ቅዱሳን መላእክት ተገልጠው«... ከእናንተ ወደ ሰማይ የወጣው ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲሄድ እንዳያችሁት ፣ እንዲሁ ይመጣል::» በማለት ነግረዋቸዋል:: ሥራ 1÷11:: «ወደ ሰማይ ወጣ» ማለት ቅዱስ እስጢፋኖስ ጌታን ወዳየበት ሰማያዊ መንበር ማለት ነው:: በዚያ ሰማይ ቅዱስ እስጢፋኖስ ከፍጡራን መካከል ማንንም አላየም:: ስለዚህ ከሰማያት ወረደ ስንል የባሕርይ አምላክነቱን መግለጣችን ነው::

ሊቀ ሐዋርያት ቅዱስ ጴጥሮስ «የእርሱን ግርማ አይተን እንጂ በብልጠት የተፈጠረውን ተረት ሳንከተል የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ኃይልና መምጣት አስታወቅናችሁ:: ከገናናው ክብር በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው የሚል ድምጽ በመጣለት ጊዜ ከእግዚአብሔር አብ ክብርንና ምስጋናን ተቀብሎአልና፣ እኛም በቅዱሱ ተራራ ከእርሱ ጋር ሳለን ይህን ድምፅ ከሰማይ ሲወርድ ሰማን::» ብሎ በሰጠው ምስክርነት ውስጥ የወልደ እጓለ እመ ሕያው የኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም አምላክነት ተገልጧል:: 2ጴጥ 1÷16–18::

«የእርሱን ግርማ አይተን » ማለቱ በደብረ ታቦር ተራራ ላይ ጌታችን የገለጠላቸውን ብርሃን መለኮቱን ሲሆን «የኢየሱስ ክርስቶስን ኃይልና መምጣት አስታወቅናችሁ» ማለቱ ደግሞ «ኃይል» ብሎ መለኮታዊ ሥልጣኑን «መምጣት» ብሎ ከሰማይ መውረዱን አመልክቶናል:: ጌታችን ከባሕርይ አባቱ ከአብ ምስጋና እና ክብር የተሰጠው መሆኑን ከገለጠ በኋላ የአብ ድምጽ ከወዴት እንደሆነ ሲናገር «ከሰማይ ሲወርድ ሰማን» ብሏል:: አብ ድምጹን ሲያሰማ ከሰማይ መንበሩ ሳይለቅ ነው:: ጌታችን እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ እንዳለ አታምኑምን... እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ እንዳለ እመኑኝ» ሲል በተናገረው መሠረት አብ ባለበት ወልድም አለና አብ ባለበት ሰማይ ወልድም በዚያ ይኖራል:: ዮሐ 14÷10–11:: በዚህ አንፃር በጸሎተ ሃይማኖትን «ከሰማያት የወረደ» በማለት የወልድን ልዑል ባሕርይነት እና መለኮታዊ ሥልጣን እንመሰክራለን::

## ተሰብአ ወተሠገወ– ሰው ሆነ

ከላይ የቃልን ከሰማይ መውረድ አስመልክተን መጠነኛ ማብራሪያ ሰጥተናል:: ያ ቃል ወይም ወልድ ከሰማያት ወርዶ ምን ሆነ? የሚለውን ምላሽ የምናገኘው በዚህኛው ንዑስ ርእስ ሥር ይሆናል:: ከሰማያት ወረደ ካለ በኋላ ሰው ሆነ የሚለው ይከተላል::

ይህንን ምሥጢር ለመረዳት ረድኤተ እግዚአብሐርን በጸሎት መጠየቅ የግድ ያስፈልጋል:: ቅዱስ ያዕቆብ «ከእናንተ ማንም ጥበብ ቢጐድለው፣ ሳይነቅፍ በልግስና ለሁሉ የሚሰጠውን እግዚአብሔ

ርን ይለምን፣ ለእርሱም ይሰጠዋል» እንዳለ:: ያዕ 1÷5:: የእግዚአብሔር ሰው መሆን ምሥጢር የተገለጠለት ቅዱስ ጴጥሮስን ጌታ « ይህን የሰማዩ አባቴ እንጂ ሥጋ እና ደም አልገለጠልህም እንዳለው» ማቴ 16÷17–19:: ሐዋርያዊ ቅዱስ አትናቴዎስም «በዚህ ሃይማኖት ትጸና ዘንድ በአርያም የለ እግዚአብሔርን ለምነው፤ ከሥጋዊ ከደማዊ ፈላስፋ ይህን ልትማር ለአንተ አይገባም፤ በአርያም ካለ ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው እንጂ» ብሏል:: ሃይ.አበ. 21÷12::

## ቃል ሥጋ ሆነ

ለፍጥረታት ሁሉ መነሻና መድረሻ መጀመሪያና መጨረሻ አላቸው:: የሁሉ አስገኝ÷ የሁሉ ፈጣሪ እግዚአብሔር ግን መጀመሪያ የሌለው ቀዳማዊ፣ ፍጻሜም የሌለው በዚህ ጊዜ ነበረ በዚህ ጊዜ አልነበረም የማይባል ዘላለማዊ ነው:: በመጽሐፍ «አቤቱ፣ አንተ ግን ትኖራለህ፤ ሁላቸው እንደ ልብስ ያረጃሉ፤ እንደ መጐናጸፊያም ትለውጣቸዋለህ፤ ይለውጡማል አንተ ግን ያው አንተ ነህ፣ ዓመቶችህም ከቶ አያልቁም» እንደተባለ:: መዝ 101÷25–27::

በዚህ ጊዜ ተገኙ በዚህ ጊዜ ያልፋሉ መባል ከሌለባቸው ከማይለወጡ እና ከማይናወጡ በቅድምና በአንድነት በሦስትነት ከነበሩት ከሥላሴ አንዱ አካል ስለሆነው አካላዊ ቃል ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ ሲናገር እንዲህ ብሏል::

«በመጀመሪያው ቃል ነበረ፣ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፣ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ:: ይህ በመጀመሪያው በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ:: ሁሉ በእርሱ ሆነ፣ ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም::» ዮሐ 1÷1–3::

«በመጀመሪያው ቃል ነበረ» ሲል «መጀመሪያ የሚለው ቃል ምንን ያመለክታል? በኦሪት ዘፍጥረት መግቢያ ላይ «በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ:: »ተብሏል:: ዘፍ 1÷1:: በዮሐንስ ወንጌል «መጀመሪያ» በተባለው እና በኦሪት ዘፍጥረት «መጀመሪያ» በተባለው መካከል እጅግ በጣም ሰፊ ልዩነት አለ::

በኦሪት ዘፍጥረት «መጀመሪያ» የተባለው እግዚአብሔር ሥነ ፍጥረት መፍጠር የጀመረበትን የሥፍረ ዘመን መነሻ ለማመልከት የገባ መነሻው የታወቀ እና የተወሰነ ነው:: ይህም ራሱ እግዚአብሔር ወልድ በቃልነቱ ለይኩን /ይሁን/ እያለ የፈጠረ እንደመሆኑ እርሱ የፈጠረበትን የፍጥረት መነሻ የሚያመላክት ቅጽል መሆኑ አያጠራጥርም:: ለመጀመሪያ ጊዜ «ይሁን» ተብሎ የተፈጠረ ብርሃን ነው:: ዘፍ 1÷3–5:: የዚያ ብርሃን እና ኋላም ተከትለው የመጡት ፍጥረታት ለይኩን እየተባሉ የተፈጠሩት እና ሌሎችም በወልድ ቃልነት የተፈጠሩ ናቸው:: ፈጣሪነቱን ቅዱስ ጳውሎስ ሲናገር «ክርስቶስ ኢየሱስን ጌታ እንደሆነ እንጂ ራሳችንን አንሰብክምና፣ ስለ ኢየሱስም ራሳችንን ለእናንተ ባሪያዎች እናደርጋለን:: በክርስቶስ ፊት የእግዚአብሔርን የክብሩን ዕውቀት ብርሃን እንዲሰጥ በልባችን ውስጥ የበራ በጨለማ ብርሃን ይብራ ያለ እግዚአብሔር ነውና::»ብሏል:: 2ቆሮ 4÷5–6::

ስለዚህ ብርሃን ይሁን ሲል እግዚአብሔር በቃሉ ተናግሮ ብርሃንን እምኀበ አልቦ ኀበ ቦ /ካለመኖር ወደ መኖር/ ያመጣበት አካላዊ ቃል፤ ብርሃን ከተፈጠረበት ቀን ወይም የመጀመሪያ ቀን ከተባለው በፊት የኖረ መሆኑ አያጠራጥርም:: ስለዚህ «በመጀመሪያው ቃል ነበረ» የሚለው ብርሃን ከተፈጠረበት ቀን በፊት የነበረ መሆኑን ያሳያል::

ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ «በመጀመሪያ ቃል ነበረ» ብሎ ያቀመቢሆን ኖሮ ሊቀ ነቢያት ሙሴ «በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ» ካለው ጋራ ያለው ልዩነት ባልተገለጠ ነበር:: ነገር ግን ቁጥር 3 ላይ «ሁሉ በእርሱ /በቃል/ ሆነ፣ ከሆ ነውም አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም » ብሎ አስቀምጦልናል:: ከተ ፈጠሩት ፍጥረታት መካከል ሰማይና ምድር የሚገኙ በመሆናቸው እነር ሱንም ወልድ በቃልነቱ ከባሕርይ አባቱ ከአብ ከባሕርይ ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ ሳይለይ ፈጥሯል ማለት ነው:: «እኔ ፊተኛ ነኝ እኔም ኋለኛ ነኝ:: እጄም ምድርን መሠርታለች፤ ቀኜም ሰማያትን ዘርግታለች::»ተብሎ እንደተጻፈ:: ኢሳ 48÷12:: በዚህ ኃይለ ቃል እኔ ባዩ ወልድ ነው:: ስለዚህ ሰማይና ምድር የተፈጠሩበት «መጀመሪያ» ቃል ነበረ ከተባለበት «መጀመሪያ» በምንም ሁኔታ አይገናኝም::

ቅዱስ ዳዊትም« በእግዚአብሔር ቃል ሰማያት ጸኑ ሠራዊታቸውም በአፉ እስትንፋስ» ብሏል:: መዝ32÷6:: ደግሞም «ምድር ሁሉ እግዚአብሔርን ትፍራው... እርሱ ተናግሯልና ሆኑ፣ እርሱ አዘዘ ጸኑም» በማለት አጽንቶታል:: መዝ 32÷8–9:: ተናጋሪው ቃል ነው፣ በቃሉ ፍጥረታት ሁሉ ተፈጠሩ:: ስለዚህ የሰማይና የምድር ፈጣሪ ለመሆኑ ምንም የሚያጠያይቅ ነገር የለበትም::

ሊቀ ሐዋርያት ቅዱስ ጴጥሮስም «ሰማያት ከጥንት ጀምረው ምድርም በእግዚአብሔር ቃል ከውኃ ተጋጥማ በውኃ መካከል እንደነበሩ ወደው አያስተውሉም» በማለት የእግዚአብሔር ቃል ወልድ እንደፈጠራቸው አስተምሯል:: 2ጴጥ 3÷5:: ቅዱስ ጳውሎስ ደግሞ «ዓለሞች በእግዚአብሔር ቃል እንደተዘጋጁ» ብሎ ያ ቃል የእነዚህ ዓለማት ሁሉ ፈጣሪ መሆኑን አስረድቷል:: ዕብ 11÷3 ቆላ 1÷15–17::

እግዚአብሔር ቃል ወልድ የሁሉ ፈጣሪ ነውና ቅዱስ ዮሐንስ «በመጀመሪያ ቃል ነበረ» ማለቱ ምንም ዓይነት ፍጥረት ሳይፈጠር በመለኮታዊ ክብር፡ በአምላካዊ ዙፋኑ ከባሕርይ አባቱ ከአብና ከባሕርይ ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ያለውን ኑባሬ ማመልከቱ መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል:: ለሰማይና ምድር «ፈጠረ» የተባለ ሲሆን ለቃል ግን «ነበረ» መባሉን ማስተዋል ይገባል:: «ፈጠረ» ማለትና «ነበረ» የሚሉት ግሶች እንደሚያስረዱት ከመፍጠር በፊት መኖር ያስፈልጋል:: ስለዚህ ቃል ሰማይ ንና ምድርን ከመፍጠሩ በፊት በመን ግሥቱ፣ በሥልጣኑ፣ በኃይሉ፣ በችሎቱ ነበረ ማለት ነው::

ቅዱስ ዮሐንስ የቃልን በመጀመሪያ መኖር ተናግሮ ብቻ አላቆመም:: ከዚያው ቀጥሎ ከማን ጋር እንደነበረ ነግሮናልና:: «ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ::» ብሏልና:: ዮሐ 1÷1:: ከልብ እና እስትንፋስ ተለይቶ ለብቻው የሚኖር ቃል የለምና:: ቃል አለ:: ወይም ነበረ:: ከተባለ ከማን ጋር? የሚለው መጠየቁ የማይቀር ነው:: በዚህ ጥያቄ ልቡናችንን እንዳይባዝን ያ ቃል ከእግዚአብሔር አብ/ከልቡ/ ጋር በሕልውና አንድ ሆኖ የነበረ መሆኑን አስረግጦ ነገረን:: በቅድምና የነበረ ቃል በቅድምና ከነበረ አብ ጋር የዘመን ልዩነት በመካከላቸው ሳይኖር በአንድነት መኖራቸውን ለማመልከት «ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ» ብሎ አስታወቀ::

ወንጌላዊው ስለ ዝርው ቃል የተናገረ እንዳይመስል ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ ብሎ አላበቃም:: አስከትሎ «ቃልም እግዚአብሔር ነበረ» ብሏል:: ያ በመጀመሪያ የነበረው ለዘመኑ ጥንትና ፍጻሜ የሌለው ቃል እግዚአብሔር መሆኑን በቁርጥ ቃል ነገረን:: ከዚህ ወዲያ እንደምን አድርጐ ስለ ቃል ሌላ ማሰብ ይቻላል? የማይለወጥ፣ የማያልፍ፣ የማይሻር፣ የማያረጅ፣ የማይቀማ፣ መሆኑን ዐውቀናል::

ቅዱስ ዮሐንስ ወደ ማይፈለግ ምርመራ ውስጥ ገብተን ቀልጠን እንዳንቀር የቃልን ቀዳማዊነት በሚገባ አስረግጦ እና መጥኖ ከገለጠ በኋላ«ቃልም ሥጋ ሆነ» በማለት መዳረሻችንን ወሰነልን:: ዮሐ 1÷14::

## እንዴት ሥጋ ሆነ?

ይቀጥላል



### ስመንፈሳዊ መዝሙር ቤቶች

የሊቀ መዘምራን ኪ. ነጥበብ ወልደ ቂርቆስ ቁጥር 2፣ 3 እና 5 እንዲሁም የዘማሪ ብዙአየሁ ተመስገን ቁጥር 1 እና ቁጥር 2 የመዝሙር ካሴቶች ከሸርና ስቲከር በጅምላ እያሠራጨን ስለሆነ አዲስ አበባ ከሚገኘው ማከፋፈያ ልትወስዱ የምትችሉ መሆኑን እንገልጻለን::

ዋና አከፋፋይ :–ማኅበረ ቅዱሳን
ስልክ 565159

# መስቀል

ሊቀ ጠበብት ሐረገ ወይን አገዘ



## ቅድመ ታሪክ

በሕግ ደረጃ ሰውን በስቅላት መቅጣት የጀመሩት ፋርሶች መሆናቸው ይነገራል:: ሄሮዶቱስ የተባለው ግሪካዊ ታሪክ ጸሐፊ የፋርሱ ንጉሥ ዳርዮስ/522–486 ዓ.ፍ/ 3000 ነዋሪዎችን በስቅላት መቅጣቱን ጽፏል:: ግሪካውያንም ይህንን ባሕል /ምናልባት ከፋርስ ወስደው ሳይሆን አይቀርም/ ተጠቅመውበታል:: ታላቁ የግሪክ ንጉሥ እስክንድር ግዛቱን አስፍቶ መላ ከነዓንን በያዘ ጊዜ በጢሮስ ከተማ 2000 ሰዎችን በስቅላት መቅጣቱ ተጽፏል::

በ267 ዓ.ፍ. /ዓመተ ፍዳ/ አንጥያኮስ 4ኛ ይሁዳን በእጁ ሲያስገባ ለእምነታቸው ቀንተው ግሪካዊውን አምልኮ ጣዖት ያልተቀበሉትን አይሁድ በስቅላት መቅጣቱን ዮሴፍ ወልደ ኩርዮን ዘግቧል:: /Joseph. Ant.12÷256/ በአይሁድ ዘንድ ስቅላት በተግባር የዋለው ከዚህ በኋላ ነው:: የሐስሞናውያን ሥርወ መንግሥት /167–37 ዓ.ፍ./ አይሁድን ሲገዛ ሰዱቃዊው ሊቀ ካህናት ኢያንዮስ /Janneus/ /103–76ዓ.ፍ./ 800 ፈሪሳውያንን በስቅላት ቀጥቷል:: /Joseph. Ant.13÷380–83; Jw. 1÷97–98/ ::

ሮማውያን ይህንን የስቅላት ቅጣት ከፋርስም ከግሪክም ወርሰው ተጠቅመውበታል:: ሲሴሮ የተባለው ሮማዊ የሥነ መንግሥት ሊቅ ስቅላትን የመጨረሻ ቅጣት (smmum supplicium) በማለት ይጠራዋል::

በኦሪት ሕግ «ማንም ሰው ለሞት የሚያበቃውን ኃጢአት ቢሠራ እንዲሞትም ቢፈረድበት በእንጨትም ላይ ብትሰቅለው በእንጨት ላይ የተሰቀለ በእግዚአብሔር ዘንድ የተረገመ ነውና ሬሳው በእንጨት ላይ አይደር:: ነገር ግን አምላክህ እግዚአብሔር ርስት አድርጎ የሰጠህን ምድር እንዳታረክስ በእርግጥ በዚያው ቀን ቅበረው:: /ዘዳ 21÷22–23/ የሚል ሕግ ተጽፏል:: ነገር ግን እሥራኤላውያን በድንጋይ በመውገር እንጅ በስቅላት መቅጣትን የጀመሩት ከ267 ዓ.ፍ. በኋላ መሆኑ ታውቋል::

በሮማውያን ሕግ መሠረት በስቅላት የሚቀጣ ሰው:-

- ሀብቱ ይወረሳል
- ልብሱ ይገፈፋል
- በችንካር ይመታል
- የሚሰቀልበትን ይሸከማል
- ሠራ የሚባለው ወንጀል ከራስጌው ይጻፋል::

## ጌታችን ለምን በመስቀል ተሰቀለ?

### 1. ሞትን ይሽር ዘንድ

በአይሁድ ዘንድ በመስቀል ላይ የሚሰቀል ሰው የተረገመ ነበር /ዘዳ.21÷22፤ ገላ 3÷13/ ጌታችንም በአዳም በርሱም ምክንያት በሰው ልጆች ሁሉ /ሮሜ. 5÷12–14/ የመጣውን ሞት /ዘፍ. 2÷17/ ይሽር ዘንድ የአዳምን በደል በደሉ አድርጎ በመስቀል ላይ ሞተ::

### 2. ፍቅሩን ይገልጥ ዘንድ

እግዚአብሔር ከፍጥረት ሁሉ ለይቶና አክብሮ ከፈጣሪ በታች ከፍጡራን በላይ ያለውን ማዕረግ ለሰው ልጅ ሰጥቶት ነበር:: ነገር ግን የሰው ልጅ በመበደሉ ምክንያት ፍጥረታት ከማይገቡበት ሲኦል ወደቀ:: በዚህም ግዕዛን ከሌላቸው እንስሳት እንኳን አነሠ::

እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ያለውን ፍቅር ይገልጽ ዘንድ እንደ ወንጀለኛ ተቈጥሮ ለወንጀለኞችና ለርጉማን በተዘጋጀ ሞት ሞተ:: በዚህም የሰውን ልጅ ከወደቀበት ውድቀት ያነሣው ዘንድ ምን ያህል እንደተዋረደለት አሳየን::

### 3 የጥበበኞችን ጥበብ ከንቱ ያደርግ ዘንድ

እግዚአብሔር ድንቅ ሥራውን የሚሠራው ሰዎች ባልጠበቁትና ባላሰቡት በናቁትና ታናሽ አድርገው በቈጠሩት ነገር ነው:: እሥራኤልን ለማሻገር የኤርትራን ባሕር የከፈለው በሙሴ በትር ነው/ ዘጸ. 14÷21/፤ እሥራኤልን ከነዳፊ እባብ ያዳናቸው በናስ እባብ ነው/ዘኁ.21÷4-9 / ፣ ምሥጢረ ሥጋዌ የተገለጠበትን ልደቱን የፈጸመው በቤተልሔም በረት ነው:: ምሥጢረ ጥምቀትን የመሠረተው በዮርዳኖስ ወንዝ ነው::

ስለሆነም ኃያላን ነን የሚሉ እንደሚያደርጉት ሞትን ድል ያደርገው ዘንድ ሠይፍና ጦር፣ ሠረገላና ወታደር አላስፈለገውም፤ ጠቢባን ነን እንደሚሉትም ምትሐትና ንግርት አላሻውም:: የዲያብሎስን ኃይልና ጥበብ ይሽር ዘንድ ሰው በማይጠብቀው በመስቀል ሞት ይሞት ዘንድ ወደደ:: «እግዚአብሔር የዚህችን ዓለም ጥበብ ሞኝነት እንዲሆን አላደረገምን?» እንዳለ ሐዋርያው::

1ቆሮ. 1÷21.

በዚህ ጥበቡ ኃያልና ጠቢብ ነኝ የሚለው «ጥበብን የተሞላህ ውበትህም የተፈጸመ መደምደሚያ አንተ ነህ» /ሕዝ.28÷12/ ተብሎ የተነገረለት ዲያብሎስ ባላወቀውና ባልጠበቀው መንገድ ድል ይነሣው ዘንድ በመስቀል ሞት ሞተ::

## 4 ትንቢቱ ይፈጸም ዘንድ

እሥራኤል ወደ ከነዓን እየተ ጓዙ በመንገድ ላይ ሳሉ በእግዚአብሔር ላይ በማጉረምረማቸው የተነሣ እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ እባቦችን ሰደደ:: ሕዝቡንም ነደፉ:: በኋላ ግን ተፀፅተው ወደ እግዚአብሔር ቢመለሱ «የናስ እባብ ሥርተህ በዓላማ ላይ ስቀል:: የተነደፈውም ሁሉ ሲያዩት በሕይወት ይኖራል» ሲል እግዚአብሔር አዘዘው:: ያም የናስ እባብ ለእሥራኤል ከመጣው መቅሰፍት ምክንያተ ድኂን ሆነ::/ዘኁ. 21÷1-9/

ይህ ምሳሌ ትንቢት ነው:: የናሱ እባብ ባልበደለው በደል ስለ ሕዝቡ ኃጢአት ተገብቶ እንደተሰቀለ፤ በኋላ ዘመን መድኃኒተ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ ንጹሐ ባሕርይ ሲሆን ባልበደለው በደል ስለ አዳም ልጆች ተገብቶ ለመሰቀሉ:: እሥራኤል በበደላቸው ያመጡት እባብ መርዛም ነበር:: መድኃኒት ሆኖ የተሰቀለው የናስ እባብ ግን ንጹሕ ነው:: አዳም በበደሉ ያመጣው ሞት ሁሉን ነድፎ የሚጥል መርዛም ነበር:: የተሰቀለልን መድኃኔዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ንጹሐ ባሕርይ ነው:: የናሱ እባብ በዓላማ ላይ እንደተሰቀለ ጌታም በመስቀል ላይ ይሰቀላል:: የናሱን እባብ የቻሉ አይተው ያልቻሉ ድምፁን ሰምተው እንደዳኑ፤ ጌታችንንም ዕድል የገጠማቸው ዘመን ያገናኛቸው መልኩን ታምራቱን አይተው፤ የኋላ ዘመን ሰዎች ደግሞ ትምህርቱን ሰምተው ይድናሉ::

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሙሴ በምድረ በዳ የሰቀለው የናስ እባብ የርሱ ምሳሌ መሆኑን ሲያስተምር «ሙሴም በምድረ በዳ የናሱን እባብ እንደሰቀለ እንዲሁ በርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ የሰው ልጅ ይሰቀል ዘንድ ይገባዋል::» /ዮሐ.3÷14/

አማሌቃውያን ከእሥራኤላውያን ጋር ሲዋጉ ሙሴ እጆቹን ሲዘረጋ እሥራኤላውያን ድል ያደርጉ ነበር:: እጆቹንም ባወረደ ጊዜ አማሌቅ ድል ያደርጉ ነበር:: ሙሴ እጆቹን ዘርግቶ መዋል ስለከበደው አሮንና ሖር እጆቹን ደገፉ:: ዘጸ 17÷8-13:: በዚሁም እሥራኤላውያን አማሌቃውያንን አሸነፉ:: ይኸም አማሌቅ የአጋንንት÷ ሙሴ የክርስቶስ÷ የተዘረጉት እጆቹ ደግሞ የመስቀል ምሳሌዎች ናቸው:: ኢየሱስ ክርስቶስ እጆቹን በመስቀል ዘርግቶ በመስቀል አጋንንትን ድል እንደሚያደርግ አመልካች ድርጊት ነበር::

## 5. ዕርቅን ይፈጽም ዘንድ

ሰማያውያንና ምድራዉያን ተጣልተው ሕዝብና አሕዛብ ተለያይተው ይኖሩ ነበር:: ሰማያውያንና ምድራውያንን ያስታርቅ ዘንድ ከምድር ከፍ ብሎ ከሰማይ ዝቅ ብሎ ተሰቀለ:: ይህም በርሱ በኩል ወደ ሰማይ እንገባ ዘንድ መንገድ መከፈቱን ሊያበሥረን ነው:: ሕዝብና አሕዛብ በወንጌል አንድ ይሆኑ ዘንድም እጆቹን ወደ ቀኝና ግራ ዘርግቶ ተሰቀለ:: ሐዋርያው አትናቴዎስ ስለ ዚህ ጉዳይ ሲያስተምር:: «ጌታችን እጆቹን ዘርግቶ ተሰቀለ፤ በአንዱ ሕዝብን በሌላውም አሕዛብን ያቀርብ ዘንድ:: አንድም ያደርጋቸው ዘንድ» ይላል::

## 6. የዲያብሎስን ጥበብ ያፈርስ ዘንድ

ዲያብሎስ አዳምና ሔዋንን በዕፀ ድል ነሥቶ ከገነት አስወጥቷቸው ይኖር ነበር:: ይህን ጥበቡን ያፈርስ ዘንድ ወልደ አብ ወልደ ማርያም ክርስቶስ በእንጨት ላይ ተሰቀለ::

## መሠረተ እምነት በእንተ መስቀል

### 1. በመጀመሪያ ስለ መስቀል ያስተማረው መድኃኔ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እርሱን ስለመከተል ባስተማረባቸው ዐንቀጾች ሁሉ «መስቀል መሸከም» የግድ መሆኑን ተናግሯል::

ማቴ.10÷37:- መስቀሉን የማይዝ በኋላየም የማይከተለኝ ለእኔ ሊሆን አይገባ ውም::

ማቴ16÷24:- እኔን መከተል የሚወድ ራሱን ይካድ፣ መስቀሉንም ተሸክሞ ይከተለኝ:: ማር.8÷34

ከሕፃንነቴ ጀምሮ ሁሉን ጠብቄያለሁ በማለት ለተመጻደቀው ፈሪሳዊ ጌታችን «አንድ ነገር ጐደለህ ሂድ ያለህን ሁሉ ሸጠህ ለድኾች ስጥ፤ በሰማይም መዝገብ ታገኛለህ:: መስቀሉንም ተሸክመህ ና ተከተለኝ አለው::» ማር.10÷21

መድኃኔዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ የርሱ ደቀ መዝሙር ሆኖ እስከ መጨረሻዋ ሕቅታ ድረስ እርሱን ስለመከተል ባስተማረበት ዐንቀጽ ሁሉ መስቀሉን ያነሣበት ምክንያት አለው:: ዓለም የዳነበት፣ ዲያብሎስ የተረታበት በመሆኑ፣ መከራን ሰማዕትነትን የሚገልጽ በመሆኑ፣ ጌታችን ለኛ ሲል ያደረገልንን ውለታ ሁሉ የሚያሳይ በመሆኑ ነው:: በመሆኑም ክርስትና መስቀልን ይዞ መስቀልን እያሰቡ በመስቀል ላይ የሚደረግ ጉዞ ነው::

### 2. የመላእክት የስብከታቸው ማዕከል ነው

ቅዱሳን መላእክት የጌታችንን ትንሣኤና ዕርገት ባበሠሩበት ጊዜ ሁሉ ስለ ጌታችን ሲገልጡ «የተሰቀለው ኢየሱስ» ይሉ ነበር:: /ማቴ. 28÷5/ ይህም ሞትና ዲያብሎስ ድል የተነሡት፣ ገነት የተከፈተችው፣ ዕርቅም የተፈጸመው በመስቀል ላይ በመሆኑ ጌታችንን «የተሰቀለው ኢየሱስ» እያሉ ጠርተውታል::

### 3. የሐዋርያት የስብከታቸው ማዕከል ነው

ሐዋርያትም ከቅዱሳን መላእክት እንደተማሩት ስለ ጌታችን ሲያስተምሩ መስቀሉን እያሰቡ ነበር::

- የሐዋ. 2÷36:- እንግዲህ እናንተ የሰቀላችሁትን ኢየሱስን እግዚአብሔር ጌታም ክርስቶስም እንዳ ደረገው የእሥራኤል ወገን ሁሉ በርግጥ ይወቅ
- 1ቆሮ 1÷23:- እኛ ግን የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካለን:
- 1ቆሮ 2÷2:- በመካከላችሁ ሳለሁ ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀር እርሱም እንደተሰቀለ ሌላ ነገር እንዳላውቅ ቈርጬ ነበር

### 4 በዳግም ምጽዐት የሚታይ የሰው ልጅ ምልክት ነው

ጌታችን በደብረ ዘይት ደቀ መዛሙርቱን ስለ ነገረ ምጽዐቱ ሲያስተምራቸው «በዚያን ጊዜም የሰው ልጅ ምልክት በሰማይ ይታያል»

ብኋቸዋል /ማቴ. 24÷30/:: የሰው ልጅ ምልክት የተባለ «የተሰቀለው ኢየሱስ» ተብሎ የተጠራበት መስቀሉ ነው:: የወጉት የሰቀሉት የፈረዱበት ሁሉ ዋይ ዋይ» የሚሉትም ይህ ታላቅ ምልክት በሰማይ በተገለጠ ጊዜ ነው:: /ማቴ.24÷30/::

### 5. መመኪያ ነው

«ነገር ግን ዓለም ለኔ የተሰቀለበት እኔም ለዓለም የተሰቀልኩበት ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል በቀር ሌላ ትምክህት ከኔ ይራቅ» ገላ.6÷14/:: በማለት ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንደተናገረው ዲያብሎስ ድል የተነሣበት እኛም የቀደመ ክብራችንን ያገኘንበት በመሆኑ መስቀል ትምክህታችን ነው::

### 6. ኃይል ነው

መስቀል ጥል የተገደለበት ነው/ኤፌ.2÷16/:: ዲያቢሎስም ከመንገድ የተወገደበት ነው /ቆላ 2÷14/:: በመሆኑም ሰይጣን ይፈራዋል:: ተሸንፎበታልና:: መስቀል ኃይል አለው:: ተአምራትን ያደርጋልና:: የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ ልብሱ፤ የሐዋርያው የቅዱስ ጴጥሮስ ጥላው ይፈውሱ፣ አጋንንት ያስወጡና አጋንንት ያርቁ ነበር:: ልብስ ወይም ጥላ በራሳቸው ኃይል ኑሮአቸው ሳይሆን የነፍሳቸው ቅድስና ለሥጋቸው፣ ለልብሳቸው፣ ለጥላቸው ተርፎ ነው:: /የሐዋ.5÷15፤ የሐዋ.19÷11/ መድኃኒተ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስም በደሙ ስለዋጀው መስቀል ኃይል ነው:: ለዚህ ነው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «የመስቀሉ ቃል ለሚጠፋት ሞኝነት ለእኛ ለምንድን ግን የእግዚአብሔር ኃይል ነው» ያለው /1ቆሮ. 1÷18/

### 7.. ትእምርት ነው

ከቀስት ፊት ያመልጡ ዘንድ ለሚፈሩህ ምልክትን ሰጠሃቸው መዝ. 59÷4 በማለት ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት አስቀድሞ እንደ ተናገረ ዲያብሎስ ከወረወረው የሞት ፍላጻ ያመለጥንበት ዛሬም ከሚወረወረው የኃጢአት ቀስት የምንድንበት መስቀል ምልክታችን ዓርማችን ነው::

### 8. ምድራዊ ዙፋን ነው

ሰማያዊ አምላክ እግዚአብሔር ወልድ ሥጋውን የቈረሰበት ደሙን ያፈሰሰበት፣ ገነትን የከፈተበት፣ በዲያብሎስ ላይ የፈረደበት፣ አዳምን ከሞት ዕዳ ያዳነበት፣ ነፍስ ወደ መንግሥተ እግዚአብሔር ትጓዝ ዘንድ መንገዱን የከፈተበት ዙፋኑ ነው::

# ክብረ መስቀል በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን

በሰውና በእግዚአብሔር መካከል የነበረው የጠብ ግድግዳ የፈረሰበትና ሰው የተወሰደበት ሰላም ተመልሶለት ከፈጣሪው ጋር የታረቀበት ነው:: «እርሱ ሰላማችን ነውና÷ ሁለቱን ያዋሐደ በአዋጅ የተነገሩትንም የትእዛዛትን ሕግ ሽሮ በመካከል ያለውን የጥል ግድግዳን በሥጋው ያፈረሰ ይህም ከሁለታችን አንድን አዲስን ሰው በራሱ ይፈጥር ዘንድ ሰላምንም ያደርግ ዘንድ ጥልንም በመስቀሉ ገድሎ በእርሱ ሁለታቸውን በአንድ አካል ከእግዚአብሔር ጋር ያስታርቅ ዘንድ ነው::» ኤፌ 2÷14–17::

መስቀል ትዕግሥትንና እስከ መጨረሻው መጽናትን ያስተምረናል:: ጌታችን ወደ መስቀል ባደረገው ጉዞ አይሁድ ብዙ መከራ አድርሰውበታል÷ ሰድበውታል÷ ርኩስ ምራቃቸውን ተፍተውበታል÷ በመሬት ላይ እያዳፉ ጥለውታል በመጨረሻም ካለ ምንም ርኅራኄ ሰቅለውታል:: የሚያሳዝነው ሰቅለውት እያለ «ተጠማሁ» ሲላቸው እንኳ መሞቱ አይቀርም ብለው ትንሽ እንኳ ኃዘኔታ ሳይታይባቸው መራራ ሐሞትንና ኮምጣጤን እንዲጠጣ ሰጥተውታል:: በዚህ ሁሉ መከራ ግን ምንም አላላቸውም÷አልተቆጣቸውም:: ይህም ለእኛ ትምህርት ነው:: «የተጠራችሁለት ለዚህ ነውና÷ ክርስቶስ ደግሞ ፍለጋውን እንድትከተሉ ምሳሌ ትቶላችሁ- ስለ እናንተ መከራን ተቀብሎአልና:: እርሱም ኃጢአት አላደረገም÷ ተንኰልም በአፉ አልተገኘበትም፤ ሲሰድቡት መልሶ አልተሳደበም ÷ መከራንም ሲቀበል አልዛተም» 1ጴጥ 2÷21–23::

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱሳዊትና ትውፊታዊት እንደ መሆንዋ መጠን ከላይ የተገለጡትን መሠረት በማድረግ በልዩ ልዩ መንገድ መስቀልን ታከብረዋለች:: ልጆቿንም የመስቀሉን በረከት እንዲያገኙ ታደርጋለች::

### 1 በመሳለም

መስቀልን መሳም ወይም መሳለም ከመስቀሉ በረከት መሳተፍና ለመስቀሉ ያለንን ፍቅርም መግለጫ ነው::/መኃ.1÷2/ መስቀሉን መውደድ ማለትም በመስቀሉ ላይ የሞተውን መድኃኔዓለም ኢየሱስ ክርስቶስን መውደድ ማለት ነው::

### 2.መባረክ

መስቀል ኃይል አለው:: ዲያብሎስ ድል የተነሣበት፣ የሲዖል ደጅ ተዘግቶ የገነት ደጅ የተከፈተበት፣ ሥጋው ተቈርሶ ደሙ የፈሰሰበት በመሆኑ ሌሎችን ነገሮች ሁሉ ይባርካል::

አስቀድሞ በሕገ ልቡና አባታችን ቅዱስ ያዕቆብ ሁለቱን የዮሴፍ ልጆች ኤፍሬምንና ምናሴን ሲባርክ እጁን በመስቀለኛ አመሳቅሎ ነበር /ዘፍ. 48÷12–14 ይህም የኋላው ዘመን ተገልጦለት በመስቀል መባረኩ ነው::

ዛሬ በዘመነ ሐዲስ የምንገኝ ክርስቲያኖችም ሁሉንም ነገር በመስቀሉ እንባርካለን::

### 3. ማማተብ

አመልካች ጣታችንን ዘርግተን መሐል ጣታችንን በማጠፍ መስ ቀልኛ ሠርተን ፊታችንንና መላ ሰው ነታችንን እናማትባለን:: ጣት የኃይለ እግዚአብሔር ምሳሌ ነው /በማቴ. 12÷28 እኔ በእግዚአብሔር መንፈስ ያለውን በሉቃ.11÷20 እኔ በእግዚአብሔር ጣት ብሎታል/ የእግ ዚአብሔር መንፈስ ሲል የእግዚአብሔ ር ኃይል ማለቱ ነው:: እኛም በመ ስቀሉ ስናማትብ በኃይለ እግዚአብሔር ተማምነን ጠላታችን ዲያብሎስን መካዳችን ማሳፈራችንም ነው::

### 4. በአንገት ማሠር

መስቀልን በአንገት ማሠር ለዚህ ላመንኩት እምነት፣ ለተሸከምኩትም አደራ አንገቴን እሰጥለታለሁ ማለት ነው:: በሌላም በኩል አደራን የመጠበቅ ምሳሌ ነው:: ጠቢቡ ሰሎሞን «ልጄ ሆይ የአባትህን ትእዛዝ ጠብቅ፣ የእናትህንም ሕግ አትተው:: ሁልጊዜ በልብህ አኑረው፤ በአንገትህም እሠረው» /ምሳ. 6÷ 20 – 21 በማለት የተናገረውም ይኼንኑ ለማመልከት ነው::

### 5. በመመስከር

ለክርስቲያኖች በምልክትነት /በዓርማነት/ የተሰጡን ሁለት ነገሮች አሉ:: መስቀልና እመቤታችን /መዝ.59÷4፤ ኢሳ.7÷13/ በመሆኑም መስቀል የምንኰራበት የነፃነት ዓርማችን በመሆኑ በግንባራችን፣ በልብሳችን፣በቤታችን አናት፣ በቤተክርስቲያን ጉልላት፣ ወዘተ. በክብር እናስቀምጠዋለን:: በዚህም የመስቀሉን ክብር፣ አዳኝነትና መመኪያነት እንመሰክራለን::

### 6. በዓሉን በማክበር

በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በድምቀት ከሚከበሩት በዓላት አንዱ የመስቀል በዓል ነው:: በቤተ ክርስቲያን የበዓላት ቀኖና መሠረት የመስቀሉ በዓል ሁለት ጊዜ ይከበራል:: የመጀመሪያው በንግሥት ዕሌኒ /255–335ዓ.ም/ ለ200 ዓመታት በአይሁድ ከተቀበረበት ይወጣ ዘንድ ቁፋሮ የተጀመረበት መስከረም 17 ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ተቆፍሮ የወጣበትና በፋርሶች ከተማረከ በኋላ በሮሙ ንጉሥ በሕርቃል በ628 ዓ.ም. ወደ ኢየሩሳሌም የተመለሰበት መጋቢት 10 ቀን ናቸው::

እግዚአብሔር አምላካችን የመስቀሉ ፍቅር ይገለጥልን ዘንድ ማስተዋልን ይስጠን::

አሜን::

# አለ ወይስ የለም?

*ቤተክርስቲያናችን ብዙ ሰማዕታት እንዳሏት ይታወቃል:: ለመሆኑ ሰ ማዕትነት ምንድን ነው? በአሁኑ ጊዜስ አለ ወይስ የለም?*

*ሥርጉት ከአሶሳ*

<u>መልስ:-</u>

ሰማዕት ማለት ምስክር ማለት ነው:: ስለቀጥተኛይቱ ሃይማኖት ሲ ያስተምሩ በከሃድያን በኣላውያን እጅ የተገደሉ፣ በእግዚአብሔር ስም /እግዚ አብሔርን አንክድም ከፈቃዱና ከሕጉ ውጪ የሆነ ማንኛውንም ድርጊት አንፈጽምም በማለታቸው/ የተለያዩ መከራዎችን የተቀበሉ ሰዎች ሰማዕታት ይባላሉ::

በቅድስት ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕ ዶ ቤተ ክርስቲያናችን ስለእግዚአብሔ ር መስክረው ከከሃድያን፣ ከመናፍቃን የሚደርስባቸውን መከራ ሁሉ ታግሰው በክብር ያረፉ በሕያው ሥራቸው በዘ መኑ ሁሉ ለሚነሣው ትውልድ አስተ ማሪ ምሳሌ የሆኑ አያሌ ሰማዕታት አሉ:: ሠለስቱ ደቂቅ፣ ቅዱስ እስጢ ፋኖስ፣ ቅዱስ ጊዮርጊስ፣ ቅድስት ዶሚአና፣ ቅድስት ኢየሉጣ፣ ቅድስት አርሴማ ለአብነት ያህል የሚጠቀሱ ሰ ማዕታት ናቸው::

ዘመናት በተፈራረቁ ቁጥር ምእመናን ሰማዕታት የሚሆኑበት የመ ከራው ዓይነት ይለያያል:: በብሉይ የነ በረው ሰማዕትነት በሐዋርያት ዘመን ከነበረው፣ በሐዋርያት የነበረው ደግሞ በዘመናችን ካለው ይለያል:: ለእሳት የተጣሉ፣ ለአናብስት የተሰጡ በመንኰ ራኩር የተፈጩ፣ በሰይፍ የተሰየፉ... ሰ ማዕታት አሉ:: ከዚህም በተጨማሪ «ከሕገ እግዚአብሔር ውጪ የሆነውን ድርጊት አንሠራም በማለታቸው ከሥ ራቸው የተባረሩ፣ ከቃልቻ ከጠንቋይ ቤት ሄደን አንሰግድም፣ ሊሰገድለት የሚገባው እግዚአብሔር ከልክሎናል» በማለታቸው ከማኅበራዊ ኑሮ የተገ ለሉ፣ ሀብት ንብረታቸው ተዘርፎ ሀገር ጥለው እንዲሰደዱ የተደረጉ /የሚ ደረጉ/ አያሌ ሰማዕታት አሉ:: እነዚህ ሁሉ በተለያየ ሁኔታ ሰማዕትነትን ቢ ቀበሉም ዋጋቸው አንድ ነው:: ገነት መንግሥተ ሰማያትን መውረስ::

በክርስትና እምነት ጸንተን ሕገ እግዚአብሔርን ለመጠበቅ ከፈቃደ ሥጋችን ከማያምኑ ሰዎች ድርጊት /መንገድ/ ለመራቅ በተነሣን ጊዜ ሁሉ ሰማዕትነት አለ:: ንጉሥ ዳዊት ውኃ ጥም ጠንቶበት ሳለ ወታደሮቹ የፍልስ ጥኤማውያን ጭፍሮች ከከበቧት ከቤተ ልሔም ምንጭ ተዋግተው ያመጡለትን ውኃ «በነፍሳቸው ደፍረው የሄዱ ሰዎች ደም አይደለምን?» በማለት አልጠ ጣም ብሎ ጥሙን መታገሡ ከሰማዕ ትነት እንደተቆጠረለት ቤተክ ርስ ቲያናችን ታስተምረናለች:: 2ሳሙ 23÷13–17፣ ውዳሴ ማርያም ዘሰ ሉስ:: እንደዚሁ ሁሉ በሥጋ የሚያ ስፈልጋቸውን፣ የሚጠቅማቸ ውን ነገር ስለ ወንጌል ስለመንግሥተ ሰ ማያት ሲሉ የተው በዚህም የእግዚ አብሔር መሆናቸውን የገለጡ ሰማዕ ታት ናቸው:: በድርቅ፣ በኀርፍ ማጥለቅለቅ፣ በመሬት መንቀጥቀጥ፣ በጦርነት... በተለያዩ ሰው ሠራሽና ተፈጥሮአዊ ችግሮች ሲቸገሩ ለረሃብ በተጋለጡበት ወቅት፣ በደዌ ዳኛ በአልጋ ቁራኛ ተይዘው በተሰቃዩበት ጊዜ እምነታችሁን ክዱችሁ /ለው ጡችሁ/ ወደኛ ብትመጡ እንረዳ ችኋለን» በሚለው የማባበያ ቃል ሳይታለሉ በእምነታቸው ጸንተው ችግሩን፣ ረሃቡን፣ በሽታውን የታገሉ /የሚታገሉ/ ሰማዕታት ናቸው::

ዓለማችን የተለያየ እምነት፣ አመለካከት፣ ባሕል ያላቸው ሰዎች ያሉባት ናት:: በውሎአችን በሥራ ችን ከነዚህ ሁሉ ጋር እንገናኛለን:: እነዚህ በዙሪያችን ያሉ ሰዎች በተለ ያየ መልኩ ፈቃዳቸውን እንድንፈጽ ምላቸው ሊፈልጉ ሲጠናም ሊያስገ ድዱን ይችላሉ:: በዚህን ወቅት በሕ ግ /የእግዚአብሔር ሕግ፣ የመንግሥ ት ሕግ/ ከተፈቀደው ውጪ አንሆ ንም በማለት ዳኛው ፍርድ ሳያጣ ምም፣ ጉቦ ሳይቀበል በመቅረቱ፣ ፀሐፊው የሌለ ያልተደረገ ነገር አል ጽፍም ያለውንም/የሚመለከተው ን/ አልሸሽግም፣ ሰባኪው እውነቱን እው ነት ሐሰቱን ሐሰት በማለቱ ከሌሎች መከራን ቢቀበሉ የሰማዕትነት ዋጋ ቸው በሰማይ ታላቅ ነው::

በአጠቃላይ ሰማዕትነት እን ድንኖርበት በቃለ እግዚአብሔር ከተ ፈቀደልን፣ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቃል አስተምሮ በግብር አርአያ ከሆነን፣ ቀደምት ሰ ማዕታት ፈጣሪያችንን ካገለገሉብ ት ሕይወት ውጪ አንሆንም በማለ ታችን የምንቀበለው መከራ ነው:: ይህም ከረሃብ እስከሞት ያለውን መከራ ሁሉ የሚያጠቃልል ነው:: /ዕብ ራ 2÷10/ ሰማዕትነት /የእውነት ምሥክር መሆን/ ለተወሰኑ ሰዎች ብቻ የተወሰነ ሳይሆን በክርስቶስ የባሕርይ አምላክነት ለሚያምኑ ሁሉ የተፈቀደ የውዴታ ግዴታ ነው:: ይህንንም ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «...በሰው ፊት ለሚመሰክርልኝ ሁሉ እኔ ደግሞ በሰ ማያት ባለው በአባቴ ፊት እመሰክ ርለታለሁ፤ በሰው ፊትም የሚክደኝን ሁሉ እኔ ደግሞ በሰማያት ባለው በአባቴ ፊት እክድዋለሁ» በማለት ገልጦታል:: ይህም የክርስቶስ ምስ ክር የሚሆነው በጊዜውም ሆነ አለጊ ዜው በቃላችን በምናስተምረው ትም ህርት፣ በሥራችን በምንፈጽመው ሥ ራ እየታገስን ለእውነት ስንል በም ንቀበለው መከራ ይሆናል:: ማቴ 10÷32–33::

ሰማዕትነት ከዚህ በላይ ለመግለጥ እንደሞከርነው በእምነት ጎዳና የሚፈጸም ተጋድሎ ቢሆንም በስሜት የሚቀሰቅሱት /የሚፈጥሩት/ ነገር አይደለም:: ለራስ ሕይወት ጽድቅ ለማግኘት /የሰማዕትነትን አክ ሊል ለመቀዳጀት/ ሲባል የማያም ኑትንም ሆነ መናፍቃንን፣ ባለሥል ጣናትንም በመስደብ የሚገኝ የሰማዕ ትነት ዋጋ የለም:: በማናቸውም አመለካከት ወይም ግብር ከወንጌል መንገድ የወጡ ቢኖሩ እንኳን በፍ ቅር በትኅትና በጾም በጸሎት እየበ ረቱ እግዚአብሔርን አጋዥ አድርጎ ወደቀናው መንገድ መመለስ፤ የማ ያምኑ፣ ለጣዖት የሚሰግዱ አላው ያን ቤተ ክርስቲያን እንድትዘጋ እን ድትሰደድ፣ የእግዚአብሔር ሕዝብ ከፈጣሪው ወደ ሌሎች አማልክት ዘወር እንዲል ሲያስገድዱት እንደ ቀደምት ሰማዕታት መቃወም ይገ ባል እንጂ ገና ለገና ሰዎቹ ስለማያ ምኑ ብቻ ሕዝብን ማወክ፣ መገዘት ምእመናንን ለበለጠ ችግር መዳረግና በእምነት ያልበረቱትም ወደኋላ እን ዲሉ ማድረግ ነው::

አንድ ምእመን በሰማዕትነት ተጋድሎውን ለመጨረስ ከመፈለጉ በፊት እምነቱን አስተካክሎ ንስሐ ገብቶ ሥጋ ወደሙ እየተቀበለ በተለ ያዩ የጽድቅ ሥራዎች / በጾምና በጸ ሎት፣ በስግደት ከሥጋ ፈቃዳት በመጠበቅ/ ኀልምሶ መገኘት ይጠበቅበ ታል:: በመሆኑም እኅታችን ሥርጉት ሰማዕትነት የነበረ ያለና እስከ ዕለተ ምጽዓት የሚኖር ቢሆንም በሰላሙ ሰዓ ት ለጽድቅ ሥራዎች ትጉኅ መሆን ተቀዳሚ ነገር በመሆኑ ለዚህ ትኩረት ልትሰጪው ይገባል:: በተረፈ እኅታ ችንም ሆንሽ ሌሎች አንባብያን በዚህ ዙሪያ ወደፊት ሰፋ ያለ ጽሑፍ ለ ማቅረብ እንደምንሞክር እንገልጻለ ን::እግዚአብሔር ሀገራችንንና ቤተ ክርስቲያናችንን ይጠብቅልን::

# ዝንጉው ምሥጢረኛ

በ1993 ዓ.ም. በዝግጅት ክፍሉ በተደረገው የአጭር ልቦለድ ውድድር 1ኛ የወጣ

*ትዕግሥት አበበ*
*ደብረ ብርሃን ቅድስት ሥላሴ ሰንበት ት/ቤት*

«... ነቢይ በሀገሩ አይከብርም...» የሚለው ቃል ዛሬም እሳቸውን ባስታወስኩ ቁጥር ትዝ ይለኛል::

ረጅም ሪዛቸውን እያፍተለተሉ ያለፈውን ሲያስቃኙ አቤት ጸጋ ወይ ስጦታ ያሰኛል:: ላያቸው ሰው ደልቷቸው የሚኖሩ ችግር የሚባለውን ነገር በጭራሽ የሚያውቁት አይመስሉም:: ውስጣቸውን ግን የቀረባቸው ሰውና ፈጣሪ ያውቁታል::

የተዋወቅነው ባልጠበቅሁት ሰዓት ነበር:: ለምን እንደሆነ የሚያውቅ ባይኖርም ሰዎችን መቅረብም ሆነ ማወቅ እንደማይሹ ይነገራል:: «ለምን» ቢባል ግን መልሱን የሚያውቁት እሳቸው ብቻ ናቸው:: ከሚኖሩባት ደሳሳ ጐጆ ገብቶ የሚጠይቃቸው እምብዛም ባይኖርም በግቢው ካሉት የቆሎ ተማሪዎች ጋር የቀረበ ግንኙነት አላቸው:: በተለይ ቀን «በእንተ ስማ ለማርያም» ሲል ውሎ መሸትሸት ሲል ደግሞ ከእግራቸው ሥር ከማይጠፋው ከኒቆዲሞስ ጋር የአባትና የልጅ ያህል ምሥጢረኞች መሆናቸውን ሰምቻለሁ::

✡ ✡ ✡

ፀሐይ በመሐል እናት ትይዩ ሆና ትንተገተጋለች:: ሙቀቱ ፋታ የሚሰጥ ዓይነት አይደለም:: ገና ከስብሰባ መውጣቴ ቢሆንም በቀጥታ ወደ ቤቴ አልገባሁም:: ራሴን ክፉኛ ይወቅረኛል:: የሠማሁትን ሁሉ ማመን አልቻልኩም:: «ለካስ ደመወዝ የምንበላው ይህን ያህል ጥፋት መኖሩን እንኳ ሳናውቅ ነው» እጅግ በጣም አዘንኩ:: በስብሰባው ላይ በተነበበው ሪፖርት በዓመቱ የተሰረቁና በባዕድ ሀገር የተሸጡ የቅርሳ ቅርስ ቁጥር ብዛት ከኀሊናዬ ሊጠፋልኝ አልቻለም:: «ምን ይደረጋል÷ የፈሰሰ ውኃ አይታፈስ» ያሉት የአንደኛው ተሰብሳቢ አባላችን አስተያየት እየደጋገመ በአእምሮዬ ያቃጭልብኛል:: «በራቸውን አይዘጉ ሰው ሌባ ይላሉ» አለ ያገሬ ሰው:: «ከማናውቀው እየተዛመድን ብር ዓይናችንን ጠፍሮ አሥሮን ባዶአችንን ልንቀር? የአባቶቻችን አምላክ አንተ ታውቃለህ» ብቻዬን እያወራሁ ሳላስበው ከጓደኛዬ ከያሬድ ቤት መድረሴን ያወቅሁት ከበሩ ፊት ለፊት ቆሞ ሳየው ነው::

«ደግሞ ዛሬ ምን ተሰረቀ? ገና በሩቅ ያወራጭሀል እኮ» አለኝ ያሬድ:: ብቻዬን ሳወራ እንደመጣሁ በሩቅ ይመለከተኝ ኖሯል:: «ለጊዜው ምንም ንብረት አልተሰረቀም:: ግና እኛንም ሊሰርቁን እያሰቡ ነው አሉ» እየተሳሳቅን ወደ ቤት ገባን::

ዛሬ ወደሱ ለምን እንደመጣሁ ያሬድ የሚያውቀው ጉዳይ የለም:: ምን እሱ ብቻ እኔም ጠንቅቄ አላውቀውም፣ ብቻ ከውስጤ የሚገነፍል ስሜት «በል በል...» ይለኛል::

«እሺ ክብሮሜ ሰውነትህ በጣም የተቀያየረ ይመስላል:: ከመ/ቤት አልተስ ማማህም እንዴ?»

«ኧረ በፍፁም:: በጣም ሰላም ነኝ::...እ... ብቻ ትንሽ ከራሴ ጋር ተጋጨሁ» አልኩት አጠገቤ ያለውን የቅርሳ ቅርስ ጥበቃ ድርጅት ያወጣውን መጽሐፍ እያገላበጥኩ::

«ችግራችን ይኸው ነው፤ ላንወጣው ከራሳችን ጋር ትግል እንጀምርና ማጣፊያው ሲያጥረን መጨነቅ እንጀምራለን:: ታዲያ ይሄ ሁሉ ተስፋችንን በአምላካችን አለማድረግ ይመስለኛል:: ሰው ስለ ትዳር፣ ስለ ትምህርት፣ስለ ቤተሰብ፣ስለተለያየ ነገር ይጨነቃል:: ታዲያ ሁሉም ነገር በልክና በመጠን ሲሆን እግዚአብሔርም የተቸገሩትን ሀሳባቸውን ያቀላል:: አንተን ደግሞ ሊያስተምሩህና ሊነግሩ የሚገባህ አይመስለኝም:: እና...... ከልክ ያለፈ ጭንቀት አያስፈልግህም» አለኝ እግሮቹን አነባብሮ በፍፁም ወንድማዊ ፍቅር እየተመለከተኝ::

«ያሬድ እንደዚያ አይደለም፤ ስለ ትዳርም ሆነ ስለሌላ ነገር አላስብም፤ ባይገርምህ ስለራሴም አልጨነቅም ግን........»

«ግን ምን? ምን የተለየ ነገር መጣ?»

«ይኸውልህ ዛሬ በመሥሪያ ቤታችን አጠቃላይ ስብሰባ ነበር:: »

«እና..... ምን ተገመገምክ?» ያሬድ የበለጠ ቀረበኝ

«አልተገመገምኩም ግን ትውልዱ ተገመገመ

«እና.....?»

«እናማ መውደቃችንን ልነግርህ ወደ አንተ እግሮቼን አቀናሁ::» ያሬድ የበለጠ እንቆቅልሽ ሆንኩበት:: «ክብሮም ነገርህ ሁሉ እንግዳ ሆነብኝ:: እ......ቆይ እስቲ ለማንኛውም ሻይ ይፈላ» ብሎኝ ወደ ውስጥ ገባ::

አብሮኝ እንደሚጓዝ እርግጠኛ ብሆንም ችግሩ ግን እሱንም ይመለከተዋልና በመጀመሪያ በዚህ ዙሪያ መነጋገር እንዳለብን ራሴን አሳመንኩት:: ያሬድ ተመልሶ ከአጠገቤ ተቀመጠ::

«የዛሬውን ስብሰባ ፍሬ ነገር አንተም ማወቅ ያለብህ ይመስለኛል.... ይኸው... እንካ» የያዝኩትን የተዘረፉና ለባዕዳን የተሸጡ ቅርሶች የሚያመለክት ዝርዝር የያዘውን መጽሐፍ ሰጠሁት:: ያሬድ በአትኩሮት ተመለከታቸው፤ ግን ምንም አዲስ ነገር የተመለከተ አይመስልም::

«ታዲያ ይሄ ምን ያስደንቃል? የቅርስ መሸጥና መዘረፍ የታያችሁ ተዘርፎ ሊያልቅ ሲቃረብ ነው'ዴ? ምነው? አልነጋባችሁም!»ነገሩን አቀለለብኝ:: «አዝናለሁ ያሬድ ምላሽህ ይህ እንደሚሆን አልገመትኩም ነበር:: የቅርሶቻችን እንክብክቤ ማጣትና መጥፋት በቀላሉ መመልከታችን ዛሬ ባዶ እጃችንን እንድንቀር አድርጐናል:: አባቶቻችን ታሪክ አስቀምጠዋል:: እኛ ደግሞ ታሪክ አጥፍተናል:: እንኳን አዲስ ቅርስ ለትውልድ ልናስረክብ ያለውን ጠብቀን ልናቆይ አልቻልንም፤ ታዲያ ተጠያቂው ማንነው?»

«ባሕልና ቱሪዝም ቢሮ ወይም ቤተ ክህነት!» ያሬድ ጥያቄዬን በፍጥነት መለሰልኝ:: ምላሹ ግን እኔንም አስደነገጠኝ «ለምን? እኮ ለምን? ቅርስ ተመዝብሮ ለባዕዳን ተቸርችሮ ሲያልቅ፤ ለሚቀጥለው ትውልድ ቅርስ እንዳናስቀርላችሁ ባቱማና ቤተ ክህነት አልተንከባከቡምና ተመዝብሮ አለቀ:: ብለን የውሸት የማይታመን ወሬ ብንተውለት የሚቀበለን ትውልድ ይመጣ ይመስልሃል:: የዚህ ትውልድ አባላት እንደ እኔና አንተ ዓይነቶች ሁሉ ቅርሶችን ካልጠበቅን ምኑ ላይ ነው የኛ አደራ ተረካቢነት?» ስብሰባው ላይ ያልነበረኝ ቁጣ ገነፈለ:: ስሜቴን መቆጣጠር አቃተኝ፤ እን ባዬም መጣ:: እልህ ውስጤን ሲቆጣቀጠኝ ተሰማኝ:: ያሬድ ተጠያቂነትን የጣለባቸው ቦታዎች በእጅጉ አስገረሙኝ:: በአንድ ዓመት ይህን ያህል ቅርስ ከጠፋ እስከዛሬማ ምን ያህሉ ባክኖዋል?

«ነገሩ እኮ እኔ አንተን ብቻ የሚመለከት አይመስለኝም:: ምናልባትም አንተ ከሥራህ ጋር ስለሚዛመድ.....»

«ኖ.....ኖ ያሬድ ከሥራዬ ጋር ስለሚዛመድ አይደለም:: ይህን ያህል ቅርስ ባክኖ እኛ ደሞዝ ማግኘታችንን ኀሊናዬ አምኖ መቀበሉን እየተቸገርኩ ነው:: የሆነው ሆኖ ከዚህ በኋላ ለሚኖረኝ ሥራ ከጐኔ እንደምትሆን እተማመናለሁ» ያሬድን በአትኩሮት ተመለከትኩ:: መልስ አልሰጠኝም:: እሱም እንደእኔ በሀሳብ ተጠምዷል::

ያሬድ የሚያሳድጋት ታናሽ እንቱ የተፈላውን ሻይ ከዳቦ ጋር አቅርባልን ተመለሰች::

«ክብሮም በመናገሬ እንደ ማትቀየም እርግጠኛ ነኝ ግን ሀሳብህ በጅምር እንዳይቀር እሰጋለሁ»

«ቃል ለራሴ ገብቻለሁ:: ያሬድ የአቅሜን ሁሉ ለማድረግ ቆርጬአለሁ በዛሬው ስብሰባ ብዙ ውይይት ከተደረገ በኋላ በመጀመሪያ «አካባቢያችን ይፈተሽ» በሚለው ሃሳብ ተስማምተን የገጠሩን አብያተ ክርስቲያናት ቅርስ ምዝገባ ለማካሔድ ያሉት አብያተ ክርስቲያን ተቆጥረው በእጣ ተከፋፍለናል::»

«በጣም ጥሩ» አለ:: የደረሱኝን ቦታዎች የያዝኩበትን ወረቀት አሳየሁት:: ቦታዎቹ ገጠራማና ውጣ ውረድ የበዛባቸው ቢሆኑም አብረን ልንጓዝ ወስነን ከመሔዳችን በፊት ቅደም ተከተል አስያዝናቸው::

የመጀመሪያውን ጉዞ ወደ እቴጌ ማርያም ለማድረግና አድረን አስቀድሰን ለመመለስ ተስማማን::

«ሪፖርቱን በቅርብ ቀን እንድናጠናቅቅ ተነግሮናል» ብዬው ከያሬድ ጋር ተሰነባብተን ስወጣ ጊዜው መሽቷል:: ሳላስበው መቆየቴ እየገረመኝና ከያሬድ ጋር ያደረግሁት ግልጽ ውይይት ልቤን ደስታ እየሰጠው ቤት ከመግባቴ በፊት የሥራ መጀመሪያም መጨረሻም ባለ ቤቱ እግዚአብሔር ነውና ወደ ቤተ ክርስቲያን አቀናሁ::

✡ ✡ ✡

ቀኑ ደስ የሚል ነው:: ፀሐይዋ እንደ ሰሞኑ አልጋለችም:: በመሐል ሸው እያለ ያጀባት ነፋስ ጥሩ ስሜትን ይሰጣል:: በየሜዳው ያሉ ከብቶችና ሕጻናት ቡረቃ...ከብልየት ያድሳል::: ለምለሙ ሜዳ ለጥ ብሎ ሲታይ ለፈጠረው አምላክ ምስጋና ሊያቀርብ እራሱን ዝቅ ያደረገ ይመስላል:: ሰዓቱ 8:20 ይላል:: እኔና ያሬድ እጅ ለእጅ ተያይዘን «አድርገህልኛልና በቸርነትህ» የምትለዋን መዝሙር እያዜምን ጉዞአችንን ተያይዘነዋል::

ቦታው አዲስ እንደማይሆንብኝ አውቃለሁ:: ግንቦት 21 ለእመቤታችን በዓለ ክብር ከሌሎች ወንድሞችና እንቶቼ ጋር መጥቼ አክብሬያለሁ:: ቦታው ትንሽ ዳገት ይብዛው እንጂ ብዙም ርቀት የለውም:: ቀኑ ቅዳሜ በመሆኑ ከገበያ ተመላሹ ከጀርባችን አጅቦናል:: እኛም 'ነጠቅ' እያልን ስለምንራመድ ሜዳውን ወደ ማገባደዱ ተዳርሰናል::

ሜዳውን ጨርሰን ወደ ዳገቱ ዘለቅን:: ዞር ብዬ ስመለከት የመጣንበት ሜዳ እንደ ቀድሞው ለጥ ብሏል:: በየመንገዱ ላይ ገበያተኞች ቁጥራቸው ይቀንስ እንጂ አልፎ አልፎ ይታያሉ::

ያሬድ ላቡ በፊቱ ላይ ችፍ....ፍ ብሎ ይታያል:: «ቦታው እጅግ በጣም መንፈስን ያድሳል» አለኝ ራቅ ብሎ ካገኘው የቋጥኝ ድንጋይ ላይ እየተቀመጠ ::

«ልበ አምላክ ዳዊትስ «እግዚአብሔር በለመለመ መስክ ያሳድረኛል» ያለው ይህን ሲያመሠጥር ሳይሆን ይቀራል ብለህ ነው» ብዬው እኔም ከአጠገቡ ሂጄ አረፍ አልኩ::

«ክብሮሜ...... እንዲህ ያሉ ቦታዎችን ለሕዝብ ማስተዋወቅ የሚቻለው እንዴት ነው?»

«ቀላል ነው ያሬድ ከዚህ በኋላ ለተተኪው ትውልድ ያለው ሥራችን ቅርሶችን ለቅርስ ተረካቢዎች ማሳየት ይሆናል:: በተለያዩ ቦታዎች በት/ቤት፣ በመንፈሳዊ ማኅበር ጉዞዎች እና በየዓውደ ምሕረት ፕሮግራሞች ላይ እንዲሁም ለቅርስ ጥበቃ ማሳወቅ ሁሉም የራሱንም አስተዋፅኦ ማድረግ እንዳለበት በማስገንዘብ የበኩላችንን ተሳትፎ ከማድረግ አንቆጠብም» አልኩት::

የሜዳውን ርዝመት፣ የአፀዱን አበቃቀልና የቦታውን አቀማመጥ እየተመለከትን ሳናስበው ሰዓቱ ወደ መምሸቱ ተቃርቧል:: ሰዓቴን ስመለከተው 11:40 ደቂቃ ይላል:: በጊዜው ገብተን ለነገ የሚያስፈልገንን ሁሉ ማሟላት እንዳለብን ተነጋግረን ዳገቱን ተደጋግፈን መውጣቱን ተያያዝነው::

የቤተክርስቲያኑ ግቢ ጸጥ ብሏል÷ ምንም የሚንቀሳቀስ ነገር የለም:: አልፎ አልፎ ከየአቅጣጫው የሚሰማው የተማሪዎች ዜማና የአዕዋፍ ዝማሬ ተደምሮ ልዩ ኅብረት ፈጥሯል:: ከውጭው በር ተሳልመን ወደ ውስጥ ዘለቅን:: የያዝነውን አነስተኛ የጉዞ ሻንጣ ወደ አንድ ጥግ አሳርፈን ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ተጠጋን:: ጸሎታችንን ጨርሰን ተመልሰን ከእቃችን አጠገብ አረፍ አልን::

የቆሎ ተማሪዎች ከበራፋቸው እሳት አቀጣጥለው ጥሬ ይቆላሉ፣ ግማሾቹ ውኃ ይቀዳሉ::

«አይገርምም» አለኝ ያሬድ ተማሪዎችን ተመስጦ እያየ::

«ምኑ» አልኩት ነገሩ ቢገባኝም ሀሳቡን ለመረዳት ፈልጌ

«እያቸው እስኪ ይህችን በልተው'ኮ ሊያድሩ ነው፤»

«የእግዚአብሔር በረከት ስለሚጨመርበት ይበቃቸዋል:: ደግሞ ከምግቡ በበለጠ በቃለ እግዚአብሔር ስለሚጠግቡ ለእነሱ ይኸ 'ኮ ብዙ ነው» አልኩት መልሴ በእጅጉ የገረመው መሰለኝ:: ከእኔ ጋር ማውራቱን ትቶ እነሱን ይመለከት ጀመር::

✡ ✡ ✡

ቀኑ ወደ መምሸቱ እየተቃረበ በመሆኑ ሻንጣችንን ይዘን ተነስተን ወደ ተማሪዎቹ ተጠጋን:: እርስ በርሳቸው ያወራሉ:: አንደኛው ሲናገር በሙሉ ይስቃሉ:: ሌላኛው ሲደግም የሚያኮርፍም አይጠፋም:: እኛም ከበሩ አጠገብ ቆም ብለን ጥቂት አደመጥን:: ከውጭ ሌላ የጥሪ ድምፅ ይሰማል:: «ሙሴ...... ሙሴ........» ረጋ ያለ የአዛውንት ድምፅ ሰማን:: ጥቂት ቆይቶ በአካል እየቀረበን መጣ::

አዛውንቱ እድሜ የተጫናቸው ይመስላሉ:: የያዟትን ቀጠን ያለች መቋሚያ አስቀድመው አጠገባችን ደረሱ:: ሪዛቸው ደስ ይላል:: የለበሱት ረጅም ቢጫ ቀሚስ ከመልካቸው ቅላት እና ከሪዛቸው ጋር ተዳምሮ ውበት አልብሷቸዋል::

«ጤና ይስጥልኝ» አሉ አጠገባችን ሲደርሱ የማያውቁትን ሰው በማግኘታቸው ደንገጥ ብለው

«እግዚአብሔር ይመስገን» ብለን መስቀል ለመባረክ ጠጋ አልን

አባ አልቀረቡንም ወደ ኋላቸው አፈግፍገው

«እነማን ናችሁ?» አሉን

«የመጣነው ከሩቅ ቦታ ነው:: አሁን ማደሪያ እየፈለግን ነው?» አላቸው ያሬድ ለማግባባት እየሞከረ::

«እኮ....ለምን? ዛሬ ክብረ በዓል ሳይኖር ተሩቅ የሚያስመጣ ነገር ምን ተገኘ?» አሉን ጥያቄዎችን በጥያቄ እየመለሱ::

ጠጋ አልኳቸው «አባታችን የመጣነው ከመንግሥት መሥሪያ ቤት ነው? በቂ መታወቂያና ደብዳቤ ይዘናል:: በከተማውና በአካባቢው ያሉ አብያተ ክርስቲያናትን የቅርስ ብዛት ለማወቅ ቆጠራ ስለጀመርን እኛም በዚህ ቦታ ስለተመደብን ነው የመጣነው» አልኳቸው:: በመጠኑም ቢሆን በፊታቸው ላይ የመረጋጋት ስሜት አየንባቸው:: የያዝኩትን በማኅተም የተደገፈ ደብዳቤና መታወቂያዬን አሳየኋቸው:: የመታወቂያውን ፎቶግራፍ ተመልክተው ቀና ብለው አዩኝ::

«ታዲያ ሲመሽ ለምን መጣችሁ?» አሉኝ መታወቂያውን እንደያዙ መስቀላቸውን እያወጡ::

«ነገ እለቱ ሰንበት በመሆኑ ለሥራችን እንዲያመቸንና በዕለተ ሰንበት ቅዳሴ ለማስቀደስ ስላሰብን ነው» ያሬድ ፈጠን ብሎ መለሰላቸው::

«ጥሩ.... ነው እንግዲያው ማረፊያ ልጠይቅላችኋ» ብለው ወደ ተማሪዎቹ በአት ዘለቁ::

አባ ጥቂት ቆይተው አንድ ተማሪ አስከትለው ብቅ አሉ:: ምን እንደሚባባሉ ባይሰማንም ራቅ ብለውን ያወራሉ:: ጥቂት እንደቆዩ ተማሪው ያሉትን ለመፈፀም እየተቻኮለ ተመለሰ:: ከአጠገባችን ደርሶ ሰላምታ ከሰጠን በኋላ

«ተከተሉኝ» ብሎን ሻንጣችንን ይዞ ቀደመ::»

በትኅትናው እየተገረምን እኛም ድካማችን ቢበረታም የግዳችንን ተከተልነው:: ከአንድ ከተቀለሰ በራፍ ሲደርስ በያዘው ትንሽ መክፈቻ ከፍቶ ገባ እኛ ግን ከዚያው ቆም አልን::

ከውስጥ ገብቶ አልቆየም:: አነስ ያለች አጐዛ ቢጤ አንጥፎልን «ግቡ» አለን:: ተከታትለን ገባን:: ኩራዝ ተለኩሷል:: ከውስጡ የተለያዩ ቅዱሳት ሥዕላት ተሰቅለዋል:: ቤቱ ምንጣፍ ተነጥፎበታል ከቤቱ በአንድ ጥግ በኩል ከበሮ ተቀምጧል::

«አረፍ በሉ ለእግራችሁ ውሀ ላምጣ» ብሎ መልሳችንን'ኳ ሳይጠብቅ ወጣ::

እኛም ከድካማችን ማረፊያ በማግኘታችን ተቻኩለን ጋደም አልን:: ከጥቂት ቆይታ ቀድታ በኋላ ያገኘናቸው አባት በመሰቦ ወርቅ የሚበላ በአንድ እጃቸው ደግሞ የሚጠጣ ነገር ይዘውልን መጡ::

«ልጆች እንግዲህ እንደ ከተማውም ባይሆን እንዳይርባችሁ ይህችን ተመገቡ» አሉን:: ተነሥቼ ተቀበልኳቸው::

«አባታችን ይቀመጡ» አልኳቸው::

«አይዟችሁ የመጣችሁበትን ሥራ እስከምትፈጽሙ እረዳችኋለሁ:: አስተዳዳሪው ዘንድ ሂጄ ነግሬያቸዋለሁ:: ለሰዓታቱ ሌሊት ስለሚመጡ ትገናኛላችሁ» አሉን::

«አባታችን እግዚአብሔር ይስጥልን:: ሥራችን የተቃና እንደሚሆንልን ግን ተስፋ አደርጋለሁ» አልኳቸው::

«አዎ ልጄ! ታዲያ ዘገያችሁ:: ዛሬ አልነበረም ቅርስ መቁጠር:: ባዕድ ቸርችሮ ሲጨርሰው፣ ያልገባው ሲወስደው፣ ዝም አለችሁ:: ዋ! ልጆቼ ዛሬማ ምን ቅርስ አለ? ዓይናችን ታውሮ ልባችን በጥቅም ታሥሮ ራሳችንን ማንነታችንን አሳልፈን ለማናውቀው ባዕድ ሰጠን:: ይሁዳስ ከፈጣሪ እግር ሥር ተቀምጦ ይማር አልነበረም:: ኋላ ግን ብር ሲያይ ልቡ ደነገጠበትና የሥጋው ነገር በልጦ ታየው እንጂ:: ዛሬም ታዲያ ነገሩ ሁሉ የይሁዳ ሆነብኝ:: የቤተክርስቲያን ልጆች ቅርስ ተረካቢዎች ጠፉ:: ሁሉም ሥጋው በልጦበት ቅርሱን እያወጣ ቸበቸበው» እንባቸው የሚተናነቃቸው መሰለኝ::

«አባታችን ችግሩን ሁሉ ለማቃለል ያሉትን ቅርሶችን በምዝገባ ለማወቅ እንዲቻል በተዘጋጀ ፕሮግራም ሁሉም በየቦታው ተልኳል:: ቅርሶች እንዳይባክኑ የሚረዳ መፍትሔ በመሆኑ ለትውልድ አሻራ ለማስቀረት ሁሉም የበኩሉን እያደረገ ነው» አልኳቸው በአትኩሮት እየተመለከትኳቸው::»

አባ ፈገግ አሉ:: «አይ ልጅ ጅብ ከሄደ......» አሉ ያገሬ ሰው ዛሬማ ምንቀረና? ምን ቅርስ አለና? ልጄ እኔኳ ተዚህ ተመጣሁ ስምንተኛ ዓመቴን ልጨርስ ነው:: ታዲያ ስለቅርስ የሚጠይቅ የሚጨነቅ ማን አለ? ክብረ በዓል ሲደርስ ብቻ ሆያ እና ሠላሳ መኪና መጥቶ ተመተራመስ ሌላ፣ ፎቶ ተነሥቶ፣ ቀርጦ ይሄዳል እንጂ ማን ስለ ቅርስ አንሥቶ? ታዲያ ይህ ነው ተረካቢ ትውልድ? ሁሉ የበኩሉን የሚያደርገው እንዲህ ነው?» አነጋገራቸው ትዝብትና ቀጣ የተቀላቀለበት መሠለኝ::

«አባ ያለፈው አልፏል ከዚህ በኋላ ላለው ነገር ግን ቆርጠን ተነሥተናል:: የእናንተ የአባቶቻችን ጸሎት እንደሚረዳን እንተማመናለን:: እናንተም የበኩላችሁን እንደምታደርጉልን ትልቅ ተስፋ አለን» አልኳቸው::

ከቤት ያስገባን ተማሪ ውኃ በትንሽ ሸክላ አድርጐ ይዞልን መጣ:: ፈቃደኛ ባንሆንም ከብዙ ትግል በኋላ እግራችንን ራሱ አጠበን:: ትኅትናው ምግባሩ የሚረሳ አይደለም:: ያመጡልንን ዳቤና ጠላ አቅርበው ከባረኩልን በኋላ አብረን ተቋደስን::

«ተቤት ጠብቀኝ መጣሁ!» አሉት ልጁን

«እሺ አባ» ብሏቸው ተሰናብቶን ወጣ::

«ይኸውላችሁ ተዚህ ሀገር ተገባሁ ጀምሮ ያልተለየኝ የፀና ልጅ ነው::

ቀኑን በሥራ ይጠመዳል እንደ ሌሎቹ ተማሪዎች ብዙም አይሞላለትም:: ታዲያ ሌሊቱን በሙሉ ተቀምጦ ሲማር ያድራል:: የቅኔ ድርሰት እንዲህ አይምሰላችሁ:: ጉበዝ ነው:: በሥራው ስለተመሳሰለብኝ ዳግማዊ ኒቆዲሞስ አልኩት» አሉን ለእሱ ያላቸውን ፍቅር ለመግለፅ እየሞከሩ::

«በጣም ይገርማል» አልኳቸው

«በሉ ልጆቼ አረፍ በሉ ሌሊት በ6:00 ሰዓታት ስለምንጀምር አረፍ ልበል:: ተቅዳሴ በኋላ ሥራችሁን ስትጨርሱ ወደ እኔ ዘንድ ብቅ በሉ:: ምናልባት ለሥራችሁ እጠቅም ይሆናል::» ብለውን መልስ'ኳ ሳይጠብቁ በሩን ዘግተው ወጡ::

✡ ✡ ✡

ሌሊቱ ረዘመብኝ:: ሳናስባቸው ያገኘናቸው አባት በእጅጉ ገረሙኝ ለሥራችሁ እጠቅማለሁ» ማለታቸው

«ምን ይሆን?» ውስጤ ዕረፍት አጣ:: ያሬድ ድካሙ አሸንፎት ነው መሠለኝ በጸጥታ ተኝቷል:: ኩራዙ ይበራል:: ሻንጣዬን ከፍቼ ማስታወሻዬን አወጣሁ:: የማቀርብላቸውን በጥያቄ በደብተሬ ላይ አስፈርኩ:: ሰዓቴን ወደ ኩራዙ አስጠግቼ ተመለከትኩት:: 7:30 ይላል «ተመስገን» አልኩ:: ከዚህ በኋላ የምንጓዝበትን መንገድ እያውጠነጠንኩ በሀሳብ ማዕበል ተንሳፈፍኩ:: በዚያው ሸለብ አደረገኝ::

ከእንቅልፌ ስነቃ 11:00 ሆኗል:: በፍጥነት ተነሥቼ ልብሴን ለበስኩና ያሬድን ቀሰቀስኩት:: እንደምንም ዓይኑን እያሸ ተመለከተኝ::

ይቀጥላል

✡ ✡ ✡

## የርዕሰ አድባራት ዙር አባ...

/ከገጽ 18 የዞረ/ እንኳን የበጐ አድራጊዎች ልገሳ ቢደረግለትም አሁን ካለው የተማሪዎች ቁጥር ጋር ባለመመጣጠኑ እና ሕንፃው ለረጅም ዓመታት እድሳት ስላል ተደረገለት እየፈራረሰ ነው:: እንዲሁም ለተማሪዎች የሚያስፈልጉ ዕቃዎች /መኝታ፣ የማብሰያ እቃዎች የመሳሰሉት/ ባለ መሟላታቸው ለተለያየ ችግር ተጋልጠዋል::

ቤተክርስቲያናችን ጥንታዊነቷን ከምታስመሰክርበት ነገሮች ዋነኞቹ ቀደምትነት ያላቸው ገዳማት እና አድባራት፣ በውስጣቸው ያለው ንዋየ ቅድሳት እና ታሪካቸው መሆኑ ይታወቃል:: ከተመሠረተ 1400 ዓመት አካባቢ ያስቆጠረው የጽርሃ አርያም ዙር አባ አረጋዊ ገዳምም ከነዚህ ውስጥ የሚጠቀስ ነው:: በውስጡ ባሉት ንዋየ ቅድሳት እና ቅርሳ ቅርስ፣ በቤተክርስቲያኑ ሥሪት እና በታሪኩ ቀደም ብለው የነበሩ አባቶችን እምነት እና ጽናት የሚያሳየው ይህ ገዳም ዛሬ ያለበት ሁኔታ እጅግ በጣም አሳሳቢ ነው:: ቀደም ብለው የነበሩ አገልጋይ መነኮሳት ይተዳደሩበት የነበረው መሬት በመወሰዱ ለረሃብ መጋ ለጣቸው፣ የአብነት መምህራን እና ተማሪዎች በተለያዩ ችግሮች መበተናቸው የዛሬውን የቤተክርስቲያን ተረካቢ ትውልድ የሚያሳፍር ነው:: ምንም እንኳን በከተማው እና በአንዳንድ ገጠር አካባቢ አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናት መታነጻቸው እና በአዲስ መልክ መሠራታቸው የሚያበረታታ ቢሆንም አባቶቻችን ያላቸውን ሁሉ ሠጥተው ያቆዩልንን ታሪካዊ እና ጥንታዊ ገዳማት እና አድባራት ከንቅርሶቻቸው ጠብቀን የማቆየትም ሃይማኖታዊ ግዴታችንን መዘንጋት የለብንም:: ለዚህ ገዳም በማኅበረ ቅዱሳን የገዳማት የአድባራትና የአብነት ት/ቤቶች መርጃና ማቋቋሚያ ንዑስ ክፍል ወደፊት ራሱን ችሎ መተዳደር የሚያስችል ፕሮጀክት ተቀርጾለት የበጐ አድራጊዎችን ልገሳ በመጠባበቅ ላይ እንደሆነ ለመግለጽ እንወዳለን:: ረድኤተ እግዚአብሔር አይለየን

## ዋቤ መጻሕፍት

1. የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ታሪክ ዕድገትና ነፃነት፣ በኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ጥቅምት 15 ቀን 1934 ዓ.ም. ፣ አዲስ አበባ
2. ድርሳነ ኡራኤል ግንቦት፣ 1991 ዓ.ም. አዲስ አበባ
3. ታሪከ ነገሥት

# የርዕሰ አድባራት ዙር አባ አረጋዊ ጽርሐ አርያም ገዳም ታሪክ

በማኅበረ ቅዱሳን የገዳማት፣የአድባራትና የአብነት ትምህርት ቤቶች
መርጃና ማቋቋሚያ ን/ክፍል
/ቴዎድሮስ ተስፋዬና ሒሩት በቀለ/



ዙር አባ አረጋዊ ጽርሐ አርያም ቤተክርስቲያን

ከሠዓሊ /ሣሊ/ መንደር በስተ ምሥራቅ የገሊላ ተራራ ዙሪያውን ሳሉት ሾጣጣ የድንጋይ ቋጥኞች እና ሠንሰለታማ ተራሮች አባወራ መስሎ ከመካከላቸው ተከፍሏል። የገሊላ ተራራ በደቡብ ጐንደር መስተዳደር ዞን በላይ ጋይንት ወረዳ ዙር አባ ቀበሌ ገበሬ ማኅበር ፣ ከባህር ዳር ወደ ንፋስ መውጫ በሚወስደው መንገድ 150 ኪሎ ሜትር ላይ ከምትገኘው ሠዓሊ /ሣሊ/ መንደር በስተ ምሥራቅ ይገኛል። ከሠዓሊ መንደር ወደ ተራራው በሚወስደው የአንድ ሰዓት ተኩል የእግር መንገድ ግራና ቀኝ የተተከሉት የባሕር ዛፎች ለመንገደኞች የተዘጋጁ ጥላዎች ይመስላሉ። በአንፃሩ ደግሞ ትንሽ አለፍ እንዳሉ ወጣ ገባውና ድንጋያማው መንገድ እንደ ምሰሶ ቀጥ ያለውን ተራራ ለመውጣት የሚደረገውን የእግር ጉዞ ፈታኝ ያደርገዋል። እግዚአብሔር ለቅዱሳኑ በአት እንዲሆን ከሰማይ ዝቅ ከመሬት ከፍ አድርጎ ያዘጋጀው ይህ ሥፍራ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዕለተ ዓርብ በተሰቀለ ጊዜ መልአኩ ቅዱስ ዑራኤል ደሙን በጽዋ ሲረጭ የበረከቱ ተካፋይ ሆኖአል። ለዚህም ነበር መልኩ ቅዱስ ዑራኤል ለአቡነ አረጋዊ እና ለቅዱስ ያሬድ በጣና ደሴት ሳሉ «በጌምድር ወደተባለው ሀገር ሂዱ በዚያ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በደሙ የዋጃት ደብር አለች» ያላቸው።

## የገዳሙ አመሠራረት

በደብረ ዳሞ በአታቸው የሚታወቁት ጻድቁ አባት አቡነ አረጋዊ በዚህ በገሊላ ተራራ ላይም ተመሳሳይ ታሪክ አላቸው። ዘመኑ በስድስተኛው ክፍለ ዘመን በንጉሡ በአፄ ገብረ መስቀል /523–537 ዓ.ም./ ዘመነ መንግሥት ነው። ጻድቁ አባታችን አቡነ አረጋዊ፣ ቅዱስ ያሬድ እና አፄ ገብረ መስቀል ከአክሱም ተነሥተው ጣና ሐይቅን እና ደሴቱን ለመጎብኘት ተጉዘው ነበር። በዚያ የቅዱስ ቂርቆስን ቤተ ክርስቲያን አንጸው እያገለገሉ ሳሉ መልአኩ ቅዱስ ዑራኤል ተገልፆላቸው፦

«ወደ በጌምድር /ጐንደር/ ሂዱ። ከዚያች በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ደም የባረከኳት የማሳያችሁ አነስተኛ ተራራ አለችና በርስዋ ላይ አምላክን በወለደች በእመቤታችን በድንግል ማርያም ስም ቤተ ክርስቲያን ሥሩ አላቸው» /ድርሳነ ኡራኤል/

ከዚያ ሦስቱም ተነሥተው ጨፋ የተባለውን ትልቅ ወንዝ ተሻግረው በተራራው አካባቢ ደረሱ። ነገር ግን ተራራውን ማግኘት ስላልቻሉ በፍለጋ ዋሉ። ጊዜው ስለመሸም በዚያው አረፉ። በመጨረሻ የገሊላን ተራራ ሲመለከቱ ይህ መሆን አለበት በማለት ወደ ተራራው ሊወጡ ቢያዩ መውጫ የሌለው ቀጥ ያለ ገደል ሆኖ አገኙት። በጣና ደሴት የተገለጸላቸው መልአኩ ቅዱስ ኡራኤል « ዙር አባ ወደ እርሷም ትወጣ ዘንድ በምሥራቅ በኩል ተራራዋን ዙር አስቀድሜ በባሕረ ጣና ደሴት የነገርኳችሁ ተራራ ይህች ናትና» አላቸው። በተጨማሪም «ለልጆችህ ማደሪያ አድርጋት፤ እንደ ክርስቶስ ወንጌል ሥርዓት ይህችን ቤተክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ ለምትወልዳቸው ልጆችና ለአንተ ጭምር ርስት አድርጌ ሰጥቿችኋልና።» /ድርሳነ ኡራኤል/ አላቸውና በስተ ምሥራቅ ሲዞሩ ዕፀ ሳቤቅ የተባለ ነጭ ሐረግ ከተራራው ወደ መሬት ተንጠልጥሎ አግኝተዋል። በሐረጉ አባ አረጋዊ እና ቅዱስ ያሬድ ወደ ተራራው ሲወጡ አፄ ገብረ መስቀል ግን ድንኳን ተክለው ከተራራው ሥር አረፉ። ቦታው «ዙር አባ» የተባለውን ስያሜ ያገኘው ከዚህ የተነሳ ሲሆን አፄ ገብረ መስቀል ያረፉበት ቦታ ደግሞ አፄ ከተማ እየተባለ እስከ ዛሬ ድረስ ይጠራል። ጻድቁ አባት አቡነ አረጋዊ እና ቅዱስ ያሬድ ተራራው ላይ ሲወጡ ከተራራው አናት ላይ የተነጠፈ ሰፊ ለምለም መስክ አገኙ። ይህ ቦታ ሰማያዊ እንጂ ምድራዊ ብቻ አይደለም በማለት ጽርሐ አርያም ብለውታል። የያዙትን ጽላት በሐር ድንኳን ውስጥ አሳርፈው ሱባኤ ይዘው ሲጸልዩ መልአኩ ቅዱስ ኡራኤል ኅብስተ መና ወይነ ሕይወት ይመግባቸው ነበር። በሃያ አንደኛው ቀን /በሦስተኛው ሱባኤ/ አፄ ገብረ መስቀል ካረፉበት ከተራራው ሥር ወደ ተራራው ለመውጣት ፈልገው መውጫ አጥተው ሲጨነቁ ጻድቁ አባታችን አቡነ አረጋዊ ከተራራው አናት ላይ ሆነው አዩዋቸው። አባታችን ተራራውን በመስቀላቸው ባረ ኩት። ከሁለት ተሠንጥቆ ከመሬት ወደ ተራራው ሊያወጣ የሚችል አንድ ሰው ብቻ የሚያሳልፍ ሠርጥ መንገድ ተከፈተላቸው። አፄ ገብረ መስቀልም በዚያ ሠርጥ በኩል ወደ ተራራ ወጥተዋል።

ከዚህ በኋላ ለሦስት ዓመት አፄ ገብረ መስቀል ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን ሲያሠሩ፣ ጻድቁ አባታችን አቡነ አረጋዊ ሕገ ቤተ ክርስቲያን እና ሥርዓተ ምንኩስና ሲያስተምሩ፣ ቅዱስ ያሬድ ዝማሬ መዋሥዕትን በዜማ እየደረሰ ሲያስተምር ቆይተዋል። በመጨረሻም ጻድቁ አቡነ አረጋዊ ስድስት መቶ አርባ /640/ ማኅበረ መነኮሳት ሰብስበው አቡነ ዮሐንስ የሚባሉ አባት ሰይመው ሦስቱም ወደ አክሱም ደብረ ሐዊ ወደ ምትባል አገር ሄደዋል።

## በግራኝ መሐመድ ጊዜ /1521 ዓ.ም./

ገዳሙ እስከ ግራኝ መሐመድ /1521 ዓ.ም./ ጥፋት ድረስ በብዙ ነገሥ

ታት እየተደገፈ ምእመኑን ሲያገለግል ነበረ:: ይህ ገዳም በግራኝ ጥፋት ምክንያት መቅደሱ ሲቀር በመፈራረሱ እና የተቀረው ክፍል በመቃጠሉ በገዳሙ የነበሩ መነኮሳት፣ አገልጋይ ካህናት፣ አንዳንድ ንዋየ ቅድሳት፣ የብራና መጻሕፍቱን እና ጽላቱን ይዘው በዋሻ ገብተዋል:: የልደታ ማርያምን ጽላት ይዘው ወደ ዋሻው ከገቡት ውስጥ ስልሣ /60/ መነኮሳት እና አርባ /40/ ካህናት በዚያው እንደተሰወሩ ቀርተዋል:: ዋሻው እስከ አሁን ድረስ ያለ ሲሆን ወደዛ ለመቅረብ ማንም አይደፍርም:: አንዳንዴ የቆሎ ተማሪዎች ቅኔ ለመቁጠር ሲሄዱ የነብር እና ያልተለመደ ድምጽ እንደሚሰማ ይናገራሉ::

ኅዳር 20 ቀን 1521 ዓ.ም. ቤተ ክርስቲያኑ ከተቃጠለ በኋላ ለሠላሳ ዓመታት ያህል ያለምንም አገልግሎት ተዘግቶ ቆይቷል::

## በአፄ ሠርፀ ድንግል ዘመን /1553 – 1587 ዓ.ም./

ንጉሡ አፄ ሠርፀ ድግል በዘመነ መንግሥታቸው ጦርነት ገጥሞአቸው በነበረ ወቅት ስዕለት ይገባሉ:: ይኸውም «ጠላቶቼን ድል አድርጌ ስመለስ የዙር አባ ቤተ ክርስቲያንን ሕንጻ አስጨርሳለሁ» የሚል ነበር:: እርሳቸውም ድል አድርገው እንደተመለሱ ቃላቸውን በመጠበቅ ቤተ ክርስቲያኑን የሚያሠሩ ባለሞያዎች እና ገንዘብ ላኩ:: ከአራት ዓመት በኋላም አስቀድሞ በአፄ ገብረ መስቀል ተሠርቶ በነበረው እና ከግራ‸ ቃጠሎ ከተረፈው ከመቅደሱ ቀ‸ ው ቅድስቱን አሠርተው የቀረውን አስጠግነዋል::

ከግራኝ መሐመድ በኋላ አራት መነኮሳት ከሸዋ ወደ ጐንደር በመ ንፈስ ቅዱስ ተመርተው መጡ:: ከዙር አባ በስተ ምዕራብ ጨፋ የሚባለው ወንዝ አካባቢ ዕቃ ቤት /ዐቃቢት ማርያም/ አረፉ:: በዚያ ሱባኤ ይዘው ሲጸልዩ ሳሉ ሀብተ መንፈስ ቅዱስ ታደላቸው እና እጣ ተጣጥለው በአካባቢው ባሉ ገዳማት እንዲያገለግሉ ደረሳቸው:: ይኸውም አባ ለባዌ ክርስቶስ ዙር አባ አረጋዊ፣ አባ መሰንቆ ድንግል ቤተልሔም፣ አባ ብእሴ እግዚአብሔር ገደባ መርቆሪዮስ እና አባ ተክለ ወልድ ደብረ ማርያም ነበር:: ለባዌ ክርስቶስ ከግራኝ መሐመድ በኋላ የነበሩ የመጀመሪያው አባት ናቸው:: ከዚያም አባ አካለ ክርስቶስ፣ አባ ቴዎድሮስ ተሹመዋል:: ገዳሙ ከተመሠረተ ጀመሮ 69 አባቶች የተሾሙ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ ገዳሙን የሚያ ስተዳድሩት አባ ውሂበ ሥላሴ ከግራኝ ወዲህ 21ኛው አባት ናቸው:: አባ ለባዌ ክርስቶስ በዚህ ገዳም ሲያገለግሉ በአራት ካህናት የምትያዝ አራት እግር /ሸንኮር/ ባላት መንበር ውስጥ የምትቀመጥ የእመቤታችን ጽላት ከሸዋ ይዘው መጥተዋል:: መንበሩ የተሠራው ከዕፀ ቄድ ሮስ /ከቄድሮስ እንጨት/ ሲሆን እግሮቹ የዝሆን ጥርስ ናቸው:: ቅድስት አርሴማ የሚል ጽሑፍ አለበት:: ጽላቱ በአራት ዓመት አንዴ ግንቦት አንድ ቀን በዑደት ይከብራል:: መንበሩ ከመጣበት ጊዜ ጀምሮ የተቆለፈ ሲሆን ቁልፉን የሚይዙት አንድ መነኩሴ ብቻ ናቸው:: እርሳቸው ሲደክሙ ለማንም ሳይናገሩ ለሌላ መነኩሴ ቁልፉን ያስረክባሉ:: በአፄ ዮሐንስ ዘመነ መንግሥት በወቅቱ የነበሩ እጨጌ ቴዎ ፍሎስ መንበሩን ከፍተው ጽላቱን ለማየት ቢነኩት እጃቸው ተኮማትሮ እራሳቸውን ስተው ወድቀው ነበር:: በኋላም መነኮሳቱ ጸሎት አድርገው እጃቸው እንደቀድሞ ደህና ሆኖ ወደ አእምሮአቸው ሲመለሱ ካባቸውን እና ልብሳቸውን ለታቦቷ ክብር ሲሉ አውልቀው እንደሰጡ አባቶች ይናገራሉ::

## የቤተ ክርስቲያኑ አሠራር እና በውስጡ ያሉ ንዋየ ቅድሳት

ንጉሡ አፄ ገብረ መስቀል የመጀመሪያውን ሕንፃ በሣርና በጭቃ ከጨጨሆ እስከ ዓባይ፣ ከኸርጣ እስከ ጐደሬ ያለውን ሕዝብ በአዋጅ እያዘዙ እንደሰሩ ይነገራል:: ሕንፃ ቤተ ክርስቲያኑ በ350 ካሬ ሜትር ቦታ ላይ ያረፈ እና አሠራሩ እና ዲዛይኑ በጣና ሐይቅ ደሴቶች ያሉትን ታሪካዊ አብያተ ክርስቲያናት እና ገዳማት እንደሚመስል ከባሕል ቱሪዝም እና ማስታወቂያ ቢሮ ከተገኘ የጥናት ጽሑፍ ተረድተናል:: ክብ ቅርጽ ያለው ይህ ሕንፃ መቅደሱ ከግራኝ መሐመድ ቃጠሎ የተረፈ ሲሆን ከታች መሠረቱ ከጥርብ ድንጋይ የተሠራ እና አራት መዓዘን ቅርጽ ያለው ሆኖ ከጣሪያው ጋር በክብ ቅርጽ ይገናኛል:: የመቅደሱ ወለል ከመጀመሪያ ጀምሮ የነበረው በጥርብ ድንጋይ የተነጠፈ ነው:: ሦስት በሮች እና ሰባት ትንንሽ መስኮቶች ሲኖሩት ግድግዳው ሙሉ በሙሉ በቅዱሳን ሥዕላት የተሸፈነ ነው:: በአፄ በካፋ ዘመነ መንግሥት /1713 – 1722 ዓ.ም./ የተሳለው ይህ ሥዕል በጐታው ላይ በምዕራብ የቅድስት ሥላሴ፣ በምሥራቅ ምጽአተ ክርስቶስ፣ በሰሜን ዕርገቱን እና በደቡብ ደብረ ምጥማቅ ይገኙባቸዋል:: የኢትዮጵያውያን የአሣሣል ዘይቤ ያላቸውና ጥንታዊነት የያዘ ውበት ያላቸው ብዙ ስዕላትም አሉት:: በስተ ምዕራብ በኩል ያለችው የእመቤታችን ሥዕል ደግሞ ልዩ መስህብ አላት:: በሁሉም አቅጣጫ ቢዞሩ የተመልካችን ዓይን የምትከታተል ይመስላል:: ይህች ሥዕል በመጋረጃ የተጋረደች ሲሆን ለማየት በሚፈለግበት ጊዜ ካህናቱ አደግድገው፣ ልብሰ ተክህኖ ለብሰው ዕጣን እያጠኑ መጋረጃውን ይገልጡታል:: በግድግዳው ላይ ያሉት ሥዕሎች በሙሉ ከጣሪያው እስከ ወለሉ በመጋረጃ የተሸፈኑ ሲሆን በወለሉ አቅራቢያ ያሉት ሥዕላት ግን ቀለማቸው ደብዝዞ የቀድሞ ውበታቸው እየጠፋ ይገኛል:: ሥዕሉን የሳሉት አብለኒዮስ እና ሕዝቅኤል የተባሉ የአካባቢው ተወላጆች ሲሆኑ ርስት ተሠጥቷቸው በዚያው አካባቢ ባለ መንደር ይኖሩ ስለነበር የአካባቢውም ስም እስከ ዛሬ ድረስ በሞያቸው ሠዓሊ /ሣሊ/ እየተባለ ይጠራል::

ቅድስቱ ከላይ አራት የመስቀል ቅርጽ ያላቸው ትንንሽ መስኮቶች፣ ትንሽ ወረድ ብሎ ስምንት ከላይኛው ተለቅ ያሉ መስኮቶች እንዲሁም ሦስት ባለ ሁለት ተከፋች እና አምስት ትናንሽ በሮች አሉት:: በሮቹ ከአንድ ወጥ ሳንቃ የተጠረቡ እና በቆዳ የተለበጡ ናቸው:: የአብዛኛዎቹ ቆዳ ከዕድሜ ብዛት የተቀደደ እና ያረጀ ነው:: ካህናቱ ማኅሌት በሚቆሙበት በኩል ባለው በር በቆዳው ላይ የተለያዩ ጽሑፎች ይገኛሉ:: አብዛኛውን በማርጀታቸው ለማንበብ ባይቻልም ‸ንዳንድ አባቶች በተለያየ ጊዜ የተቀኙ‸ ቅኔዎች እንደሚጽፉ ከአባቶች ተረድተናል:: ወለሉ የሲሚንቶ ሊሾ ሲሆን ያ‸ ጁ እና የተበጣጠሱ ምንጣፎች አልፎ አ‸ ‸ዩበታል:: በዚህ ክፍል ውስጥ ከ‸ ‸ት በኋላ ቤተ ክርስቲያኑ በአፄ ሠ‸ ድንግል ሲታደስ የተተከሉ 20 ዓምደ ወርቆች /ምሰሶዎች/ ይገኛሉ:: በተጨማሪም በሁለት ትላልቅ አግዳሚዎች የተያያዙ እና ጣሪያውን /ባጡን/ የተሸከሙ ሠላሳ አምስት ትንንሽ ዓምዶቹ አሉ:: ዓምዶቹ በጣም ትላልቅ እና በአካባቢው ካሉ ዛፎች የተለዩ ናቸው:: ዓምዶቹን ወደ ተራራው ለማውጣት በዚያ በሰርጥ መንገድ በእግዚአብሔር ተአምር ካልሆነ በስተቀር በጣም አስቸጋሪ እንደሆነ መገመት ይቻላል:: ከሀያዎቹ በስተ ምዕራብ የሚገኘው አንዱ ምሥዋር የሚባል ክፍል አለው:: ዓምዱን በቁመቱ ወደታች በመፈልፈል ከዓምዱ እንጨት ክዳን ተሠርቶለታል:: የፍልፍሉ ክፍተት እስከ መሬት የሚደርስ ሲሆን በውስጡ ስላሉት ነገሮች ግን ማንም ምሥጢሩን እንደማያውቅ ገልጸውልናል::

ቅኔ ማኅሌቱ ዙሪያውን ግድግዳው ከድንጋይ ከጭቃና ከጽድ እንጨት የተሠራ ነው:: ሃያ ስድስት ሰፋፊ መስኮቶችና ሦስት በሮች አሉት:: መስኮቶቹም ሆኑ በሮቹ መዝጊያ የሌላቸው ናቸው:: ቀደም ሲል በሸንበቆ ጉንጉን /አቴና/ ለብሶ የነበረው ወለል ዛሬ ግን በባዶ አፈር ላይ የሣር ጉዝጓዝ ተሸፍኖ ይገኛል:: ሕንፃ ቤተ ክርስቲያኑ በተለያየ ጊዜ እድሳት የተደረገለት ሲሆን የመጀመሪያው በአፄ ሠርፀ ድንግል ዘመነ መንግሥት ነው:: ሁለተኛው በአፄ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግሥት ሲሆን ለሦስተኛ ጊዜ በአፄ ኃይለ ሥላሴ /1959 ዓ.ም./ ቤተ ክርስቲያኑ ታድሶአል:: የገዳሙ ግቢ ጠባብ ቢሆንም ከቤተልሔሙ በተጨማሪ የተግባር /የማኅበር/ ቤት፣ የግብር ቤት፣ ሁለት የመነኮሳት ቤት እና የዕቃ ቤት ይገኙበታል:: የተለያዩ የዛፍ ዓይነቶች አልፎ አልፎ ሲኖሩት በስተምሥራቅ በኩል «ከርሞ አይደርቅ» የምትባል ቅዱስ ያሬድ እንደ ጥላ እየተጠቀመ ያስተምርባት የነበረች የወይራ ዛፍ አለች:: «ከርሞ አይደርቅ» የተባለችው ለረጅም ዓመት ሳትደርቅ በመቆየቷ ነው::አንዳንድ ጊዜም በአንድ ጐኗ እየደረቀች በሌላ በኩል እየለመለመች ኖራለች:: አሁን ግን ቤተ ክርስቲያኑ በሚታደስበት ጊዜ ስትመለመል ደርቃ እንጨቷ ብቻ ቆሞ ቀርቷል::

ከቤተ ክርስቲያኑ በስተ ደቡብ ከተራራው ቁልቁል ሲወረድ የአቡነ ተክለ ሃይማኖት ዋሻ ይገኛል:: ጻድቁ አባታችን በዚህ ዋሻ ውስጥ ለስድስት ዓመት እንደኖሩ አባቶች ይናገራሉ:: ከዋሻው አናት

ላይ ለማየት የሚያስፈሩ የድንጋይ ቋጥኞች ተከምረዋል። ከፊት ለፊቱ ያለውን ገደል ለማለፍ አስቸጋሪ ቢሆንም ከተራራው ጥግ ቀጭን መንገድ አለ። ዋሻው በጣም ጠባብ ሲሆን ጻድቁ ይጠቀሙባቸው የነበሩ ገበቴ፣የመጻሕፍት መስቀያ ባለባላ እንጨት፣ሙቀጫና የመሳሰሉት ቁሳቁሶች ይገኛሉ። በውስጡ የነበረውን ጽላት በዙር አባ አረጋዊ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አስገብተውታል። አሁን ዋሻውን አንዳንድ አባቶች ለሱባኤ ይጠቀሙበታል።

በግራኝ ጊዜ አባቶች በዋሻ ደብቀዋቸው ከቃጠሎ የተረፉ ብዙ የብራና መጻሕፍት እና ከዚያም ወዲህ መኳንንት እና ነገሥታት ለገዳሙ ያበረከቷቸው ብዙ ንዋየ ቅድሳት፣ የብርና የወርቅ ካባዎች፣ አክሊሎች፣ ደወሎች፣ የመፆር እና የእጅ መስቀሎች፣ የያሬድ የብር መቋሚያ እና ጸናጽል ይገኛሉ። በዕቃ ቤት ጥበት እና ማስቀማጫ ሳጥን ወይም ለመጻሕፍቱ መደርደሪያ ባለመኖሩ በጨርቅ ከረጢት ውስጥ እየተጠቀለለ በመቀመጣቸው አብዛኛዎቹ ለብልሽት ተዳርገዋል። የብራና መጻሕፍቱን አባቶች ከቃጠሎና ከጥፋት ያዳኗቸው ቢኖሩም በቅዝቃዜ እና መሸፈኛዎቻቸው በመገንጣጠሉ አብዛኛዎቹ ጽሑፋቸው እየጠፋ ይገኛል። የወርቅ እና የብር ካባዎች አቀማመጣቸው ጥሩ ባለመሆኑ ጨርቃቸው እየተተለተለ የወርቅ እና የብር ፈርጦቻቸው እየረገፉ ነው። የመስቀሎቹ፣ የአክሊሎቹ እና የደወሎቹ መልክም አፈር መስሏል። የገዳሙ መነኮሳት እና የአካባቢው ኅብረተሰብ ለንዋየ ቅድሳቱ ጥሩ ጥበቃ ቢያደርጉለትም አቀማመጣቸው ግን እንደነበሩ የመቆየት እድሜያቸውን ይቀንሰዋል።

ቤተ ክርስቲያኑ ወደ አለበት የተራራ ጫፍ ለመውጣት ያለው መንገድ አንድ ብቻ ሲሆን እርሱም ጻድቁ አባት አቡነ አረጋዊ በመስቀላቸው ተራራውን ሲባርኩት ተራራው ተከፍሎ የተሰነጠቀው የሥርጥ መንገድ ነው። ሥርጡ አንድ ሰው ብቻ የሚያሳልፍ ሲሆን የአካባቢው ኅብረተሰብ በተለይ በቀብር ጊዜ አስከሬን ይዞ ወደ ላይ ለመውጣት በጣም ይቸገሩ ነበር። በ1985 ዓ.ም. ግን በአንድ በጎ አድራጊ እና በአካባቢው ኅብረተሰብ ትብብር መውጫ የሚሆኑ አነስተኛ ደረጃዎችን በመሥራት ችግሩን አቃለውታል። የሥርጡ መንገድ እንደ አለቀ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ የሚያደርስ ሁለት መንገድ አለ። መገንጠያው ላይ የአካባቢው ሕብረተሰብ አንድ ጉጆ ቤት ሠርተው ለቀን ሁለት ሰው ለማታ ደግሞ አራት ሰው በየተራ እየተመደቡ ይጠብቃሉ። ኅብረተሰቡ ለቤተ ክርስቲያኑ እና ለንዋየ ቅድሳቱ ያለው ትኩረትና ጥበቃ በእጅጉ የሚደነቅ ነው።

በገዳሙ ያሉት መነኮሳት ሦስት ሲሆኑ ሁለት ወንዶች እና አንድ ሴት ናቸው። በገዳሙ ደንብ መሠረት የቅዱሳው ሥርዓት የሚከናወነው በደናግል መነኮሳት እና ከ10-18 የእድሜ ክልል ባሉ ዲያቆናት ብቻ ነው። በተጨማሪም ከአንድ መቶ ሃምሳ በላይ የሚሆኑ ካህናት ከተራራው ሥር ባለው መንደር በግብርና ሥራ የሚተዳደሩ አሉ። በገዳሙ በሰዓታት፣ በማኅሌት እና በሌሎች አገልግሎት ጊዜ ያገለግላሉ። በየወሩ የእመቤታችን ዕለት /በ21/ የእመቤታችንን ሥዕል አድኅኖ በመያዝ ዑደት ይደረጋል። በየቀኑ ከኪዳን በኋላ ቅዳሴ ከሌለ በስተ ምሥራቅ በኩል በውጪ በመቆም ስብሐተ ነግህ ያደርሳሉ። በገዳሙ ዙሪያ አስቀድሞ በዚሁ ገዳም ቀፈፍ /ትተዳደር/ የነበረች በአባ ገብረ ሥላሴ የተተከለች ወፍ ዋሻ ማርያም የምትባል እና አስራደ ሚካኤል የሚባሉ አብያተ ክርስቲያናት አሉ። በወፍ ዋሻ ገደል ስር በስማዕቱ ቅዱስ ጊዮርጊስ ስም የተሰየመ እና ብዙ ሕሙማኖችን የሚፈውስ ጸበል አለ። እንዲሁም በሌሎች ቅዱሳን ስም የተሰየሙ ብዙ ጸበሎች ይገኛሉ። የአካባቢው ኅብረተሰብ ኅዳር 30 የአጼ ገብረ መስቀልን ዕረፍት፣ ግንቦት 11 ቅዱስ ያሬድ የተሰወረበትን፣ ሰኔ 8 የለባዊ ክርስቶስ ዕረፍታቸውን እና ሌሎችንም ያዘክራሉ።


/ከርሞ አይደርቅ ዛፍና የቅዱስ ያሬድ መቋሚያና ጸናጽል

## የዝማሬ መዋሥዕት ማስመስከሪያ ት/ቤት

ቅዱስ ያሬድ ወደዚህ ሥፍራ ከመጣበት ጊዜ ጀምሮ የዝማሬ መዋሥዕት የአብነት ትምህርት ቤት ሆኖ ሲያገለግል ነበር። ቅዱስ ያሬድ በዚያው በገዳሙ ግቢ ውስጥ በስተ ምሥራቅ በኩል ዛፍ ስር ቁጭ ብሎ ያስተምር ነበር። አባ በኪሞስ የሚባሉ አባት ከቅዱስ ያሬድ ቀጥለው በዚሁ ቦታ አስተምረዋል። ዘመኑ በትክክል ባይታወቅም ከገዳሙ ግቢ ውስጥ ወጥተው ከተራራው ሥር ብዙ አባቶች ሲያስተምሩ ቆይተዋል። በ1956 ዓ.ም. በጊዜው የጋይንት አውራጃ አስተዳዳሪ በነበሩት በደጀአዝማች ገሠሠ ረታ አማካይነት ከጀርመን መጥተው ገዳሙን የጐበኙት አንድ በጎ አድራጊ ነበሩ። እኚሁ ጀርመናዊ ለዘመናዊ ት/ቤት ባሠሩት ቤት ውስጥ የዝማሬ መዋሥዕት አድራሽ ተማሪዎች ይማሩ ነበር። በ1974 ዓ.ም. በአዲስ መልክ ቢያሠሩትም ዘመናዊ ትምህርቱ መቀጠል ስላልቻለ ለዝማሬ መዋሥዕት አድራሽ ተማሪዎች መማሪያ እና መኖሪያ ሆኖአል። ሕንፃው በድንጋይ የተሠራ ሲሆን ስድስት /6/ ክፍሎች አሉት። አንዱ የዝማሬ መዋሥዕት አድራሾች መማሪያ፣ ሦስት /3/ የመኝታ ክፍሎች፣ አንዱ በመደበኛ ለሕፃናት የፊደል ሥርዓት ትምህርት መማሪያ እና አንዱን የዕቃ ቤት አድርገው ይጠቀሙበታል። እኚሁ በጎ አድራጊ ለሠላሳ ስድስት /36/ ተማሪዎች በወር አሥር ብር /10ብር/፣ ላሉት ሦስት መምህራን ለእያንዳንዳቸው በወር አንድ መቶ ሃያ /120/ ብር ይልኩላቸዋል።

አሁን ያሉት መምህር መሪጌታ ጓንጉል ከ1955 ዓ.ም. ጀምሮ በማገልገል ላይ ይገኛሉ። እርሳቸው ማስተማር ሲጀምሩ በግምት ሃያ /20/ ተማሪዎች ብቻ ነበሩ። አሁን ግን ከስልሳ እስከ ሰባ /60 – 70/ የሚደርሱ ተማሪዎች ይገኛሉ። ሁሉም ትምህርቱን የሚማሩት በአንድ ክፍል ውስጥ ሲሆን ዙሪያውን አድራሽ ተማሪዎች ክብ ሠርተው መምህራቸውን መሐል አድርገው ይቀመጣሉ። ተረኛው አድራሽ ተማሪ ፊት ለፊት በመቆም የራሱን መጽሐፍ ይዞ የዕለቱን ትምህርት በዜማ ያደርሳል። ከዚያ ዙሪያውን የተቀመጡት ተማሪዎች የሱን ዜማ ከመጽሐፋቸው በመከታተል እየተቀበሉ በአንድ ላይ ያዜማሉ። በመሐል በዜማ ላይ ስህተት ካለ ክርክር ይፈጠራል። ከየአድራሾቹ የተለያየ ሐሳብ ይቀርባል። በመጨረሻ መምህራቸው በሚሰጡት ሐሳብ ይስማሙና ስህተቱ ይታረማል። ሁሉም አድራሽ ተማሪዎች በእንዲህ ዓይነት ተራ እየደረሳቸው ትምህርቱ ይቀጥላል። ተማሪዎቹ አስመስክረው ለመውጣት የሚፈጅባቸው ጊዜ አንድ ዓመት ከስድስት ወር ሲሆን በዚህ ጊዜ ውስጥ አጠናቆ ያልጨረሰ ተማሪ ወደ መጣበት በመሔድ ትምህርቱን እንደገና አጥንቶ እንዲመጣ ይደረጋል። ተመልሶ ሲገባ ከተማሪዎቹ ጋር ከበጎ አድራጊዎች የሚሰጠው ርዳታ ተካፋይ አይሆንም። የራሱን ቀለብ ይዞ ይመጣል። በትምህርቱ ቤቱ ያሉት አድራሾች አብዛኞዎቹ መሪጌቶች ሲሆኑ ከተለያዩ የአብነት ት/ቤቶች አስመስክረው የመጡ ናቸው። አድራሽ ተማሪዎቹ በሚያገኙት የበጎ አድራጊዎች ገንዘብ እና ከቤተሰብ በሚያመጡት ቀለብ የሚተዳደሩ ናቸው።

በአካባቢው ወንበር ተክለው የሚያስተምሩ ብዙ መምህራን ሲኖሩ መምህር ውሂብ ሥላሴ /የገዳሙ አበምኔት/ ዳዊትና ንባብ፣ መሪጌታ ፈንታ አፈወርቅ ድጓ፣ ጾመ ድጓ፣ የዳዊትና የመጽሐፍ ንባብ መሪጌታ ዘርዐ ዳዊት ያስተምራሉ። ሦስቱም ሊቃውንት ከጀርመን በጎ አድራጊ በወር መቶ ሀያ ብር ለእያንዳንዳቸው ድጐማ ይደረግላቸዋል። በኢትዮጵያ ብቸኛ የሆነው ይህ የዝማሬ መዋሥዕት ማስመስከሪያ ትምህርት ቤት ምንም /ወደ ገጽ 15 ዞሯል/

# ንጉሠ ነገሥት ቅዱስ ይምርሐነ ክርስቶስ

ግርማ ኤልያስ

ኢትዮጵያ ሀገራችን ከጥንት ታሪኳ ጀምሮ በእግዚአብሔር የሚያምን ሕዝብ፣ እግዚአብሔርን የሚፈሩ ነገሥታት፣ ምእመናንን የሚያስተምሩና ቤተ እግዚአብሔርን የሚያገለግሉ ካህናት አሳጥቷት አያውቅም:: ከዚያም አልፎ በመንግሥታቸው ሕዝባቸውን እያስተዳደሩ ጎን ለጎንም እንደ አንድ ሐዋርያ እምነተ ክርስትናን ተቀብለው፣ ወንጌልን በመስበክ፣ አረማውያንን በማስተማር እና በማጥመቅ፣ አብያተ ክርስቲያናትን በመትከል ለክርስቲያናዊ እምነት መስፋፋት ባደረጉት እጅግ በጣም የላቀ አስተዋጽኦ ከንጉሥነት ወደ ቅዱስነት የተሸጋገሩ ኢትዮጵያውያን ነገሥታት ቁጥራቸው ጥቂት አይደለም::

ከእነዚህም መካከል ለመጀመሪያ ጊዜ ክርስትናን በመንግሥት ደረጃ ተቀብለው ግንባር ቀደም ሰባክያን በመሆን ቀዳሚ ድርሻ ያላቸው ቅዱሳን ነገሥት አብርሃ ወአጽብሃ ናቸው :: በመቀጠልም ቤተ ክርስቲያናችን በቅድስና የመዘገበቻቸው አፄ ካሌብና አፄ ገ/መስቀል በዘመነ አክሱም ከነገሥታቱ በናሙናነት የሚጠቀሱ ናቸው::

ለሺ ዘመናት የተገነባው የአክሱም ዘመነ መንግሥት የሥልጣኔ ውጤት የነበሩት ሐውልቶች፣ አብያተ መንግሥት፣ አብያተ ክርስቲያናት እና ከተሞች፤ አረማዊቷ ዮዲት ጉዲት ባጠፋቻቸው ማግስት በአሥራ ሁለተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ አካባቢ በከፍተኞቹ የላስታ ተራሮች ዙሪያ ብቅ ያለው የዛጉዬ ሥርወ መንግሥት በአዲስ መንፈስ ተነሣሥቶ በዘመነ ጉዲት የወደሙትን አብያተ ክርስቲያናት እንደገና በማደስ ፣ የራሱ የሆኑ አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናትንም በጥርብ ድንጋይ እና እንጨት በማሠራት እና ጠንካራ ዐለትን ፈልፍሎ ግሩም ድንቅ የተባለላቸውን አብያተ ክርስቲያናት አንፆ አልፎአል::

ይህን ታላቅ ትውፊት አውርሰውን ካለፉት ቅዱሳን ነገሥታት መካከል አንዱ እና ግንባር ቀደም ተጠሪው ቅዱስ ይምርሐነ ክርስቶስ ይባላል:: ቅዱስ ይምርሐነ ክርስቶስ ዘውድ ደፍቶ ቅብዐ መንግሥት ተቀብቶ በኢትዮጵያ የነገሠ ይሁን እንጂ በሕይወት ዘመኑም ሆነ በዘመነ መንግሥቱ የፈጸማቸው ነገራት በሙሉ መንፈሳዊ ተግባራት ናቸው:: ቤተ ክርስቲያንን ከማስፋፋት ተግባር የተቆጠበበት ዘመን የለም::

የቅዱስ ይምርሐነ ክርስቶስ የትውልድ ዘር እንዲህ ነው:: የመጨረሻው የአክሱም ሥርወ መንግሥት ተብሎ የሚታወቀው አፄ ድልነአድ መሰበ ወርቅን ይወልዳል:: መሰበ ወርቅ መራ ተ/ሃይማኖት የተባለውን የቡግና ባላባት ልጅ አግብታ ይርጋ ሥዩምን፣ ዣን ሥዩምን፣ግርማ ሥዩምን፣ ትርድዓን ገበዝን ትወልዳለች:: ግርዋ ሥዩምም ይምርሐነ ክርስቶስን ይወልዳል:: ከነዚህ መካከል የግርማ ስዩም የበኩር ልጅ የሆነው ጠንጠውድም የተባለው በነገሠ ጊዜ ከሱ በኋላ መንግሥቱን የሚወርስ ማን እንደሆነ ኮከብ ቆጣሪዎችን እና ጠጠር ጣዮችን ጠርቶ ጠየቀ:: እነሱም የወንድምህ የግርማሥዩም ልጅ ይምርሐነ ክርስቶስ የሚባል ልጅ መንግሥትህን ይወርሳል ሲሉ ነገሩት::

አፄ ጠንጠውድም የወንድሜ ልጅ እንዴት ይወርሰኛል? ብሎ ሰይጣናዊ ቅንዓት አደረበት:: ይምርሐነ ክርስቶስን አባቱ በሕፃንነቱ ስለሞተ እናቱ እየተንከባከበች ታሳድገው ነበር:: ወታደሮቹን ልኮ «ልጅሽ የወንድሜ ልጅ በመሆኑ ገና ከልጅነቱ ፈረስ ግልቢያ፣ ጦር ውርወራ፣ የባሕር ዋና እየተማረና የቤተ መንግሥትን ሥነ ሥርዓት እየተከታተለ እንዲያድግ ወደኔ ላኪው» የሚል መልእክት አስይዞ ላከባት:: የቅዱስ ይምርሐነ ክርስቶስ እናትም የበቁ ገዳማውያንን አማከረች:: «ልጅሽ የተባረከ መንግሥትም ክህነትም ይዞ ኢትዮጵያን የሚመራ ነው፤ እና አጎቱ በቅንዓት እንዳይገድለው ወደ አጎቱ ቤተ መንግሥት እንዳትልኪው» የሚል የተቀደሰ ምክር ሰጧት:: የጠንጠውድም ወታደሮች ወደ እርሷ በመጡ ጊዜ ወታደሮቹ ከመድረሳቸው በፊት ልጇን ማንም ከማይደርስበት ደብቃ «ልጄ ጠፋ ልጄ ሞተ» እያለች እሪታዋን እያለቀቀችው ጠበቀቻቸው:: መሠሪ ዓላማ ይዘው የመጡት ወታደሮች ልቅሶዋንና እሪታዋን አመኑ:: ይምርሐነ ክርስቶስ ጠፋ ብለው ወደ ቤተ መንግሥታቸው ተመለሱ::

መንፈስ ቅዱስ ያማከራት የይምርሐነ ክርስቶስ እናትም ልጇን ወደ ሩቅ ሀገር ላከችው:: መንፈሳዊ ትምህርት እየተማረ አደገ:: ቅዱስ ይምርሐነ ክርስቶስ ነፍስ እያወቀ ሲሄድ አጎቱም በሕይወት መኖሩን አውቆ እንዳይገድለው በ17 ዓመቱ ወደ ግሪክ ሀገር እንዲሄድ አደረገች:: በዚያ ለብዙ ዓመታት ሲኖር የግሪካውያንን የግብረ ሕንፃ ጥበብ፣ የሥዕል እና ቅርፃ ቅርፅ ሙያ እንደዚሁም ብሉያትን እና ሐዲሳትን ተማረ:: እንዲሁም ቅዱሳት መካናትን በመሳለም በሮም እና በኢየሩሳሌም እየተዘዋወረ ለ40 ዘመናት ያህል ቆይቶ በ57 ዓመቱ በኢየሩሳሌም ከሚገኙት ቅዱሳት መካናት በአንዱ ተቀምጦ የወደፊቱ እጣ ክፍሉ ምን እንደሆነ ፈጣሪው እንዲገልፅለት ሱባኤ ገባ:: ይህ ፃደተኛ ካህን ይምርሐነ ክርስቶስ «እግዚአብሔር ወሀቤ ብርሃን» የተባለውን ጸሎተ ኪዳን እየደገመ ከሚጸልይበት ወቅት እግዚአብሔር ተገለጸለት:: «ወደ ሀገርህ ተመልሰህ ሒድ፤ ሀገርህ እንደደረስህ ቅብዓ መንግሥት ተቀብተህ ካህንም ንጉሥም ሆነህ ኢትዮጵያን በሰላም እና በደስታ ትመራለህ:: ስመ መንግሥትህም ዳዊት የሚል ይሆናል» በማለት መጪው ዕድሉን አበሰረው:: ቅዱስ ይምርሐነ ክርስቶስ ግን «ካህንም ንጉሥም መሆን እንዴት ይቻላል?» ሲል ጠየቀ:: መንፈሰ እግዚአብሔርም «ሁለቱም ላንተ የተሰጡ ሀብቶች ስለሆኑ እኔ ባርኬ መርቄ ሁሉንም በየመልኩ እንዲገዙልህ አደርግልሃለሁ እና ወደ ሀገርህ ተመልሰህ በሰላም ግባ» ሲል አሰናበተው::

ቅዱስ ይምርሐነ ክርስቶስ በኃይለ እግዚአብሔር ሀብተ ክህነት እና ሀብተ መንግሥት ተጎናፅፎ በ57ኛው ዓመቱ ወደ ቅድስት ሀገሩ ኢትዮጵያ ተመለሰ:: ወደ ቅድስት ሀገሩ እንደተመለሰ ያ በልጅነቱ አንቆ ሊያጠፋው አልሞ የነበረው አጎቱ ጠንጠውድም ወይም ስመ መንግሥቱ አፄ ሰሎሞን ገና በሥልጣነ መንግሥት ላይ ነበረ:: ቅዱስ ይምርሐነ ክርስቶስ የትንቢት ዘመናት እስኪፈጸሙ ድረስ በሰሜን ኢትዮጵያ የሚገኙትን የቅዱሳን ገዳማት፣ መቃብረ አበውና ታላላቅ መንፈሳዊ ት/ቤቶችን እየተዘዋወረ በመጎብኘት ለአንድ ዓመት ያህል ቆየ:: ኢትዮጵያን በመንግሥትነት ይመራ የነበረው ጠንጠውድምም ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ:: ቅዱስ ይምርሐነ ክርስቶስ ወደ ቡግና በመምጣት በዛሬዎቹ ቅዱስ ይም

ርሐነ ክርስቶስ ገዳምና ብልበላ ቅዱስ ጊዮርጊስ መካከል ከምትገኝ ዛዚያ ከተባለች ቦታ ታላቅ ድንኳን ተክሎ መናገሻ ከተማ በማድረግ፣ ዘውድ ደፍቶ፣ ቅብዐ መንግሥት ተቀብቶ ነገሠ:: እንደ አበው አባባልም «ዛዚያ» «ዝየ ስመርኩ መንፈስየ» መንፈሴ ይህንን ቦታ ወደደች ማለት እንደሆነ ይናገራሉ::

ቅዱስ ወንጉሥ ይምርሐነ ክርስቶስ ዛዚያ ከተባለችው መናገሻ ከተማው ቤተ መንግሥት ሳይሠራ ይህንን ዓለም ጊዜያዊ፣ ኃላፊና ጠፊ መሆኑን ተገንዝቦ ለ22 ዓመታት ያህል በድንኳን ውስጥ ተቀምጧል:: ብሔረ ኢትዮጵያን ንጉሥ ሆኖ በማስተዳደር፤ ካህን ሆኖ ሥርዓተ ቅዳሴን በመፈጸም እና ሥጋወ ደሙን በመፈተት፣ መንፈሳዊና ሥጋዊ ተግባራትን አከናውኗል:: በዚህ ሁኔታ እንዳለ በድጋሚ እግዚአብሔር ተገልጾ «ወዳጄ፣ አገልጋዬ ይምርሐነ ክርስቶስ፣ ገና በኢየሩሳሌም ሳለህ ወደ ሀገርህ ተመልሰህ ትነግሣለህ፤ ስሜ የሚቀደስበት ያንተም ስም ለዘለዓለም የሚዘከርበትን ቤተ ክርስቲያኔን ታንፃለህ፤ ብዬ ነግሬህ ነበር:: አሁንም የኔ ቤት ገና ስላል ታነፀ አሁን ካለህበት ቦታ ተነሥተህ ወደ ፀሐይ መውጫ ሂድና እኔ በምገልጽልህ ቦታ ቤተክርስቲያን ታንፃለህ» በማለት ነገረው::

ቅዱስ ይምርሐነ ክርስቶስም በነገሠ በ22 ዓመቱ በተወለደ በ79 ዓመቱ በአሁኑ ወቅት በስሙ ወደሚታወቀው ዋሻ ሂዶ በራዕይ የተገለጸለትን ዋሻ ፍለጋ ጀመረ:: ይህንን እግዚአብሔር በጥበቡ ሰውሮ ያስቀመጠውን እና ለንቋጣ በተባለ ሐረግ ተሸፍኖ ክረምት ከበጋ የማይነጿጿ የጸጋ ምንጭ ፏፏቴ የማይቋረጥበትን ዋሻ አገኘው:: አሁንም እግዚአብሔር እንደገና ተገልጸለት:: «ኢየሩሳሌም ሳለህ የገለጽኩልህ ምሥጢር ይህ ዋሻና ባሕር ነው:: ደኑን መንጥረህ በባሕሩ ላይ እንጨት ረብርብበት:: በእንጨቱም ላይ ሣር አንጥፍበት:: በሣሩ ላይ ድንጋይ ረብርብበት:: በድንጋዩም ላይ እንጨቱን ከምድረ ገነት በነፋስ ጭነው የሚያመጡልህ ትጉህን መላእክትን አዝዤልሀለሁ እና ያልኩህን ፈጽም» በማለት በራዕይ ገለፀለት::

ቅዱስ ይምርሐነ ክርስቶስ በራዕይ በተነገረው መሰረት መስከረም 13 ቀን የዚያችን ግሩም ድንቅ የዋሻ ቤተ ክርስቲያን ሕንፃ ሥራ ጀመረ:: ሰኔ 20 ቀን የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምና አዲሲቱ የይምርሐነ ቤተ ክርስቲያን ህንፃም በልዩ ጥበብ በተጠረቡ ድንጋዮች፣ እምነበረድ፣ ጥርብ እንጨት፣ አልማዝ እና ዕንቁ ደምቃና አሸብርቃ ሥራዋ ተጠናቀቀ::

ቅዱስ ይምርሐነ ክርስቶስ የአዲሲቱን ቤተ ክርስቲያን ሕንፃ ሥራ ከፈጸመ በኋላ ሰኔ 20 ቀን ሕንፀተ ቤትዋን ቅዳሴ ቤቷን በታላቅ ድምቀትና ክብር በሚያከብርበት ዕለት ራሱ ገባሬ ሠናይ ሆኖ አሐዱ አብ ቅዱስ አሐዱ ወልድ ቅዱስ አሐዱ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ» ብሎ በሚቀድስበት ወቅት ከሰማየ ሰማያት ኅብስተ ሕይወትና ጽወዐ ሕይወት ወርዶለት ሥርዓተ ቅዳሴውን ፈጸመ:: ምእምናንንም አቆረበ:: ከዚህ በኋላ 18 ዓመታት ሙሉ በሰማያዊ ሕብስትና ጽወዐ ሕይወት ከሰማየ ሰማያት እየወረደለት ቀድሷል::

ቅዱስ ይምርሐነ ክርስቶስ እንደ ንጉሠ ነገሥት የሀገር መሪና አስተዳዳሪ እንደ ካህን ቀዳሽ መካሪና አስተማሪ፤ እንደ መሐንዲስ ግንበኛ፣ አናጺና ቤተ ክርስቲያንን በዕንቁና በአልማዝ አሳማሪ ሆኖ ኖረ:: የሱን ልዩ ስብእናና ቅዱስ ዜና የሰሙ የእስክንድርያ ፓትርያርክና ሊቀ ጳጳሳት፣ የሮምና የኢየሩሳሌም ሊቃነ ጳጳሳት፣ ታላቅ አድናቆትና ፍቅር አደረባቸው:: የዚህን ቅዱስ ካህንና ንጉሥ ተአምራታዊ ተግባር ለማየትም ከሮምና ከእስክንድርያ የተወጣጡ 5700 ሮማውያንና ግብፃውያን በረሃውን አቋርጠው ወደ ኢትዮጵያ መጡ:: ከቅዱስ ይምርሃነ ክርስቶስ ጋር ተገናኝተው «ለምን መጣችሁ?» ቢላቸው «ዜናህንና ተአምራትህን ሰምተን መጣን» አሉት:: እሱም ሥርዓተ ቅዳሴ አዘጋጅቶ፤ አሐዱ አብ ቅዱስ ብሎ ሲቀድስ መልአኩ ኅብስተ ሰማይ ይዞ ሲያቀብለው በወቅቱ ለነበሩት 5700 ሮማውያንና ግብፃውያን ተገለጸላቸው:: ከሰማየ ሰማያት የወረደውን ቅዱስ ሥጋውና ክቡር ደሙን በቅዱስ ይምርሐነ ክርስቶስ እጅ ተቀበሉ:: አባ አትናቴዎስ እና አባ ያዕቆብ በሚባሉ ጳጳሳት የሚመሩት ግብፃውያንና ሮማውያን «ከአሁን ወዲያ ሰማያዊ ኅብስት ተቀብለን ወደ ሀገራችን በመመለስ ዳግም ምድራዊ ኅብስት ለመቀበል አንሄድም» አሉ:: ቅዱስ ይምርሐነ ቤተ ክርስቲያን ባነፀበት ዋሻ ሁሉም በአንድ ጊዜ ተኝተው እህል ውኃ በመተው ገድላቸውን ፈጸሙ:: የነዚህ መናንያን አፅም /አስከሬን/ አካለ ሥጋቸው ከአጥንታቸው ሳይለይ እንደተጋደሙ ለትንግርት ያህል እስከ ዛሬ ድረስ ይታያል::

ቅዱስ ይምርሐነ ክርስቶስ ቤተክርስቲያኒቱን ሲሠራ ሦስት ቤተ መቅደስ አድርጎ ነው:: የእመቤታችን ቤተ መቅደስ በፀሐይና በጨረቃ አምሳል፣ የታቦተ ይምርሐነ ክርስቶስ ቤተ መቅደስ በጽርሐ አርያም አምሳል፣ የታቦተ ጊዮርጊስ ቤተ መቅደስ በንጋት ኮከብ አምሳል አድርጎ አንፆአቸዋል::

የቤተ ክርስቲያኒቱን ቅድስትና ማኅሌት በሰባቱ ሰማያት ምሳሌ አድርጎ በሥዕል ፣በሐረግና በልዩ ቅርፅ አስጊጦአቸዋል:: ኢዮር፣ ኤረር፣ ራማ፣ኢየሩሳሌም ሰማያዊት ፣ሰማይ ውዱድ መንበረ ጸባዖት፣ ጽርሐ አርያም በማለት በቀስተ ደመናዊ ቅርፅ ለያይቷቸዋል:: በተለይም የቅዱስ ይምርሐነ ክርስቶስ ታቦት ያለበት ቤተመቅደስና ከፊት ለፊት ያለው የቅድስተ ቅዱሳን አምሳል በጽርሐ አርያም ምሳሌ እንደ ፀሐይና ጨረቃ፣ እንደ ከዋክብት የሚያበሩ መስቀላትን፣ የማኅተም ቅርፆችን ቀንና ሌሊት የሚያበሩ የከበሩ ዕንቁዎችና የአልማዝ ፈርጥ ያለበት መቅረዝ አበጅቶለታል::

ቅዱስ ይምርሀነ ክርስቶስ ይህችን ቤተ መቅደስ አንፆ ከፈጸመ በኋላ ከፈጣሪው ዘንድ ምንጊዜም የማይሻር ቃል ኪዳን ተሰጥቶታል:: «በዚህ ቅዱስ ቦታ ደርሶ የተሳለመ፣ በደብሩ ካህን ሆኖ ያገለገለ፣ በቦታው የተቀበረ፣ ከልጅነት እስከ ዕውቀት የሠራው ኃጢአት እንዲደመሰስ ስለት ፣ዕድሜው እንዲረዝምለት፣ የወለደው እንዲያድግለት፣ የዘራው በረከት ረድኤት እንዲያድርበት በመጨረሻም ከዚህ ዓለም ሲለይ ቅዱስ ይምርሐነ ክርስቶስ በገባበት መካነ ዕረፍትና መንግሥተ ሰማያትን አወርሰዋለሁ» በማለት ቃል ኪዳን ተቀብሎአል:: በዘጠና ሰባት ዓመቱ ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ:: ባነፃት ቤተመቅደስ በስተምሥራቅ በኩል በክብር ተቀበረ:: መካነ መቃብሩም እስከ ዛሬ ድረስ ከመላው ኢትዮጵያ የሚመጡትን ሕሙማንን ሲፈውስ ይኖራል::

ቅዱስ ይምርሐነ ክርስቶስ በመንግሥታዊ ሥልጣኑ ከፈፀማቸው ታላላቅ ተግባራት መካከል፤ ከእስክንድርያ በወርቅ እየተገዙ የሚመጡትን ባዕዳን ጳጳሳት ለማስቀረት ሲል 12 ኢትዮጵያውያን ኤጲስ ቆጶሳትን አስመርጦ ለማዕረግ ጵጵስና እንዲበቁ ብዙ ጥረቶችን አድርጓል:: በዮዲት ጉዲት አማካይነት ተቋርጦ የነበረው ክርስቲያናዊ ሥነ ጥበብ፣ ግብረ ሕንፃና፣ ሥነ ጽሑፍ እንዲቀጥል አድርጓል:: በመላ ኢትዮጵያ ተስፋ ቆርጠውና ተዳክመው የነበሩትን የሥነ ጥበብ ሰዎች አሰባስቦ እስከ ዘመናችን ድረስ በሥዕሏና በቅርጿ ወደር ያልተገኘላትን አሁንም ያለች ደብረ ወግረ ስሒን ይምርሐነ ክርስቶስ ሕንፃ አሁን ላለው ትውልድ አስረክቦ አልፏል::

በተለይም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የሥዕል ታሪክ ዕድገትና መስፋፋትን በተመለከተ፤ ምዕራባዊው የቤተ ክርስቲያኒቱ ቅድስት ገጽ ላይ ተሥለው የሚገኙት፤ የቅድስት ድንግል ማርያም ስደት፣ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በበዓለ ሆሳዕና፤ ሥርዓተ ቀርባን፣ የግርፋቱን፣ የኩርዓቱን፣የስቅለቱንና የሞቱን፣ የትንሣኤውንና የዕርገቱን ምሳሌ የሚገልፁ ሥዕሎች ተቀምረውና በልዩ የሥዕል ጥበብ ተቀነባብረው መገኘታቸው የምንመካበትና የምንኮራበት በመሆኑ ልንከባከበውና ልንጠብቀውም የሚገባ ታላቅ ቅርሳችን ነው::

የደብረ ወግረ ስሒን ይምርሐነ ክርስቶስን አጠቃላይ ገፅታ በዓይነ ኅሊና ለመጐብኘት ያህል፤ 4196 ሜትር ከባሕር ጠለል በላይ ከፍታ ካለው ታላቁ የአቡነ ዮሴፍ ተራራ ምዕራባዊ መካከለኛና ወይና ደጋማውን አግድመት ተንተርሳ የምትገኝ አረንጓዴ ለበስ ተራራ ላይ የተመሠረተች ጥንታዊት ገዳም ነች:: በየአቅጣጫው በሚፈልቁት ምንጮችና ወንዞች ተከባለች:: መዓዛቸው መንፈስን የሚያድስ ልዩ ልዩ አረንጓዴ ተክሎች፣ የጥድና የወይራ ዛፎች ምድረ ገጹን ከቆላማው የብልብላ አካባቢ ጀምሮ በስተ ምሥራቅ አቅጣጫ ወደ ይምርሐነ ገዳም ሲወጡ የአካባቢው ውበት ይማርካል:: ይህንን ተፈጥሮና የተቀደሰ ውብ ሥፍራ እንዲሁም በሥነ ጥበብ ያሸበረቀችውን ጥንታዊት ቤተ ክርስቲያን መጐብኘት ምንጊዜም ከኅሊና የማይፋቅ መንፈሳዊ ጸጋ ተቀዳጅቶ መኖር ነው::

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር*

# የዘመኑ ወጣት እና የአብነት ትምህርት - ተፈላላጊ

/አቡጊዳ/

የደስታ ተክለ ወልድ የአማርኛ መዝገበ ቃላት መጽሐፍ አብነት የሚለውን ቃል አባትነት፣ አባት መሆን፣ምሳሌነት፣ መምርነት፣ ፍቱን መዳኒት በማለት ይፈታዋል:: እነዚህ በቃሉ መፍቻነት የተደረደሩት ቃላት ተመሳሳይነት አላቸው:: ሁሉም ታላቅነትን፣ ተፈላጊነትን፣ ዋናነትን /ዐቢይነትን/ የሚገልጡ ናቸው:: ስለዚህ ከዚህ ተነሥተን የአብነት ትምህርትን የዕውቀቶች ሁሉ ታላቅ፣ ዋና፣ ተፈላጊ ትምህርት ብለን ልንበይነው እንችላለን:: አንድም «የአሥራው፣ የአባትነት፣ የመምህርነት፣ የምሥክርነት ትምህርት ማለት ነው::» /ሐመር 9ኛ ዓመት ቁጥር 3፣ገጽ 28/

የጸጋ ግምጃ ቤት የሆነች ቤተ ክርስቲያናችን ዕውቀቶቿን በየዓይነቱ /ትርጓሜ፣ ዜማ፣ ቅኔ/ አሰናድታ ለልጆቿ ስትመግብ ኖራለች፣ አሁንም እየመገበች ነው፣ ወደ ፊትም ትመግባለች:: እናታቸው ምንም የማይጐድላት ስንዱ እመቤት መሆኗን የተረዱ ልጆቿን ሰብስባ ዕውቀት በየዓይነቱ እየመገበች የምታፋፋባቸው ዐውደ ጥበባት ደግሞ የአብነት ት/ቤቶች ይባላሉ::

የዚህ ጽሑፍ ርዕስ «የዘመኑ ወጣት እና የአብነት ትምህርት ተፈላላጊ»ነው:: በዚህ ደረጃ ደግሞ ርዕሱን እንዲህ እንግለጠው:: የዘመኑ ወጣትና የአብነት ትምህርት በእጅጉ ተፈላላጊዎች ሆነዋል:: አሁን ባሉበት ሁኔታ አፍን ሞልቶ ተገናኝተዋል ማለት አይቻልም:: ሁኔታዎች በዚሁ ከቀጠሉ የሚገናኙም አይመስሉም::

ለመሆኑ ወጣቱ የአብነት ትምህርት በመማሩ የሚያገኘው ጥቅም ምንድን ነው? ጥቅሞች ናቸው የሚባሉትን ከብዙ በጥቂቱ እንደሚከተለው እናያለን::

ሀ. ቤተ ክርስቲያን በምትፈጽማቸው አገልግሎቶች ለመሳተፍ

ቤተ ክርስቲያናችን ሳትታክት ጠዋት ማታ ልጆቿን እየሰበሰበች በደሙ ለዋጃት እግዚእ ኢየሱስ ክርስቶስ ልዩ ልዩ የስብሐት አምኃዎች ታቀርባለች:: ቅዳሴ፣ ማኅሌት፣ ሰዓታት፣ ኪዳን ወዘተ:: እነዚህ የስብሐት አምኃዎች የየራሳቸው መልክና ልክ ያላቸው፣ ቀመራቸውንም ተወካፌ ስብሐት የሆነው ራሱ የሠራዊት ጌታ ልዑል እግዚአብሔር ለልጆቿ በልዩ ልዩ መንገድ የገለጠላቸው ናቸው:: በመሆኑም

**ልጆቼ፣ እናንተ ድልድዮች ናችሁ:: ያውም ብዙ ከባድ ነገር በላያችሁ ተሸክማችሁ ማሳለፍ ያለባችሁ ድልድዮች:: ከእናንተ በፊትም ሆነ በኋላ የሚሠራው ድልድይ የእናንተን ያህል ከባድ ነገር አይሸከምም:: እናንተ ዝላችሁ ሸክሙን መሸከም ካልቻላችሁ ብዙና ከባድ የሆነውና ከእናንተ አልፎ ዓለምን የሚጠቅመው ነገር ወደሚወርደው ወንዝ ወድቀ፣ ላይመለስ ላታገኙትም በውሃ ተወሰደ ማለት ነው:: ስለዚህ አንዱ ሌላውን ያበርታና ሸክሙን ተሸከሙ::**

ቤተ ክርስቲያናችን እነዚህን ፈርጀ ብዙ የስብሐት አምኃዎቿን ሊቃውንት ልጆቿን አሠማርታ፣ ጉባኤ ዘርግታ፣ ተቋማትን ከፍታ ለተተኪዎች እንዲተላለፉ ታደርጋለች:: በእነዚህ ተቋማት ታቅፎ ጉባኤያቱ የሚጠይቁትን ያህል ጊዜ ቆይቶ ጠንቅቆ በመማር የወጣ ወጣት አንድም ቤተ ክርስቲያኑን በእሷም በኩል ምሥጋና የባሕርይው የሆነውን እግዚብሔርን ያገለግላል::

ዛሬ በርካታ ወጣት የቤተ ክርስቲያን ልጆች በልዩ ልዩ የስብሐት ሰዓታት በተለይ በቅዳሴ ጊዜ ወደ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የሚሄዱበት ወኔ ሳያጡ ሄደው እንደሥርዓቱ ከቆሙ በኋላ ለሚቀርበው ስብሐት ባይተዋር ወይም ተደናጋሪ ሲሆኑ ይታያሉ:: ቅንዓታቸው ጕልምሶ እንሳ ተፍ እንኳ ቢሉ አንድም መሠረታ ዊውን የዜማ ይትበሃል ተከትለው በግላቸው የሚቀምሯቸውን ዜማዎች ያዜማሉ፤ ካልሆነም በሰፈር፣ በት/ቤት ወደውም ይሁን በግድ በሚሰሟቸው ዓለማዊ ዜማዎች የታጀለ ስብሐተ እግዚአብሔር ሊያቀርቡ ይዳዳቸዋል::

የዚህ ሌላው አብነት ከመሠረታውያኑ የቤተ ክርስቲያናችን የስብሐት /የዜማ/ ዓይነቶች ውጭ ወጣቶች በየሰንበት ት/ቤቶቻቸው የሚያዜሟቸው መዝሙራት ናቸው:: ትክክለኛውን የያሬዳዊ የዜማ ቀመር ተከትለው የሚዜሙ መዝሙራት የመኖራቸውን ያህል በጥንቃቄ ለሚሰማቸው በመንፈሳዊ ቃላትና ሐረጋት የተቀናበሩ ቅልጥ ያሉ ዘፈኖች ናቸው::

ከዓመት በፊት «ይሰግዱ ለኪ ይሰ ግዱ ለኪ ወይትመሀለሉ በቅድመ ገጽኪ» የሚለውን «መዝሙር» በአንድ የቅዱስ ገብርኤል የንግሥ በዓል ላይ ቆሞ የሰማ አንድ ወዳጄ «ወይ አልማዝ፤ መልኳን ቀይራ መጣችሳ?» ብሎ ያሳቀኝን አልረሳውም:: «አልማዝ ምንዕዳ ነው» የሚለውን ዘፈን ማለቱ ነው::

ከላይ እንደተባ ለው፤ ወጣቱ ለማኅሌቱ፣ ለሰዓታቱ፣ ለቅዳሴው ወዘተ. ባይተዋር መሆን፣ በሰፈር ከጐረቤቶቻቸው የሚሰሟቸው ዘፈኖች መልካቸውን ቀይረው ቤተ ክርስቲያን ገብተው ሲያገኟቸው በንቃትና በቅል ጥፍና ከቅጽረ ቤተ ክርስቲያን የሚያስወጡበትን ወኔ ያጡት መጀመሪያውኑ የቤተ ክርስቲያንን የዜማ ስልት ከሌላው የሚለዩበትን ዕውቀት ባለመቅሰማቸው ነው:: ስለዚህ የወጣቶች የአብነት ትምህርት፤ ከዚህ ርዕስ አንጻርም የዜማውን ዘርፍ በሚገባ ጠንቅቀው መማር እውነተኛውንና አባቶቻችን በረከት ያገኙበትን ስብሐተ እግዚአብሔር ለአምላካቸው በአምኃነት እንዲያቀርቡ ያስችላቸዋል::

### ለ. የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ወደ ቀጣዩ ትውልድ እንዲያልፍ ያደርጋል

ቤተ ክርስቲያን የጸጋ ግምጃ ቤት ስንዱ እመቤት በመሆኗ የምታሳፍርባቸው እንጂ የማታፍርባቸው ልዩ ልዩ የዕውቀት ዘርፎች አሏት:: በዶግማዋ ቅድስት፣ በሥርዓቷ ብቃት፣ በዜማዋ ትባት፣ በቅኔዋ ምጥቀት፣ በፍልስፍናዋ ጥልቀት እኛ ልጆቿ እንኮራለን:: አፍ እናስይዛለን እንጂ አፋችንን አንይዝም::ዓለም ዕውቀት ሲሻ ወደእኛ ይገሰግሳል እንጂ እኛ ሃይማኖታዊ ዕውቀት ፈልገን ወደ ዓለም አንሄድም:: በጥቅሉ አብነቶች ተጠያቂዎች ነን:: ይህ በዚህ ሁኔታ ሲታሰብ የሚያስደስተንን፣ የሚያስፈነድቀንን ያህል የዚህ ኩራትና ፍሥሐ ምንጭ የሆኑት ልዩ ልዩ የዕውቀት ዘርፎች የሚረከባቸው እየጠፋ ከሊቃውንቱ ጋር ወደ መሬት እየገቡ፣ በመጻሕፍት ያሉትም ብልና ውሃ እያወደማቸው መሆኑን ስንረዳ በሀዘን አንገታችንን እንደፋለን::

እዚህ ላይ የአንድን አባት ምክር መጥቀስ ይገባል:: እኒህ አባት በአንድ የወጣቶች ጉባኤ ላይ ተገኝተው «ልጆቼ፤ እናንተ ድልድዮች ናችሁ:: ያውም ብዙ ከባድ ነገር በላያችሁ ተሸክማችሁ ማሳለፍ ያለባችሁ ድልድዮች:: ከእናንተ በፊትም ሆነ በኋላ የሚሠራው ድልድይ የእናንተን ያህል ከባድ ነገር አይሸከምም:: እናንተ ዝላችሁ ሸክሙን መሸከም ካልቻላችሁ ብዙና ከባድ የሆነውና ከእናንተ አልፎ ዓለምን የሚጠቅመው ነገር ወደሚወርደው ወንዝ ወደቀ፤ ላይመለስ ላታገኙትም በውኃ ተወሰደ ማለት ነው:: ስለዚህ አንዱ ሌላውን ያበርታና ሸክሙን ተሸከሙ::» ይህ የአባታችን ምክር ለዚህ ትውልድ በውኃዎች ቀለምነት፣ በቅጠሎች ሁሉ ብራናነት፣ በኢትዮጵያዊው ሁሉ ጸሐፊነት ቀን ከሌት ክረምት ከበጋ መታወጅ ያለበት ታላቅ ምክር አንድም ፀዋጅ ነው::

እውነት ነው:: ይህ የዛሬው ወጣት ብዙ ሸክም አለበት:: እኔ እንደገባኝ እኒህ የተከበሩ አባት «ብዙና ከባድ ሸክም» ያሉት ተረካቢ፣ ስፊውንና ጥልቁን ባሕር የሚያሻግረው ድልድይ አጥቶ ሊወድቅና በውኃ ሊወሰድ ያለውን የአብነት ትምህርት ነው:: ዘርፈ ብዙውን የቤተ ክርስቲያን ዕውቀት:: የዛሬው ወጣትም በድልድይ መመሰሉ አባቶቹ በጸሎት በጾምና በመሳሰሉት ተጠምደው በአምላካቸው ኢክናዋኝነት ያቆዩትን ዕውቀት ምንም ነገር ሳይቆነ ጻጸል እሱን ወደሚተካው ትውልድ ማሳለፍ ስላለበት ነው:: መሸከሙም ቢናውዝ ላያገኛቸው [illegible] ካሉት አባቶቹ እግር ሥር ቁጭ ብሎ መማሩን ለማጠየቅ ነው::

በነገራችን ላይ የአባቶችን በልዩ ልዩ ችግሮች በሞት መነጠቅን አስመልክቶም እላይ ምክራቸውን የጠቀስንላቸው አባት ያሉት ነገር አለ:: እንጥቀሰው:: «ሊቃውንት አባቶቻችሁ አመለጧችሁ እኮ ልጆቼ፤ ሕጻናት ሆናችሁ መሰለኝ? ዛሬ ቢሄዱ ነገ የሚመለሱ እየመሰላችሁ ወደማያልቀው መንገድ ሲሄዱ ዝም ብላችሁ ታዩአቸዋላችሁን? ቅረቡና ያሏቸውን ያውርሷችሁ እንጂ? ያደፈ የቆሸሸ ለብሰው ብታዩ አንድም እንደምታውቋቸው ቱጃሮች የታጠበ የተተኮሰ ለብሰው ስላላያችኋቸው ምግባቸው ኮቸሮ መኝታቸው ከጐጆ ሆኖ ብታዩ ድሆች እያላችሁ ትሸሿቸዋላችሁን? ኧረ በእነሱ ያደፈ÷የቆሸሸ÷ጐጆ ውስጥ ብዙ ሀብት አለ:: ሂዱና ያውርሷችሁ እንጂ:: ልጅ ወደ አባቱ ሄዶ አባቴ ያለህን አውርሰኝ ብሎ ይለምናል እንጂ፤ እንዴት አባት ልጁን ልጄ እባክህ ና ላውርስህ ብሎ ያባብላል?»

አስታውሳለሁ:: አባ ይህንን ሲሉ በኃዘንና አንዳች ነገር እያራቀው በሚሄድ ዓይነት ድምጽ ነበር:: እውነት ነው:: ከእኛ የበለጠ የእኛን አባቶች ማንነት የተረዱት ፈረንጆች «የሚራመዱ አብያተ መጻሕፍት–the walking libraries» የሚሏቸውን ዕንቁ አባቶቻችንን ሞት እየተሻማ ወደ መሬት እየከተታቸው ነው:: እኛም በዝምታ እያየን ነው::

ስለዚህ የዛሬው ወጣት የቤተ ክርስቲያን ልጅ ዛሬውኑ ነቅቶ «የድልድይነት» ተግባሩን ከተወጣ ነቅዕ የሌለበት የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ለቀጣዩ ትውልድ ይደርሳል:: አሁን እንደሚታየው ወጣቱ በተለይ ከተሜው ወጣት «ተማሪ ቀንጫ ለቃሚ»ን እያዜመ ከተቀመጠ የሚፈራው አደጋ ከመድረስ ወደኋላ አይልም::

### ሐ. በአንድ ቦታ የተከማቸው የቤተ ክርስቲያን ዕውቀት እንዲናኝ ያደርጋል

ብዙ ጊዜ የአሁኑ ወጣት ለምን የአብነት ትምህርት እንደማይማር ሲጠየቅ የትምህርት ማዕከሎቹ ስለሚርቁ አንድም የተወሰኑ በመሆናቸው እንደሆነ ይናገራል:: በትርጓሜው ጐጃም ዲማ ቅዱስ ጊዮርጊስ፣ ጐንደር መካነ ኢየሱስ፤ በቅኔው ዋድላ፣ዋሸራ፣ ጐንጅ፤ በዜማው ዙር አባ ጽርሐ አርያም ገዳም፣ ሰለልኩላ ቅዱስ ሚካኤል ገዳም በዋናነት ይጠቀሳሉ:: በእነዚህ የትምህርት ማዕከላት የሚሰጡት የአብነት ትምህርቶች ፈልጎ ጠይቆ ለሄደ ካልሆነ በብዛት እንደሚታየው ለሌላው ምእመን አይደረሱም:: በዚህ ቤተ ክርስቲያን የምትወቀስ አትሆንም:: ለአንድ ሀገር ትምህርት አስፈላጊ ነው ቢባልም በየስፈሩ በየጐጡ ዩኒቨርሲቲ እንክፈት አይባልምና:: ስለዚህ ከላይ በተጠቀሱትና በሌሎች ባልተጠቀሱ ጥቂት የትምህርት ማዕከላት የተወሰነው የቤተክርስቲያን ዕውቀት ባልተዳረሰበት እንዲዳረስ ለማድረግ ወጣቱ የአብነት ትምህርት ቤት መማር አለበት:: የዚህም የተለያየ መገለጫ አለው::

<u>አንደኛ፤</u> ለዓመታት በአብነት ትምህርት ቤቶች ከአባቶቹ እግር ሥር ተቀምጦ የተማረ ወጣት እሱም በተራው ወደሌላ ቦታ ሄዶ እንደየኔታ ጉባኤውን ከእግሩ ሥር ዘርግቶ የድልድይነት ሥራውን ይሠራል:: <u>ሁለተኛ፤</u> ጉባኤ ቤት ለዓመታት ሲቀመጥ በብል፣ በውኃ፣ በስርቆት ወዘተ... ፍዳቸውን እያዩ ካሉ በርካታ የዕውቀት መዛግብት ጋር ይተዋወቃል:: በዚህ ጊዜ ብልሁ ወጣት እየጠፉ ካሉት መጻሕፍት የደረሰባቸውን በመተርጐም፣ በመገልበጥ ወዘተ... ለተቀረው ትውልድ እንዲዳረሱ ያደርጋል:: እዚህ ላይ አንድ የውጭ ዜጋ ያለውን አስታውሳለሁ:: እዚህ እኛ አገር በትንሽ ቀናት ቆይታው የልዩ ልዩ የብራና መጻሕፍትን አደጋ ላይ መሆን ያየው ይህ ፈረንጅ «ኢትዮጵያውያን የመጻሕፍታቸውን ውድመት በአርምሞ እያዩ ያሉ ይመስላሉ:: ምናልባት ጥንታውያኑን የብራና መጻሕፍት ማደሱ ወይም ቀድቶ ማስቀመጡ የሃይማኖታቸውን ሥርዓት እንደ መጣስ እየቆጠሩት ሳይሆን አይቀርም»

የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት በሚገባ ቀስሞ በጥንቃቄ ልዩ ልዩ መጻሕፍትን መተርጐምና መጠገን በምንም ዓይነት የቤተ ክርስቲያንን ሥርዓት መጣስ አይሆንም:: ስለዚህ የወጣቱ በአብነት ትምህርት መሰማራት መጻሕፍቱን ከመጠገንና ከመተርጐም አንጻር ጠቀሜታ አለው::

ሦስተኛ፣ የአብነት ትምህርት የተማረ ወጣት በስብከተ ወንጌል አገልግሎት ቢሠማራ ከእውነተኛው የቤተ ክርስቲያን ዕውቀት እየቀዳ የሚያጠጣ ሊቅ ይሆናል:: አበው ሐዋርያት ብዙ መከራና ችግር አይተውበት ያለፉትን ቅዱስ ወንጌል ይዞ ከተቀደሰው መድረክ ላይ ሲወጣ አይፈራም አይደናገርም:: ከብሉይ ከሐዲሱ ከታሪክ ከፍልስፍናው

እያጣቀሰ ለሰማእያኑ ያቀብላል እንጂ::

ስለዚህ በእነዚህና በሌሎች መገለጫዎች የተነሣ የወጣቱ የአብነት ትምህርት መማር በተወሰኑ ቦታዎች ብቻ የተከማቸው ዕውቀት እንዲዳረስ ያደርጋል::

### መ. የግእዝን ቋንቋ የቀድሞ ክብር መልሶ በቋንቋው የተጻፉ መዛግብትን ለመረዳት ያስችላል

ብዙ ጊዜ ሰዎች በተለይ የቋንቋ ምሁራን በግእዝ ቋንቋ የዛሬ ሁኔታ ዙሪያ የሚሰጡት የተሣሣተ አስተያየት አለ:: ግእዝ ሞቷል የሚል:: በመሠረቱ አንድ ቋንቋ ሞተ የሚባለው ቋንቋውን የሚናገር ምንም ዓይነት ሰው ሳይገኝ ሲቀር፣ ምናልባት ቋንቋው በጽሑፍ ላይ የዋለ ከሆነ በእሱ የተጻፉትን መዛግብት አንብቦ ሊረዳ የሚችል ሰው የሌለ እንደሆነ ነው:: ታዲያ ግእዝ በምን ዓይነት የሞተ ቋንቋ ነው ይባላል? ዛሬም ቢሆን ባያንሱም ባይበዙ ግእዝን በቋንቋነት ተጠቅመው የሚግባቡ ሊቃውንት አሉ፤ ወርቃማ በሚባለው የቋንቋው የወጣትነት ዘመን የተጻፉትን መዛግብት በሚገባ ተረድተው የሚያስረዱ አበው ሞልተዋል:: ታዲያ ስለምን ነው ግእዝ ሞቷል መባሉ? አይመስለኝም:: ምናልባት አንቀላፍቷል ቢባል የሚመረጥ ይሆናል::

የወጣቱ የአብነት ትምህርት መማር አንዱ ጥቅም አንዳንድ የቋንቋ ምሁራን ሳይሞት ሞተ እያሉ ሙሾ አውርዱለት መቃብር ቆፍሩለት የሚሉትንና የራሱ የሆነ ፊደል ያሉትን፣ በርካታ ዕውቀቶችን ይዞ ጋደም ያለውን ቋንቋችንን ወደነበረበት ክብሩ ይመልሳል:: በእውነቱ በቋንቋ ምሁራን ስብከት ይመስላል ትውልዱ የግእዝን ቋንቋ በሚመለከት ተስፋ ቆርጧል:: ልማር እንኳ ቢል የእሱ አእምሮ ሊያስተናግደው የማይችል ይመስለዋል:: እንደውም ሞቶ የተቀበረ ቋንቋ እየመሰለው ሊያስበውም ፈቃደኛ አይደለም:: በመሠረቱ ግእዝ ቋንቋ ነው:: በመሆኑም ለቅሶ እያለ እንባ ካልገደደን እንደ አንድ አፋችንን እንደፈታንበት ወይም ገንዘብ ከፍለን እንደምንማረው ቋንቋ መማር እንችላለን:: ያንን የምናገኘው ደግሞ አንድም ወደ አብነት ትምህርት ቤቶች ጐራ ስንል ነው:: የእኛ ያልሆነውን ለመንተባተብ ከመዳዳት ይልቅ፣ ልጆቻችንንም በለጋ አዕምሮአቸው የፈረንጁን ፊደላት በኬክ እያስቀረጹ በማስተማር ፈንታ /ጐን/ የእነሱ የሆነውን አቡጊዳ ፊደል እያስተማርን ስናሳድጋቸው ነው:: በቅርቡ አንዲት ኢትዮጵያዊት ወጣት አንዱን ዘፋኝ «አቡጊዳ ፍቅረኛህ ናት ወይስ?» ብላ እንደጠየቀች ሰምቼአለሁ:: ለማጠቃለል የወጣቱ ወደአብነት ትምህርት ቤት መሠማራት ትና ንት አባቶቻችን ከመግባቢያነት አልፈው ልዩ ልዩ የቤተ ክርስቲያንን ዕውቀቶች፣ ታሪካቸውን ገድላቸውን ወዘተ... ጽፈውበት ያለፉትን የግእዝን ቋንቋ ወደቀደመ ክብሩ መልሶ በማህደርነት የያዛቸውን ፈርጀ ብዙ ዕውቀቶች ለማውጣት ያስችላል::

### ሠ. በቤተ ክርስቲያን ዙሪያ በቂ ጥናትና ምርምር ለማድረግ

የወጣቱ የአብነት ትምህርቶችን መማር ሌላው የሚሰጠው ጥቅም በነገረ ቤተ ክርስቲያን ዙሪያ ልዩ ልዩ ጥናትና ምርምሮችን ለማድረግ ማስቻሉ ነው:: ቤተ ክርስቲያናችን እንደ ልዩ ልዩ የዕውቀት ዘርፎች ማኅደርነቷ በውስጧ በርካታ ለጥናትና ለምርምር የሚጋብዙ ጉዳዮች አሏት:: ነገር ግን እውነታው ይህ ሆኖ ሳለ ዘመናዊውን ትምህርት በተማሩ ልጆቿ እንኳን «ምንም የለም» ወደሚል ጽንፍ እስከሚያደርስ ድረስ የተሠሩ ጥናቶችና ምርምሮች የሉም:: ነገሩ በራሱ ሌላ ጥናት የሚጠይቅ ቢሆንም ዛሬ አሉ በሚባሉ የሀገራችን ከፍተኛ ትምህርት ተቋማትም ሆነ ሌሎች የኢትዮጵያ ጥናት ተቋማት አብያተ መጻሕፍት ከሚገኙት 100 የምርምር ሥራዎች ከአምስት የማይበልጡ ብቻ በነገረ ቤተ ክርስቲያን ላይ የተሠሩ ናቸው:: ከእነዚህም ውስጥ ከግማሽ የሚበልጡቱ የተሠሩት ቤተክርስቲያን በዕውቀት ባልወለደቻቸው ባዕዳን ነው:: በመሆናቸውም በዕውቀት ማነስም ሆነ ሆን ተብለው በተሠሩ ስህተቶች የተሞሉ ናቸው::

የቤተክርስቲያን ልጆች በዙ ጥናትና ምርምሮች በነገረ ቤተ ክርስቲያናችን ዙሪያ ላለማድረጋቸው ከሚጠቀሱት ምክንያቶች አንዱና ዋነኛው የቤተክርስቲያናቸውን ዕውቀት በዓይነት በዓይነቱ ብለማወቃቸው ነው:: ቀድሞውኑ ቅድስት ቤተክርስቲያን ለዕውቀቷ፣ ለታሪኳ፣ ለትውፊቷ ሁሉ ባይተዋር ስለሆኑ በነዚያ ዙሪያ ጥናትና ምርምር ለማድረግ አያስቡም:: ለማሰብም አይፈልጉም:: በድፍረት እንኳ ቢሠሩ በምርምራቸው ውስጥ ስህተት ይበዛል:: ስለዚህ ወጣቶች በዘመናዊው ትምህርት ቤታቸው ያገኙትን የምርምር ዘዴ ተጠቅመው በነገረ ቤተ ክርስቲያናቸው ዙሪያ ጥናቶችን መሥራት እንዲችሉ በመጀመሪያ የአብነት ትምህርቶችን በሚገባ መማር አለባቸው:: የዚህ ውጤቱ ብዙ ነው:: አንደኛ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችንን ለማያውቁና ለማወቅ ሳይፈልጉ ባዕድ ያቀበላቸውን የጥፋት ፍልስፍና ለሚሰሙ ሁሉ የቤተ ክርስቲያንን ማንነት በሚገባ ያሳውቃል:: በዚያ አልፎም ቤተ ክርስቲያን ከታወቀች ዘንድ እሷን ብለው ከሚመጡ ባዕዳንም ሆነ ሌሎች ገቢ ታገኛለች:: ከዚህ [illegible] የወጣቶች የአብነት ትምህርት [illegible] ጥናትና ምርምር ማድረግ ከላይ ለተጠቃሣው አንድ ችግር መፍትሔ ይሰጣል:: [illegible] ዛሬ አሉ በሚባሉ ጥናትና ምርምሮች ለሚታዩት ሆን ተብለውም ሆነ ባለማወቅ ለተሠሩ ስህተቶች ምላሽ ለመስጠት ይረዳል::

*ስለአብነት ትምህርት ጠቅለል ያለ ሐሳብ ሰጥቶ ወጣቱና የአብነት ትምህርት ሊገናኙ የሚመጣውን ጥቅም የቃኘንበት ይህ ጽሑፍ ይቀጥላል:: ቀጣዩ ጽሑፍ ወጣቱና የአብነት ትምህርት ተፈላላጊ ሆነው ሳለ ያልተገናኙበትን ምክንያትና መፍትሔዎቹን ይዳስሳል:: እስከ እናንተም በነዚህ ነጥቦች ዙሪያ ያሏችሁን አስተያየቶች ሰጉዙልን::*

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

**ሊቃውንት አባቶቻችሁ አመለጧችሁ እኮ ልጆቼ፣ ሕጻናት ሆናችሁ መሰለኝ:: ዛሬ ቢሄዱ ነገ የሚመለሱ እየመሰላችሁ ወደማያልቀው መንገድ ሲሄዱ ዝም ብላችሁ ታዩአቸዋላችሁን? ቅረቡና ያሏቸውን ያውርሷችሁ እንጂ? ያደፈ የቆሸሸ ለብሰው ብታዩ አንድም እንደምታውቋቸው ቱጃሮች የታጠበ የተተኮሰ ለብሰው ስላላያችኋቸው፣ ምግባቸው ኮቸሮ፣ መኝታቸው ጐጆ ሆኖ ብታዩ ድሆች እያላችሁ ትሸሿቸዋላችሁን? እረ በእነሱ ያደፈና የቆሸሸ ጐጆ ውስጥ ብዙ ሀብት አለ:: ሂዱና ያውርሷችሁ እንጂ:: ልጅ ወደ አባቱ ሄዶ አባቴ ያለህን አውርሰኝ ብሎ ይለምናል እንጂ፣ እንዴት አባት ልጁን ልጄ እባክህ**

# ክርስቲያናዊ የሕይወት ለውጥ

*ዲ. ያሬድ ገ/መድኅን*

ክርስቲያናዊ የሕይወት ለውጥ ማለት ከኃጢአት ተለይቶ ጽድቅን መሥራት መጀመር፣ ፈቃደ ሥጋን ለፈቃደ ነፍስ አስገዝቶ መኖርን መለማመድ፣ የቀደመን ሥጋዊ አስተሳሰብ ትቶ በአዲስ መንፈሳዊ አኗኗር መመላለስ ማለት ነው::

ክርስቲያናዊ የሕይወት ለውጥ የሰው ከኃጢአት ወደ ጽድቅ መሸጋገር እግዚአብሔርን መበደል ትቶ በንስሐ መመለስም ነው:: ከዚህ አንጻር ክርስቲያን ቀድሞ ይሠራው የነበረውን ኃጢአት ትቶ ንስሐ ሲገባ፣ ዓለማዊ ግብር መፈጸም አቁሞ ወደ እግዚአብሔር ሲመለስ የሕይወት ለውወጥ ኖረው ይባላል:: በሕይወቱም ዙሪያ ለውጥ እንዳለ ይነገራል:: ክርስቲያናዊ የሕይወት ለውጥ ክርስቶስን ለመምሰል የአባቶችን ፈለግ ለመከተል ክርስትናን በተግባር ለመተርጎም ይረዳል:: ከዚህ ውጭ ይኸ ለውጥ በሕብረተሰቡ መካከል ስንኖር ኑሮአችን ጣፋጭ እንዲሆን ጨው ሆነን ዓለሙን እንድናጣፍጥ ... ይጠቅማል:: በመሆኑም መንፈሳዊ ሕይወቱ የተስተካከለ ክርስቲያን ከራሱ አልፎ ለሌላውም ስለሚተርፍ በሕይወቱ አካባቢውንም ያጣፍጣል::

በቀደመው ዘመን የነበሩ አባቶች ይኸንን ተረድተው በሕይወታቸው ዙሪያ የነበረውን ችግር ቀርፈው ወደ ቤተክርስቲያን ሲቀርቡ ፍፁም መንፈሳዊ እንደሆኑ ታሪካቸው ይነግረናል:: ለምሳሌ ቅዱስ ጳውሎስ አንዱ ነው:: ይኸ አባት ቀድሞ ባለማወቅ ክርስቲያኖችን ያሳድድ የነበረ የቤተክርስቲያን ጠላት ሆኖም የተመላለሰ ነበር:: ኋላ ግን ሲመለስ ፍፁም መንፈሳዊ ሆነ:: ሐዋ 9÷1:: ማሳደዱም ቀርቶ እየተሳደደ መኖር ጀመረ:: ፈያታዊ ዘየማን ሌላው የምናነሳው ሰው ነው::: ይኸ ወንበዴ ጌታችን አጠገብ እስከተሰቀለበት ሰዓት ድረስ የብዙዎችን ደም አፍስሷል:: በሽፍትነት እየቀማና እየሰረቀ ቆይቷል:: «ሓሳበ-ምድራዊ» ነበር:: ኋላ ግን መስቀል ላይ ሲወጣ የክርስቶስን ተአምራት አይቶ ተመለሰ:: «ጌታ ሆይ በመንግሥትህ በመጣህ ጊዜ አስበኝ» /ሉቃ 23÷42/ አለ:: ለገነት ክብርም በቃ:: በዚህ ሰው ሕይወት ውስጥ እንደ ምንመለከተው የሰው ልጅ ሲለወጥ ስለ ሥጋው ብቻ ማሰብ ቀርቶ ስለነፍሱም መጨነቅ ይጀምራል:: በእግዚአብሔር ፊት በቆመ ቁጥር በመንግሥትህ አስበኝ ይላል:: ጌታችን አስቀድማችሁ «ጽድቁን እሹ» /ማቴ 6÷33/ እንዳለ ከሁሉ በፊት የሚያስቀድመው ጽድቁን ነው:: ፈያታዊ ዘየማን በሞት አፋፍ ላይ ስለነበረ እንደባልንጀራው ከመስቀል አውርደኝ ማለት ይችላል:: ግን አላለም መንፈሳዊነትን ገንዘብ በማድረግ ስለነፍሱ ነፀር የለመነው::

ከዚህ አንጻር በአባቶች እንዳየነው ክርስቲያን ወደ ቤተክርስቲያን ሲቀርብ ስለ ሥጋዊ ሕይወቱ ብቻ መጨነቁን ትቶ ስለነፍሱም ሊያስብ ይገባዋል:: ያን ጊዜ በሕይወቱ ዙሪያ ለውጥ እንዳለ ማረጋገጥ ይቻላል:: ቅዱስ ጳውሎስ «ፊተኛ ኑሮአችሁን እያሰባችሁ እንደሚያታልል ምኞት የሚጠፋውን አሮጌውን ሰው አስወግዱ» ኤፌ. 4÷22/ የሚለንም ለዚህ ነው:: ከዚሁ ሁሉ ጋር በሕይወቱ የተስተካከለ መንፈሳዊ ሰው ታማኝ፣ ትሑት፣ ከሁሉ ጋር የሚግባባ መሆን አለበት ወይም ክርስትናውን በሥራ መግለጥ ይገባዋል:: ይኸንን የሚያደርገው ደግሞ ለመታየት ብቻ ሳይሆን ከልቡ ተረድቶ መሆን አለበት:: ምክንያቱም ክርስቲያናዊ የሕይወት ለውጥ ከልብ የመነጨ መንፈ ሳዊነትን የሚሻ ስለሆነ ነው:: ቅዱስ ጳውሎ ስም ስለዚህ ሲነግረን «የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም በጎና ደስ የሚያሰኝ ፍጹም የሆነው ነገር ምን እንደሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይኸን ዓለም አትምሰሉ» /ሮሜ 12÷2/ ይለናል:: መለወጥ ከልብ የመነጨ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በመፈጸም የሚሻ የሚገለጥ መሆኑን ያስተምረናል::

## ትክክለኛ ያልሆነ ለውጥ

ክርስቲያናዊ የሕይወት ለውጥ ምን እንደሚመስል በመጠኑ አይተናል:: እውነታው እንዲህ ሆኖ ሳለ አንዳንድ ሰዎች ግን ባለማወቅ እንዲሁም የሚጎድላቸውን ባለመረዳት ትክክለኛውን የሕይወት ለውጥ አዙም:: «መንፈሳዊ» ከሆኑም በኋላ ክርስትናቸው ጉድለት አያጣውም ይሆናል:: ስለዚህ አንድ ሰው ወደ ቤተክርስቲያን ሲቀርብ በሕይወቱ ዙሪያ የተፈጠረውን ለውጥ ምንነት መመርመር አለበት:: ትክክለኛነቱንም ሊያረጋግጥ ይገባዋል:: ይኸንን ለመረዳት ቀጥለን ትክክለኛ ያልሆኑ ክርስቲያናዊ የሕይወት ለውጦችን እንመለከታለን፡

- የስም ለውጥ

አንዳንድ ሰው «መንፈሳዊ» የሚለውን ስም በመጨመር ብቻ በቤተክርስቲያን የሚኖር አለ:: የቀድሞ ጠባዩን ሳይሽር ከኃጢያት ሳይለይ ቁጣ ስድብ... ሳይተው «መንፈሳዊ» ይሆናል:: ወይም ተብሎ መጠራት ይጀምራል:: ከዚያ ስሙን በማግኘቱ በመደሰት ከምግባር ከትሩፋት ይርቃል:: ያገኘው ሁሉ መንፈሳዊ ነው ብሎ ስለሚመሰክርለት መንፈሳዊነቱን አረጋግጦ ይቀመጣል:: በየዕለቱ የሚጨምረው ነገር አይኖርም:: ሕይወቱን ለማሻሻልም አይጥርም::

ይኸን ሳነሳ አንድ የማውቀው ወጣት ትዝ አለኝ:: አስቀድሞ በአካባቢው የታወቀ ተደባዳቢ፣ ተሳዳቢ... ነበር:: ኋላ ከዚህ ሁሉ ታቅቦ «መንፈሳዊ» ሆነ:: በቤተ ክርስቲያንም ማገልገል ጀመረ:: ነገር ግን በሕይወቱ አልተለወጠም:: አኗኗሩ እንደ ድሮው ነበር:: ቤተክርስቲያን በአገልግሎት ወቅት ሓሳቡን የሚቃወሙት ሰዎች ከገጠሙት ዱላ ይመዛል፣ የሚነቅፈውንም ይነቅፋል...:: በዚህ የተነሣ ቀድሞ የሚያውቁት ጓደኞቹ መንፈሳዊነቱ አልታይ እያላቸው ብዙ ጊዜ ሲነቅፉት እሰማለሁ:: «አንተ ብሎ መንፈሳዊ...»ይሉታል::

በመሠረቱ ይኸ ሰው ወደ ቤተ ክርስቲያን መቅረቡ ራሱ አንድ ትልቅ ውሳኔ ነው:: ነገር ግን ከገባ በኋላ ማሻሻል ያለበትን ነገር ባለማሻሻል መንገድ ጀምሮ እንደተበላሸና ጉዞውን እንዳቋረጠ አውቶቡስ ሆነ:: ከዚህ አንጻር እንዲህ ዓይነት ችግር ያለበት ወደ ቤተ ክርስቲያን የቀረበ በስም ብቻ መንፈሳዊ የተባለ በሕይወቱ ግን ለውጥ ያላሳየ ክርስቲያን ስሙን ከግብሩ ጋር ለማጣመር መጣር አለበት:: ለውጡ የስም ብቻ ከሆነ ትክክለኛነቱ ስለሚያጠራጥር ሊያስተካክለው ይገባል::

እስክንድር የተባለ ንጉሥ /ጀግና የነበረ ሰው ነው/ አንድ ወቅት ወደ ጦር ሜዳ ይሄድና ከሚዋጉ ወታደሮች አንዱን ሲሸሽ ያገኘዋል:: በጣም ገርሞት ጠራና ጠየቀው «ስምህ ማነው?» አለው ያም ፈሪ ወታደር ስሙ እስክንድር ነበርና ይኸንኑ መለሰለት:: «እስክንድር እባላለሁ» አለው:: ንጉሡም ስሙን ሲሰማ ይብስ ገርሞት «አንተ እስክንድር ነህ!» ካለ በኋላ «በል ወይ ስሜን መልስ አልያ አጥብቀህ ተኩስ» አለው ይባላል:: የጀግና ስም ይዞ ፈሪ መሆን አይገባም ሲለው ነው:: እንዲሁ «መንፈሳዊ» ተብሎ ቁጣ÷ሐሜት÷... ስለ ማይገባ እንደ ስም ለመኖር መጣር ያስፈልጋል::

- የቦታ ለውጥ

የአንዳንድ ሰው መንፈሳዊነት ደግሞ ከቦታ ጋር ይያያዛል:: ይኸም ከቤተ ክርስቲያን ውጪ ዓለማዊ፣ ቤተ ክርስቲያን ሲደርሱ መንፈሳዊ መሆን ማለት ነው:: በሚሠራበት መሥሪያ ቤት በመኖሪያ ቤቱ... ክርስትናውን የማይገልጥ ነገር ግን ቤተክርስቲያን ሲደርስ ፍፁም መንፈሳዊ ሆኖ የሚታይ አለ:: ሌላ ቦታ ሰውን አሳዝኖ የተሰጠውን ኃላፊነት ባለመወጣት ሕዝብ አማርሮ የሥራ ባልደረቦቹ ጠልተውት ቤተክርስቲያን ነጠላ አጣፍቶ ቢታይ ወይም የቤተ ክርስቲያን ሰዎች ስለጥሩነቱ ቢመሰክሩለት ክርስትናው በቦታ የተወሰነ ሆኗል ማለት ነው::

ታቦተ ጽዮን በፍልስጥኤም የተማረከችበት ወቅት እንደነበር ቅዱሳት መጻሕፍት ይነግሩናል:: ይህች ታቦት አሕዛብ ወስደዋት ከጣዖታቸው ከዳጎን ጋር አስቀመጧት:: ነገር ግን ከዳጎን ጋር

ተስማምታ አልተቀመጠችም፡፡ በማግስቱ ሲመጡ ዳጎን ወድቆ ተገኘ፡፡ አሁንም ደግመው በአንድነት ቢያስቀምጧቸው ጣለችው፤ በሦስተኛው እንደዚያው ቢያደርጉ እንዲያውም ጣዖታቸውን ሰባብራ ጠበቀቻቸው፡፡ በዚህ የተነሣ ፈርተዋት ወደ ሃገሯ በክብር መልሰዋታል፡፡ 1ሳሙ. 5÷1–12 6÷1÷21፡፡ እዚህ ላይ ታቦተ ጽዮን በሃገሯ ታቦት በአሕዛብ ምድር ጣዖት አልሆነችም ሁሌ ታቦት ናት፡፡

እንደዚሁ ክርስቲያንም በየትኛው ውም ቦታ ታቦት /የእግዚአብሔር ማደሪያ/ ነው እንጂ፡፡ ከጣዖት ጋር ጣዖት ከታቦት ጋር ታቦት ሊሆን አይገባውም፡፡ ይኸንን ተረድቶ መንፈሳዊ ለመሆን የቀረበ ሰው መንፈሳዊነቱን በቦታዎች ሁሉ ማረጋገጥ አለበት፡፡ ያን ጊዜ ትክክለኛ ለውጥ በሕይወቱ መኖሩ ይታወቃል፡፡

• የጊዜ ለውጥ

አንዳንድ ሰው ደግሞ የሚለወጠው በጊዜ ወስኖ ነው፡፡ ለምሳሌ በኑሮ ችግር ሲያጋጥመው÷ ሲታመም÷ ትዳሩ ሲናጋ ቤተሰቡ ሲረበሽ... መንፈሳዊ ይሆናል፡፡ ከዚያ ሁኔታዎች ተስተካክለው ሰላም ሲያገኝ ደግሞ ይተወዋል፡፡ እንደዚሁም ቤተክርስቲያን ሰላም ስትሆን ፈተና ሲርቅ መንፈሳዊ ይሆናል፡፡ ከዚያ ትንሽ ችግር ሲነሳ የሰበካ ጉባኤ ምርጫ እንኳን ኖሮ አለመግባባት ሲፈጠር ቤቱ ይከተታል፡፡ መንፈሳዊነቱ ከጊዜ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ አንድ ወቅት መራቅ ሌላ ወቅት መቅረብ፡፡ እንዲህ ዓይነቱ መንፈሳዊነትም ትክክለኛ አይደለም፡፡

በመሠረቱ ክርስትና ሲቸግረን የምንኖረው ችግራችን ሲወገድ የምንተወው ሕይወት አይደለም፡፡ ቅዱስ ዳዊት እረኛ ሆኖም የእግዚአብሔር ነበር፡፡ ከዚያ ተነሥቶ ንጉሥ ከሆነም በኋላ ፈጣሪውን አልረሳም፡፡ ለዚህ ነው እግዚአብሔር «እንደ ልቤ የሚሆንልኝ» ብሎ የመሰከረለት፡፡ ከዚህ አንጻር ክርስቲያን ሲያጣም ሲያገኝም ከእግዚአብሔር መለየት የለበትም፡፡ በሌላ በኩል የቤተ ክርስቲያን አካባቢ ችግር ሲኖር መሸሹ ሰላም ሲኖር መምጣቱም አግባብ አይደለም፡፡ ቅ.ጳውሎስ ወደ ክርስትናው ከተጠራ በኋላ ብዙ መከራ ገጥሞታል፡፡ አባቶቻችን ሐዋርያትም በየደረሱበት በመከራ ተፈትነዋል፡፡ ይኸ ግን ከመንፈሳዊነቱ አልለያቸውም፡፡ ዓለሙ ወርቅ አንጥፎ በእልልታ በደስታ ባይቀበላቸውም አገልግሎታቸውን ፈጽመዋል፡፡ እነዚህ አባቶች የተመቻቸ ነገር ብቻ እየጠበቁ የሚገለፁ የሚያገለግሉ ቢሆን ክርስትና እንደ ሰደድ እሳት ዓለምን ባላዳረሰ ነበር፡፡ ወንጌል በዓለሙ ሁሉ እንዲሰበክ ምክንያት የሆነው ችግሩንና ስቃዩን ታግሠው ዞረው ማስተማራቸው ነው፡፡ ይኸን ተረድቶ መንፈሳዊ ሰው «በጊዜውም አለጊዜውም» መጽናት /2ጢሞ. 4÷2/ ይገባዋል፡፡

• ከሰው ጋር የተያያዘ ለውጥ

አንዳንድ ሰው የሚለወጠው ደግሞ ሰው እያየ ነው፡፡ ባልንጀራው ሲያስቀድስ የሚያስቀድስ ሲቆርብ የሚቆርብ ሲጾም የሚጾም... አለ፡፡ በመሠረቱ ሰውን አይቶ መንፈሳዊ መሆን በራሱ ወንጀል አይደለም፡፡ ክርስትና የጸኑትን የምንከተልበት ከአባቶች ከወንድሞች እየተመለከትን ራሳችንን የምናስተካክልበት ሕይወት ነው፡፡ ነገር ግን መንፈሳዊ የምንሆነው ገብቶን ተረድተነው አምነንበት ሳይሆን ሰውን ተመልክተን ብቻ ከሆነ በራሱ ችግር ይኖረዋል፡፡ ስለዚህ ክርስቲያን ሌላውን እያየ ቢመጣ እንኳን ወደ ክርስትናው ከገባ በኋላ በራሱ እግር የሚቆም የሚሰራውን የሚያውቅ ባመነበት የሚጓዝ መሆን አለበት፡፡

ብዙ ጊዜ ሰውን የሚያይ ክርስቲያን ያ የሚመለከተው ሰው ሲወድቅ ሲመለከት ሊወድቅ ይችላል፡፡ ይኸን ስል አንድ የማውቀው ምእመን ትዝ ይለኛል፡፡ ቤተሰቦቹ መንፈሳዊነትን ሲያጠብቁ ያጠብቃል፣ ጉባኤ ሲሄዱ፣ ሲያስቀድሱ ... እነርሱን ተከትሎ ይጠነክራል፡፡ ይኸ ቀርቶ መንፈሳዊነቱን ሲተዉት ክርስትናቸውን ሲያላሉ ደግሞ እርሱም ይላላል፡፡ ስለዚህ ብዙ ጊዜ ስለቤተሰቦቹ ሁኔታ ለማወቅ እርሱን ማየት ብቻ በቂ ነው፡፡ ጠንካራ የሆነ ሰሞን እንደጠነከሩ ይታወቃል፡፡ ሲላላ ደግሞ ላልተዋል ማለት ነው፡፡

እንዲህ ዓይነቱ ክርስትና አማንያን ባሉበት ብቻ እንጂ ኢ-አማንያን በበዙበት ስለማይሠራ ሰውን የሚመለከት ክርስቲያን ይኸንን ልምድ መተው አለበት፡፡ ነቢዩ ዳዊት በመዝሙሩ ተራሮች ወደ ባሕር ልብ ቢወሰዱ አልፈራም» መዝ.45÷2 ይላል፡፡ በዚህ ቃሉ ተራራ ያላቸው ቅዱሳ ንን፤ ከፍ ብለው የሚታዩ የእግዚአ ብሔር ሰዎችን ነው፡፡ እነርሱ እንኳን ወደ ባሕር ልብ ቢገቡ /ዓለማዊ ቢሆኑ፣ ይህች ዓለም በፈቃዷ ብትስባቸው ብታስጥማቸው/ እኔ አልናወጥም፡፡ ይላል ዕንባቆምም በትንቢቱ «ምንም እንኳ በለስ ባታፈራ በወይንም ሐረግ ፍሬ ባይገኝ÷ የወይራ ሥራ ቢጎድል÷ እረኞችም መብልን ባይሰጡ÷ በጎች ከበረቱ ቢጠፉ÷ ላሞችም በጋጡ ውስጥ ባይገኙ÷ እኔ ግን በእግዚአብሔር ደስ ይለኛል፡፡ በመድኃኒቴ አምላክ ሐሴት አደርጋለሁ» ዕንባ. 3÷17 ብሏል፡፡ ወይን የተባለ ሰው እንደተጠበቀው ባይገኝ/ፍሬ ባያፈራ/ ከበረት/ቤተክርስቲያን/ በጎች ምእመናን ቢጠፉ...፡፡ እኔ በእግዚአብሔር ደስ ይለኛል /በእርሱ እታመናለሁ/ ሲል ነው፡፡ መንፈሳዊ ሰው «እገሌ ስለሰከረ ሰከርኩ እገሌ ስለበደለ በደልኩ» እንዳይል ሁል ጊዜ ሰውን ብቻ እየተመለከተ መጓዝ የለበትም፡፡ ሰውን እያየ ሳይረዳና ሳይገባው መለወጥም ትክክለኛ ለውጥ አይደለም፡፡

ከዚህ በላይ እንዳየናቸው ሰውን መንፈሳዊ ነኝ በሎ እንዲያስብ የሚያደርጉ ነገር ግን ትክክለኛውን መንፈሳዊነት ያልተከተሉ አካሄዶች አሉ፡፡ ይኸንን ተረድቶ መንፈሳዊነትን የጀመረ ሰው ራሱን መመርመር አለበት፡፡ ቅ.ጳውሎስ «የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም በጎና ደስ የሚያሰኝ ፍጹምም የሆነው ነገር ምን እንደሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይኸን ዓለም አትምሰሉ» ሮሜ 12÷2 እንዳለ መንፈሳዊ ሰው ለውጡ ልባዊ መሆኑንና አለመሆኑን ለማወቅ ራሱን መመዘን ይገባዋል፡፡

## እንዳንለወጥ የሚያደርገን ምንድነው?

ብዙ ጊዜ ሰውን መንፈሳዊ እንዳይሆን የሚያደርጉና በጉዞው እንቅፋት የሚሆኑ ነጥ ቦች አሉ፤ የተወሰኑትን ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

• የሠራውን ሥራ ማሰብ

መንፈሳዊ ሰው እየሠራ አልሠራሁም የሚል፣ ብዙ ደክሞ ወጥቶ ወርዶ በሠራው ሥራ የማይመካ ነው፡፡ ከዚህ የተነሣ ሁልጊዜ ሠርቻለሁ ሳይሆን ምን ልሥራ እያለ ያስባል፡፡ ያልሠራው ለመሥራትም ይዘጋጃል፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ «አሁን እንዳገኘሁ ወይም አሁን ፍጹም እንደ ሆንሁ አይደለም ነገር ግን ስለ እርሱ በክርስቶስ ኢየሱስ የተያዝሁበትን ደግሞ እይዛለሁ፡፡ ብዬ እፈጥናለሁ ወንድሞች ሆይ እኔ ገና እንዳልያዝሁት እቆጥራለሁ፡፡ ነገር ግን አንድ ነገር አደርጋለሁ፡፡ በኋላዬ ያለውን እየረሳሁ በፊቴ ያለውን ለመያዝ እዘረጋለሁ» ፊል. 3÷12 የሚለንም ለዚህ ነው፡፡

አንዳንድ ሰው ከዚህ በተቃራኒ እየተጓዘ ያልሠራውን ሳይሆን የሠራውን ብቻ የሚያስብ አለ፡፡ በዚህ የተነሣ ብዙ የሠራ ስለሚመስለው ይዘናጋል፡፡ መሥራት የሚገባውን እንዳይሠራ ሆኖ ባለፈ ተግባሩ በመፅናናት ብቻ ይቀመጣል፡፡ ይኸ ደግሞ በመንፈሳዊ ሕይወቱ እያደገ ጉድለቱን እያስተካከለ እንዳይሄድ ያደርገዋል፡፡

• ደካሞችን መመልከት

ከላይ ከሰው ጋር የተያያዘ ለውጥ ሊኖረን እንደማይገባ እንዳየነው ክርስቲያን በመንፈሳዊ ጉዞው ሰውን መመልከት የለበትም፡፡ ይልቁንም ደካማ የሆኑ የማይጸሙ የማይጸልዩ በጎ ምግባር የሌላቸው ካየ ስለሚያደክሙት ሊመለከታቸው አይገባም፡፡ አንዳንድ ሰው ግን ይኸን ባለመረዳት ሁል ጊዜ ከበጎ ምግባር ውጭ የሆኑትን የሚመለከት አለ፡፡ ይኸ ደግሞ በራሱ እንዲጸናና ከእነርሱ ስለ ምሻል ይበቃኛል ብሎ እንዲያስብ ስለ ሚያደርገው ለመንፈሳዊነቱ እንቅፋት ይሆነዋል፡፡ ስለዚህ መንፈሳዊ ሰው ቅ. ጳውሎስ «የፀናውን አስቡ» እንዳለ ዕብ.12÷4 ማሰብ ያለበት የጸኑትን ቅዱሳኑን ሰማዕታትን ነው ወይም በዚህ ዘመን ያሉ በበጎ ምግባር የጸኑትን አባቶችን ነው፡፡

• ራስን አለማየት

አንዳንድ ሰው በመንፈሳዊ ሕይወቱ እንዳይለወጥ የሚያደርገው ራሱን አለማየቱ ነው፡፡ እንዲህ ያለ ሰው «እኔ ማን ነኝ» የሚልበት ጊዜ ስለማይኖረው ይቁም ይውደቅ አያውቅም፡፡ በመንፈሳዊ ሕይወቱ ለውጥ ይኑር አይኑር አይረዳም፡፡ ከዚህ የተነሣ መለወጥ ይከብደዋል፡፡ ጉድለቱን የሚያስብበት አእምሮ ስለሌለው ከነጉድለቱ ይኖራል፡፡ እዚህ ላይ ቢያንስ ችግር እንዳለበት ቢያውቅ በአንድ ጊዜ ባይሻሻል ቀስ እያለ ይስተካከል ነበር፡፡ ነገር ግን ያንንም አያውቅም፡፡ ስለዚህ ባለመለወጡ ልቡናው ጥያቄ አይፈጥርለትም፡፡ አይደነቅም ወደ እግዚአብሔር አይለምንም...፡፡

ነገር ግን ጌታችን ለኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን መልአክ/አለቃ/ «ከወዴት እንደወደቅህ አስብ» ራእ. ዮሐ. 2÷5 እንዳለ ሰው ሁልጊዜ ራሱን ሊመረምር ያለበትን የመንፈሳዊ ሕይወት እንቅስቃሴ ሊመለከት ይገባዋል፡፡ «እኔ ማን

ነኝ?» ብሎ ራሱን እየጠየቀ የቀደለውን ለማሻሻል መዘጋጀት ይኖርበታል፡፡ ያን ጊዜ ነው መለወጥ የሚችለው አለበለዚያ ግን ራሱን ካላየ ማጥፋቱንም ሳያውቅ በመንፈሳዊ ሕይወቱም ሳይሻሻል ይኖራል፡፡

- አስመወሰን

በክርስትና ስንኖር መንፈሳዊ ለመ ሆን በሕይወታችን ለመስተካከል በእያ ንዳንዱ ጉዞአችን ለውሳኔ ቆራጥ መሆን ያስፈልጋል፡፡ ንስሐ ለመግባት፣ ለመቁረብ፣ ለመጾም... ውሳኔ ይጠይቃል፡፡ አንዳንድ ሰው ግን ይኽን ባለማድረግ መወሰን ስለሚከብደው የሚያመካኘው አለ፡፡ ኃጢአቱንም ጽድቁንም ቀላቅሎ እየተጓዘ ወደ አንዱ መቅረብ የሚከብደው አይጠፋም፡፡ በመሠረቱ ሰውን ከኃጢያት የሚለይ እግዚአብሔር ነው፡፡ ቢሆንም ግን በዚህ ውስጥ የሰውም ድርሻ አለ፡፡ ወደ እርሱ ለመቅረብ እንዲችል መንፈሳዊ ሰው ፍላጎት ሊኖረው ይገባል፡፡ ሎጥ ራሱን ከሰዶም እንዲያሸሽ /እንዲወጣ/ ታዟል፡፡ እዚህ ላይ የእግዚአብሔር ፈቃድ እንዳለ ሆኖ የሎጥም ለመውጣት መወሰን ያስፈልግ ነበረ፡፡ «ራስህን አድን» ዘፍ.19÷17 የሚለው ቃልም የሚያመለክተው ይኽንኑ እውነታ ነው፡፡

እግዚአብሔር በግድ ስለማያ ጸድቅ ለመዳን የሰው ልጅ ሙሉ ፈቃደኝነት መኖር አለበት፡፡ ይኽ ፈቃደኝነት ደግሞ ለውሳኔ ያነሳሳል፡፡ የእግዚአብሔር ኃይል እየጠየቀ ንስሐ እንዲገባ ሕይወቱንም ለማስተካከል እንዲዘጋጅ ያደርገዋል፡፡ ስለዚህ አንድ ሰው ሕይወቱን ለማስተካከል መወሰን አለበት፡፡ መወሰን ካቃተው ግን የሚመኘውን መሆን አይችልም፡፡ በዘመናችን ብዙ ሰው ንስሐ መግባት እየተመኘ የማይገባው መንፈሳዊ መሆን እያሰበ የማይሆነውም ለዚህ ነው፡፡ ሐዋርያው ያዕቆብ በመልዕክቱ «ሁለት አሳብ ላለው በመንገዱም ሁሉ ለሚ ወላውል ለዚያ ሰው ከጌታ ዘንድ አንዳች እንዲያገኝ አይም ሰለው» ያዕ. 1÷7 ይለናል፡፡ የሰው ልጅ የእግዚአብሔርን ርዳታ አግኝቶ ሕይወቱን ለማስተካከል ወደ እርሱም ለመቅረብ እንዲችል መወሰን ያስፈልገዋል፡፡ ሁለት ሀሳብ መሆንንም ማራቅ አለበት፡፡

## እንዴት እንለወጥ?

መንፈሳዊ ሰው ራሱን እንዴት ማስተካከል እንዳለበት ማወቅ የመጀመ ሪያ ተግባሩ መሆን አለበት፡፡ ችግሮቹን መፍታት የሚችለው ይኽንን ሲያውቅ ሲረዳ ነው፡፡ እንዴት መንፈሳዊ መሆን እንደሚችል ሲረዳ እንቅፋቶቹን እያስወገደ ይቀርባል፡፡ የጎደለውንም ያሟላል፡፡ ከዚህ ቀጥሎ እንዴት መለወጥ እንደሚቻል በየተራ እንመለከታለን፡፡

- ቃለ እግዚአብሔርን በመስማት

በየዕለቱ ቃለ እግዚአብሔርን የሚሰማ ሰው በመንፈሳዊ ሕይወቱ ያለበትን ጉድለት ያስተካክላል፡፡ ምግባር ትሩፋትም እየጨመረ ይመጣል፡፡ ቅ.ዳዊት የእግዚአብሔርን ሕግ በቀንና በሌሊት የሚያስብን ሰው «በውሃ ፈሳሾች ዳር እንደተተከለች ፍሬዋን በየጊዜው እንደምትሰጥ ቅጠልዋም እንደማይረግፍ ዛፍ ይሆናል» መዝ.1÷3 የሚለውም ለዚህ ነው፡፡ ውሃ ዳር ያለ ዛፍ ሁልጊዜ እንደሚያፈራ ከቃለ እግዚአብሔር የማይለይ ክርስቲያንም ከሕይወቱ በጎ ምግባር አይጠፋም፡፡ ሦስት ሺህ የሚሆኑ ሰዎች በእነ ቅዱስ ጴጥሮስ ስብከት ልባቸው ተነስቶ «ምን እናድርግ?» ብለዋል፡፡ እነዚህ ሰዎች ጉድለታቸውን ለመሙላትና የሚባሉትን ለመሆን ራሳቸውን ያዘጋጁት በመማራቸው በመሰበካቸው ነው፡፡ ሐዋ.2÷37፡፡ ሐር ሻጭ የነበረችው ልድያ በቅዱስ ጳውሎስ ስብከት ልቧ ስለመነካቱ ተጽፎ እናገኛለን፡፡ ይህም የሆነው ቃለ እግዚአብሔርን በመስማቷ ነው/ ሐዋ.16÷4፡፡ ከዚህ አንጻር መንፈሳዊ ሰው ራሱን ለማስተካከል ሁል ጊዜ ቃለ እግዚአብሔርን መስማት ራሱንም በዚያ ውስጥ አስገብቶ መመርመር ይኖርበታል፡፡

- ምሥጢራትን በመፈጸም

ለመለወጥ የሚሻ ሰው እግዚአብሔርን በረከቱን እንዲያሳድርበት በዚህም ሕይወቱ እንዲስተካከል ምሥጢራትን መፈጸም አለበት፡፡ ለምሳሌ መንፈሳዊ ለመሆን የቀረበ ሰው ንስሐ ሊገባ ቅዱስ ሥጋውን ክቡር ደሙን ሊቀበል ይገባዋል፡፡ ጌታችን በወንጌል «ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ በእኔ ይኖራል፡፡ እኔም በእርሱ እኖራለሁ» ዮሐ 6÷56 የሚለን ለዚህ ነው፡፡ ሥጋውን ከሚበላ ደሙን ከሚጠጣ ጋር አብሮት እንደሚኖር ገልጿል፡፡ ስለዚህ ሰው ምሥጢራትን ሲፈጽም ከእግዚአብሔር ጋር መኖር ይጀምራል ይኽ ደግሞ በሕይወቱ እንዲለወጥ ይረዳዋል፡፡

- በጸሎት

አባቶቻችን የጎደላቸውን የሚያሟሉት ችግራቸውን የሚያስወግዱት በጸሎት ነበር፡፡ እግዚአብሔር የለመኑትን የማይነሳ አምላክ በመሆኑ ከኃጢአት በቀር የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ እየሰጠ አስደስቷቸዋል፡፡ ይኽንን ረድቶ መንፈሳዊ ሰው ስለ እምነቱ ፅናት ስለመንፈሳዊ ሕይወቱ ጥንካሬ... መጸለይ ይኖርበታል፡፡ አባቶቻችን «እምነት ጨምርልን» ብለው ስለመለመናቸው ተጽፎ የምናገኘውም ለዚሁ ነው፡፡ ይኽ ልመናቸው ሰው ስለ ሥጋዊ ሕይወቱ ብቻ ሳይሆን በመንፈሳዊ ሕይወቱም የጎደለውን ለሟሟላት መለመን እንዳለበት ያሳየናል፡፡

አንዳንድ ሰው ለጸሎት ወደ ቤተ ክርስቲያን በሄደ ጊዜ በሥጋ ያለውን ችግሩን ብቻ አንሥቶ ይለምንና ይመለሳል፡፡ አኗኗሩ ሲታይ ግን በመንፈሳዊ ሕይወቱም ብዙ ጉድለት ይኖርበት ይሆናል፡፡ በዚህ የተነሣ ውስጡ ሰላም አይሆንም፡፡ ገንዘብ እያለው ሥጋዊ ቁሳ ቁስ ሁሉ ተሟልቶለትም ያዝናል፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ችግር እንዳይከሰት ክርስቲያን አስቀድሞ ጽድቁን መሻት አለበት፡፡ ማቴ 6÷33፡፡ ስለመንፈሳዊ ሕይወቱ መስተካከል መለመን ይገባዋል፡፡ ይኽን ካስተካከለ ሌላው ሁሉ ስለሚጨመርለት ደስተኛ መሆኑ አይቀርም፡፡ በመሆኑም መንፈሳዊ ሰው ለመለወጥ መጸለይ መለመን ደጅ መጥናት ይኖርበታል፡፡

- በመታገስ

እግዚአብሔር እኛ እንዳሰብነው የሚሠራበትም የማይሠራበትም ጊዜ አለ፡፡ ለምሳሌ እኛ ስጠን ብለን የጠየቅነውን ነገር ባሰብነው ሰዓት የሚሰጥበት ጊዜ አለ፡፡ በሌላ በኩል ባልጠነውና በነገርነው ሰዓት ሳይሆን አቆይቶ ትዕግስታችንን ተመልክቶ አይቶም የሚሰጥበት ወቅት አለ፡፡ ስለዚህ መንፈሳዊ ሰው እየተማረ እየጸለየ ለመለወጥ እየሞከረ የሚፈልገውን ለውጥ ባያገኝ እንኳን መታገስ አለበት፡፡ እግዚአብሔር ሥራ የሚሠራበት ጊዜ እስኪደርስ ሊጠብቅ ይገባዋል፡፡ ይህ ሲባል እግዚአብሔር ስላልፈቀደልን ነው እያለ ይዘናጋና ከኃጢአት አይለይ ማለት አይደለም፡፡ ነገር ግን የራሱ ጥረት እያደረገ በዚህ ሁሉ የሚፈልገውን መሆን ቢያቅተው እግዚአብሔርን ደጅ እየጠና መጠበቅ አለበት ለማለት ነው፡፡

በመሠረቱ ክርስትና በአንድ ጊዜ ፍፁም የሚሆኑበት ሕይወት አይደለም፡፡ እንደጀመሩ መብቃትም አይቻልም፡፡ ስለዚህ መንፈሳዊ ሰው መቸኮል የለበትም፡፡ዕድገቱ ትክክለኛ እንዲሆን ቀስ እያለ እየታገሠ ቢጓዝ መልካም መሆኑን መረዳት ይገባዋል፡፡ አባቶቻችን ሐዋርያት ጌታችን እግር ሥር ተቀምጥው እየተማሩ ድውይ ያልፈወሱበት ጊዜ ነበር፡፡ የእምነታቸው መጉደል እየተነገራቸውም ተስፋ ሳይቆርጡ ከእርሱ ሳይለዩ በመጠበቃቸው በመጨረሻ ምሉአን ሆኑ፡፡ ፍርሃት ርቆላቸው ደፋሮች በመሆን ዓለምን ዞረው አስተማሩ፡፡ ከዚህ አንጻር መንፈሳዊ ሰው በአንድ ጊዜ የሚፈልገውን ባያገኝ እንኳ መታገሥ አንድ ቀን እንደ ሚሟላለት በማሰብ መጽናት ይገባዋል፡፡ ቅዱስ ጴጥሮስ በመልእክቱ «ለጥቂት ጊዜ መከራ ከተቀበላችሁ በኋላ እርሱ ራሱ ፍጹማን ያደርጋችኋል÷ያበረታችሁማል» 1ጴጥ 5÷10 እንዳለ ጥቂት ጊዜ ከተፈተነ በኋላ ሊያጸናው ስለሚችል በፈጣሪው ታምኖ መቆየት ይኖርበታል፡፡

- መጻሕፍትን በማንበብ

ቅዱሳት መጻሕፍት ሐዋርያው እንዳለው ፍፁማን ያደርጋሉ፡፡ ለበጎ ሥራም ያዘጋጃሉ፡፡ 2ኛ ጢሞ 3÷16፡፡ ስለዚህ መንፈሳዊ ሰው በየጊዜው ሊያነባቸው ይገባል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስን እንዲሁም ድርሳናትን የሚያነብ ሰው የሚያነባቸው ታሪኮች /የቅዱሳን ገድል/ ለተጋድሎ ሊያነሳሳውና ወደ በጎ ሥራ ሊመራው ስለሚችል መጻሕፍትን ማንበብ አለበት፡፡

ከላይ እንዳየነው ቅዱስ ጳውሎስ ጢሞቴዎስን ከልጅነትህ ጀምሮ ቅዱሳት መጻሕፍትን እየተማርህ አድገሃል ብሎ መስክሮለታል፡፡ ራሱም ገማልያል እግር ሥር ተቀምጦ መጻሕፍትን አጥንቷል፡፡ ይኽ የሚያሳየን አባቶችን የቤተ ክርስቲያን አደራ ለመረከብ ያበቃቸው መጻሕፍትን መመርመራቸው እንደሆነ ነው፡፡ ስለዚህ ከራሱ አልፎ ሌላውን እንዲያድን ወይም በመንፈሳዊ ሕይወቱ እንዲለወጥ አስቦ ወደ ቤተክርስቲያን የቀረበ ሰው መጻሕፍትን ማንበብ ይኖርበታል፡፡

- በግልጽነት በመመካከር

መንፈሳዊነትን ይዞ ለመቆየት በየጊዜው ራስን ለማሻሻል የሚያስብ ሰው ከንስሐ አባቱ ከመንፈሳዊ ወንድሞቹ ጋር ቢመካከር መልካም ነው፡፡ ይህንንም ሲያደርግ ግልጽነት በተሞላ ሁኔታ መሆን አለበት፡፡ ይኽ መመካከሩ ለእርሱ ያልታየው ጉድለት ለሌሎች ሊታይ ስለሚችል ጉድለቱን ያሳውቀዋል፡፡ ከዚህ ውጭ እርሱ ያልደረሰበትን መፍትሔ ሌሎች እንዲጠቀሙበትም ያደርገዋል፡፡ ቅዱስ ዳዊት በመዝሙሩ «ወንድሞች በኅብረት ቢቀመጡ መልካም ነው» መዝ 136÷1 እንዳለ በኅብረት መሥራት በአንድነት እየተመሳከሩ መጓዝ ለመንፈሳዊነት ትልቅ ጠቀሜታ አለው፡፡

አንዳንድ ሰው ይኽንን ሳያደርግ ከሌሎች ጋር ሳይመካከር ብቻውን ለመጓዝ የሚሞክር አለ፡፡ ችግሩን ገልፆ ስለማይናገር መፍትሔውንም ለብቻው ማመንጨት ስለማይችል ሁል ጊዜ በፈተና የሚኖር አይጠፋም፡፡ ነገር ግን ከዚህ ይልቅ መንፈሳዊ ሰው እየተመካከረ ቢጓዝ በመንፈሳዊነቱ መለወጡ አይከብደውም፡፡

ከብዙ በጥቂቱ እንደተመለከትነው መንፈሳዊ ሕይወት በበጎ መለወጥን የሚሻ ዕለት በዕለት እየጨመርን የጎደለንን እያሟላን የምንጓዝበት ሕይወት ነው፡፡ ስለዚህ መንፈሳዊ ሰው ራሱን ለማስተካከል ከትናንት ዛሬን ለማሻሻል መጣር ይኖርበታል፡፡ ይኽ ጽሑፍ ስለክርስቲያናዊ የሕይወት ለውጥ የተወሰኑ መነሻ ሐሳቦችን ለመስጠት ተጻፈ እንጂ ሙሉ ሐሳቦችን ይዟል ለማለት አይቻልም፡፡ ይኽን አስቦ ጽሑፉን የሚያነብ ማንኛውም ክርስቲያን ካነበበ በኋላ በዚህ ዙሪያ ከቤተክርስቲያን አባቶች ወንድሞችና እኅቶች ጋር የበለጠ መመካከር ይኖርበታል፡፡

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር*

# የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ትምህርት

ክአሉላ ጥላሁን

**ባለፈው እትማችን የቤተ ክርስቲያንን ሥርዓተ ትምህርት ምንነትና አስፈላጊነት፣ አከፋፈሉንና ከንባብ ቤት እስከ ቅኔ ቤት ያሉትን ቤተ ጉባኤያት ገጽታ መዳሰሳችን ይታወሳል። በዚህ በሁለተኛውና በመጨረሻው ክፍል ዝግጅታችን ከፍተኛውን የመጽሐፍ ቤት ሥርዓተ ትምህርት ተቋማቱ ዛሬ ያሉበትን አኳኋንና ሊወሰዱ የሚገባቸውን የመፍትሔ እርምጃዎች በደምሳሳው እንቃኛለን።**

## 1. መጽሐፍ ቤት /ትርጓሜ መጻሕፍት/

አንድ ተማሪ ከቅኔ ት/ቤት ወጥቶ ወደ ከፍተኛው የመጽሐፍ ትርጓሜ ት/ቤት ሲገባ በዕድሜው የበሰለ በአእምሮ የተደላደለ የግእዝን ቋንቋ ጠንቅቆ ያወቀ መሆን ይገባዋል። ምክንያቱም የትርጓሜው አንድምታና ሐተታ ረዥምና ሰፊ ከመሆኑ የተነሣ እርስ በእርስ ማገናዘብ፣ የተዛባውን ንባብ ማቃናትና ማስተካከል አድካሚ በመሆኑ አስተዋይ ጭንቅላት ስለሚጠይቅ ነው። የመጽሐፍ ቤት ተማሪ በጠባዩ ግብረ ገብነት ያለው የመናኝነት መልክ የሚታይበት፤ ትምህርቱን በሚገባ አጠናቅቆ በመምህርነት የሚገለጠው በዕርግና ዘመኑ ስለሆነ መጽሐፍ ቤት መግባት እንደምነና ይቆጠራል፤ አንዳንድ ሊቃውንትም «መጽሐፍ ቤት ሲገባ እንደሎጥ ሚስት ዞሮ ለማየት አይደለም» የሚሉት ለዚህ ነው።

ምንጊዜም ቋንቋቸው እንዳይለወጥ ምሥጢር እንዳይፋለስ ዓይናቸው መጽሐፍ ከመመልከት አእምሮአቸው ምሥጢር ከማሰራሸት አይለይም። ሌሎች ሊቃውንት ምንም ውሉን ቢያውቁት ትንሽም ትልቅም ክርክር በመካከላቸው ከተነሣ «ከመጽሐፍ መምህር እንሂድ» በማለት ነገሩ ያልቅ ክርክሩም ይበርድ ነበር። ይህም ያላቸውን የላቀ አስተያየትና ጥበብ እንዲሁም ክብር ያሳያል። ይሁንና በዋና ዋና ከተሞች ስመ ጥር በሆኑ አድባራትና ገዳማት/ ካልሆነ በቀር በየደብሩና በየገጠሩ በብዛት ከሚገኙት የዜማና የቅኔ መምህራን አንጻር የመጻሕፍት መተርጉማን ቁጥር አናሳ ነው። ከተመርጉማኑም መካከል ቢሆን የሐዲሳት መጻሕፍት መተርጉማን ከብሉያት ከሊቃውንትና ከመጻሕፍተ መነኮሳት ይልቅ አንጻራዊ ብዛት እንዳላቸው ይነገራል።

የመጽሐፍ ቤት ትርጓሜ መጻሕፍትን ብቻ ያይደለ የቀደሙትን የቅኔና የዜማ ትምህርቶች በሊቅነት ማዕረግ አስመስክረው የሚወጡበትም ነው። ለምሳሌ ወጣንያን በንባብ ማዕከላውያን በዜማ የተማሩትን መዝሙረ ዳዊት በትርጓሜ ተምረው ምሁር የሚሰኙት በመጽሐፍ ቤት ነው። በአጠቃላይ ይህ ቤተ ጉባኤ መጻሕፍትን አስተካክሎ ማንበብና መተርጎምን፤ መሠረተ ሃይማኖት፣ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን፣ የቤተክርስቲያን ታሪክ የመሳሰሉትን ጠንቅቆ ለማወቅ የሚያስችል ከፍተኛ የምርምር ተቋም ነው።

የቅዱሳት መጻሕፍት የአንድም ትርጓሜ ስልት በብሉይ ኪዳን ዘመን ጀምሮ በአይሁድ ዘንድ የነበሩት የአብነት ት/ቤቶች /ታልሙድ/ ሲሠራበት የኖረ ሲሆን ከሕገ ኦሪት ጋር ሊቃውንተ ኦሪት ከቀዳማዊ ምኒልክ ጋር አብረው ወደ ሀገራችን ከገቡ በኋላ ይዘዋቸው የመጡትን መጻሕፍተ ኦሪት /ስምንቱ ብሔረ ኦሪት፣መጽሐፈ ኩፋሌ፣ መጽሐፈ ሄኖክ፣መጽሐፈ ኢዮብና እስከ ሰሎሞን ዘመን ድረስ የሚተርከውን መጽሐፈ ነገሥት /ከዕብራይስጥ ወደ ግእዝ በአንድምታ በመተርጎም ሲያስተምሩት ስለኖሩ ትርጓሜ መጻሕፍት ከዚያን ዘመን አንሥቶ በኢትዮጵያ እንደተጀመረ ይታመናል። ከጊዜ ወደ ጊዜም በእነ አባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን፣በእነ ቅዱስ ያሬድና በመሳሰሉት አባቶች ትጋት ተስፋፍቷል።

ይሁንና ትርጓሜ መጻሕፍት አካል ገዝቶ፣መልክ አግኝቶ፣ አደባባይ ወጥቶ ደቀመዝሙር አብዝቶ የአሁኑን ፍሊጋ ለመያዝ የበቃው በጎንደር ዘመነ መንግሥት ነው። መጻሕፍት የነጠላ ትርጓሜና የአንድምታ ትርጓሜ ዓይነት ስልት ያላቸው ሲሆን፤ ነጠላ ትርጓሜ የምንለው ሙሉ ንባቡን /ዘይቤውን/ በቁጥሩ ያለምንም ሐተታ መተርጎም፤ ከአንድ ቋንቋ ወደ ሌላ ቋንቋ መመለስ ማለት ነው። በዚህ መልክ ብዙ ቅዱሳት መጻሕፍት ከውጭ አገር ቋንቋዎች ወደ ግእዝ ከግእዝም ወደ አማርኛ ተተርጉመዋል።

በመጽሐፍ ቤት የሚሠራበትና ንባብ ለማቃናት ምሥጢር ለማሰራሸት የሚያመቸው ግን የአንድምታ ትርጓሜ ስልት ነው። አንድምታ ትርጓሜ የሚባለው አንድ ጊዜ ከተተረጐመ በኋላ እንደገና አንድም እያለ እስከ 10 እና 16 ጊዜ የሚያወርዱት አወራረድ፣ የሚሰጡት ሐተታ ነው። በግእዝ ቋንቋ አው፣ቦ ይላል። ፍችውም ሌላ ይህን ይህን የመሰለ ትርጉም አለው እንደ ማለት እንደማማረጥም ነው።

በአማርኛም አንደኛ፣ ሁለተኛ ብሎ እንደመተንተን ነው። በዚህም አገባብን ወይንም ዘይቤን ብቻ በመጠበቅ አለያም ምሥጢሩን በመከተል ወዲያውም ደግሞ ታሪክ በመተረክ፣ምሳሌ በመመሰል ሐተታ በማተት ለእያንዳንዱ ኃይለ ቃል ሞያ ሰጥተው ይተረጉማሉ፤ የተሠወረውን ገልጠው ያስረዳሉ።

የትርጓሜ መጽሐፍ ትምህርት በንግግር መልክ አንድ ጊዜ ብቻ ተሰምቶ የሚያዝ እንጂ እንደ ዜማና ቅኔ ቤት ቃል በቃል የሚሸመደድ ወይም የሚነገር ትምህርት አይደለም። የመምህሩ የንግግር መልክ ማሄድ ይባላል። የጉባኤውም ዓይነት በመጽሐፍ ክፍል ብቻ ሳይሆን በሰዎች ልክ ይወሰናል። ሁልጊዜ በሚ.ት የማይታጐሉ ጉባኤዎች አሉ፣እነሆንም አልፎ አልፎ ደቀ መዛሙርቱ በትምህርት መልክ ይከታተሏቸዋል። ሁለት ሦስት ጊዜ ስለሚመላለሱ በቶሎ ያስቀሯቸዋል። እንዲህም እያለ በተዘለቀና በተከለሰ ቁጥር ተከታትለው ሊያጠኑ ትርጉሙን ሊያስተና ይችላሉ። የሚኬድላቸው ጉባኤ በጆሮ አንድ ጊዜ ሰምቶ ማስቀረት ከባድ ስለሆነ፣ በየሰዓቱ ጆሮአቸውን ቀቅረው የልቡናቸውን ሀሳብ ሰብስበው መዋል ግድ ይሆንባቸዋል፤ በኋላም ለብቻቸው ተቀምጠው የተነገራቸውን ሁሉ በልባቸው እያሰላሰሉ በብዙ ድካም ያጠኑታል። በቃል ያለ ይረሳል፤ በመጽሐፍ ያለ ይወረሳል እንደሚባለው የደከሙበት ትምህርት እንዳይጠፉቸው በጽሑፍ አስፍረው ይደጋታል። ለመምህሩ የሚከብደው ለእያንዳንዱ ተማሪ እንደሚሸ ለዚያውም ሁሉ አማርኛው እንዳይለወጥ ምሥጢሩ እንዳይፋለስ እንዳገኘ እንዳይናገር ከፍ ያለ ጥንቃቄ ማድረግ ነው።

መምህሩ ጊዜውን እንደ ጉባኤው ስፋት ሊወስን ይችላል። ትምህርቱ ለመምህሩም ለተማሪውም አንድ በመሆኑ በቀን ብቻ ይማራሉ ያስተምራሉ እንጂ በሌሊት ጉባኤ የለም።

የትርጓሜ መጻሕፍት ትምህርት አራት ክፍሎች አሉት፤ ስለዚህም እነዚህን ሞያዎች አጠናቅቀው የሚያውቁት ሊቃውንት «የአራት ጉባኤ መምህር እጓሌ፣አራት ዓይና» የሚል የሊቅነት ስም ይሰጣቸዋል። ይኸውም ፍጹም ዕውቀትን፣ምሥጢር ተመራማሪ፣ኃይለ ቃሉን አነጻጻሪ፣ በላኤ መጻሕፍት ማለትን የሚያመለክት የአድናቆት ጽዋዕ /አጠራር/ ነው። አራቱ ጉባኤያት የሚባሉትን እንደሚከተለው ዘርዝረን እንመለከታቸዋለን።

1. **መጻሕፍተ ብሉያት፡–** በቁጥራቸው 46 ሲሆኑ የሕግ፣የታሪክ፣የመዝሙር /የጥበብ ወይም የቅኔ/ እና የትንቢት መጻሕፍት በተባሉ አራት ዋና ዋና ክፍሎች ይመደባሉ። እኒህን አጠናቅቆ ያወቀ ምሁር መጋቤ ብሉይ እየተባለ ይጠራል። አንድ የግእዝን ቋንቋና ቅኔውን በሚገባ ያወቀ ደቀ መዝሙር የብሉያትን ትርጓሜ በስድስት ዓመት አጥንቶ በተጨማሪ አንድ ዓመት አደላድሎ በአጠቃላይ በሰባት ዓመት ውስጥ ለመምህርነት ሊበቃ ይችላል።

2. **መጻሕፍተ ሐዲሳት፡–** በቁጥራቸው 35 ሲሆኑ በይዘታቸው የወንጌል፣ የታሪክ፣ የመልእክት ወይም የትምህርት እና የትንቢት በሚባሉ አራት ዋና ዋና ክፍሎች ይመደባሉ። ይሁንና በጉባኤ መልክ በሦስት ይከፈላሉ። እነርሱም ሀ/ አርባዕቱ ወንጌል ለ/ 14 ቱ መልእክታተ ጳውሎስ ሐ/ ግብረ ሐዋርያት ፣ሰባቱ መልእክታትና የዮሐንስ ራእይ /አቡቀለምሲስ/ ወይም ሠለስቱ ሐዲሳት የሚባሉት ናቸው። እነዚህም እያንዳንዳቸው በዓመት ሁለት ጊዜ ያህል ይዘለቃሉ። ከሐዲስ ኪዳን የአንድምታ ትርጉም ብዙ ጊዜ የሚወርደው እስከ 16 ጊዜ ድረስ ሐተታ ያለው ነው። ይኸውም በዮሐንስ /ራእይ 19÷11/ ላይ የሚገኘው «ፈረስ ፀዓዳ» የሚለው ታላቅ አወራረድ ነው። እርሱን ያወቀ ደቀ መዝሙር የሐዲስ መምህር፣ መጋቤ ሐዲስ ይባላል። ከላይ እንደተገለጠው ግእዝንና ቅኔውን በደንብ ያወቀ ደቀ መዝሙር ከአራት እስከ አምስት ዓመት የሐዲሳትን ትርጓሜ አጠናቅቆ በተጨማሪ አንድ ዓመት በማደላደል በአጠቃላይ ከአምስት እስከ ስድስት ዓመት መምህር ለመሆን ይችላል።

3. **መጻሕፍተ ሊቃውንት /ሊቅ/ ፡–** እኒህ መጻሕፍት እንደ ፍትሐ ነገሥት /የሕግና የሥርዓት መጽሐፍ/፣መጻሕፍተ ቄርሎስ፣መጻሕፍተ ዮሐንስ አፈወርቅ፣ሃይማኖተ አበው፣14ቱ መጻሕፍተ ቅዳሴያት ሌላም እኒህን የመሳሰሉ ናቸው።

ፍትሐ ነገሥት በፍትሕ መንፈሳዊ ክፍሉ 22 አናቅጽ፣ በፍትሕ ሥጋዊ ክፍሉ 30 አናቅጽ የያዘ የሕግና የሥርዓት መጽሐፍ ነው። ለአውግዞተ አርዮስ በዘመነ ቆስጠንጢኖስ በኒቂያ የተሰበሰቡ 318ቱ ሊቃውንት፣ከእነርሱም በኋላ በየጊዜው የተሰበሰቡ የዓለም ቤተ ክርስቲያንና የብሔራዊ ቤተ ክርስቲያን ሲኖዶሶች /ጉባኤያት/ ውሳኔ ነው። በቀጥተኛ ትርጉሙ የነገሥታት ፍርድ ማለት ሲሆን የሃይማኖትም የአስተዳደርም ኃላፊነት የነበራቸው መንፈሳውያን ነገሥታት የመጨረሻ ፍርድ የሚሰጡበት /የሕግ መድበል/ ነበር። ከዐረብኛ ወደ ግእዝ ቋንቋ የተተረጎመው «ዘተሰምየ ቆስጠንጢኖስ» በተባሉት በአፄ ዘርዐ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት ነው። የፍትሐ ነገሥት ዐዋቂ ሊቁ የሚባል የማዕረግ ስም ይሰጠው ነበር። መጻሕፍተ ሊቃውንት ንባባቸው ጠንከር ያለ፣ ብዛትና ጥልቅነት ያላቸው በመሆናቸው ትርጓሜያቸውን ለማጠናቀቅ ከ6–8 ዓመታት ይወስዳል። ሁሉንም የዘለቀና ያወቀ መምህር ደግሞ ሊቀ ማእምራን ወይም ሎጋቤ ማእምራን ይባላል። የቁጥር መጻሕፍት /አቡሻህር ባሕረ ሐሳብ ወይም መርሐ ዕውር /ከፍተኛ ትምህርት/ ቢሆኑም ከአንዳንድ ሊቃውንት በቀር ሁሉም አይማሯቸውም። የውዳሴ ማርያምንና የቅዳሴ ማርያምን፣የኪዳንን፣የትምህርተ ኅቡአትን፣የጸሎተ ሃይማኖትን ትርጓሜ ግን የማንኛውም መጽሐፍ ተርጓሚ መምህር ማወቅ ይኖርበታል።

4. **መጻሕፍተ መነኮሳት**

የአበው መነኮሳትን መከራቸውን ገድላቸውንና ክብራቸውን የሚናገሩ ሦስት መጻሕፍትን ማለትም ማር ይስሐቅ፣ አረጋዊ መንፈሳዊና ፊልክስዩስ የተባሉትን ያቅፋል። እያንዳንዳቸውን በአንድ፣ በአንድ ዓመት መፈጸም ስለሚቻል በጠቅላላው ሦስት ዓመታትን እንደሚወስዱ መምህራን ይናገራሉ። እነርሱን ጠንቅቆ ዐውቆ ለማስተማር የሚችል መምህር መጋቤ ምክር ይባላል።

በመጽሐፍ ቤት የሚገኙ ደቀ መዛሙርት በዚህ መልክ ተምረው ምሥጢር አደላድለው አብነት ሁነው ወጥተው የሚያስተምሩ ነበሩ። አንዳንድ ተማሪዎች ከአንድ መምህር ሲቀጽሉ ኖረው ወደ ሌላው ተዛውረው ያስፋፋሉ። ከአንዱ ቤተ ጉባኤ በአንድ ሞያ ቢመረቁ ም በዚያ ዘርፍ ብቻ ሳይገቱ፣የሚያስተምሩበት ጉባኤ ስፋት ሳይወስናቸው የጠፋውን በመፈለግ የደከመውን በማጽናት ከዕውቀት ወደ ዕውቀት ይራመዱ ስለነበር በርካታ አራት ዓይናዎች ነበሩን። እነ አራት ዓይና ጎሹ፣መምህር ፈላታዎስ፣መምህር ጽላሉ ወ/ማርያም፣በጎንደር መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን ያስተምሩ የነበሩትና በ1960 ዓ.ም. ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ የክብር ዶክትሬት ዲግሪ የተቀበሉት አለቃ አየለ ዓለሙ ለአብነት የሚጠቀሱ ናቸው።

ከእነዚህ ሌላ ብዙዎች በዚያው በተማሩበት ሞያ «ተናገር በከንፈሬ፣ ተቀመጥ በወንበሬ፣እኔን መስለኽ እኔን አኽለህ አስተምር» ተብለው ተመርቀው ማስተማር ይጀምራሉ። እናት አገራቸውንና እናት ቤተ ክርስቲያናቸውን በታማኝነት ያገለግላሉ። ከዕለት ጉርስ ከዓመት ልብስ በስተቀር ለሞያችን ተመጣጣኝ የሆነ ደመወዝ ክፈሉን፣በጀት ደልድ ሉልን ሕንጻ ሥሩልን ሳይሉ ከሚበላው ቆርሶ ከሚጠጣው ቀንሶ በነጻ ያበላቸውንና ያጠጣቸውን ምእመን ልጆች በደጀ ሰላም፣በመቃብር ቤትና በዛፍ ሥር ወንበር ተክለው አትሮንስ ዘርግተው በነጻ ያስተምራሉ። ይህም በጸጋ ያገኛችሁትን በጸጋ ስጡ የሚለውን ወንጌላዊ መመሪያ ይተረጉማል።

ተማሪው ሠርከ ኅብስት ለማግኘት /ለልመና/ በጠቅላላው ለሕይወቱ ከተመቸው መምህሩ ለሚፈራረቅባቸው ማግኘትና ማጣት ግምት አይሰጡትም። ለሌሎች ላለመክበድ ራሳቸው እየቆፈሩ እያረሱ የሚያስተምሩ ነበሩ። አሉም። እንዲያውም ተማሪውን በአራቱ ማዕዘናትና በእርሻቸው መካከል አቁመው እያረሱ በተመላለሱ ቁጥር የሚያስተምሩም ነበሩ። እንዲህ ያለው የመምህር የትሩፋት አገልግሎት እና የተማሪው የአስርተ ዓመታት የነጻ ትምህርት ዕድል የቤተክርስቲያን የሕልውናዋ የማዕዘን ደንጊያ ሆኖ ኖሯል፣ ይኖራልም።

5. **ጥንታዊው ሥርዓተ ትምህርት ዛሬ**

ጥንታዊው ትውፊታዊ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ትምህርት እስከ 19ኛው መ/ክ/ዘ መግቢያ በሀገራችን ብቸኛው የትምህርት መስክ ስለነበር የሁሉም ትምህርት ፈላጊ የምርጫ ትኩረት ወደ አብነት ት/ቤቶች ነበር። በተጠቀሰው መቶኛ ክፍለ ዘመን መግቢያ ላይ ግን ይህን ትኩረት የሚለውጡ ሁኔታዎች መከሰት ጀመሩ። የመጀመሪያው ክስተት የዘመናዊ ሥልጣኔ መስፋፋት፣ ይህንንም ተከትሎ በመጣው የመንግሥታዊ አስተዳደር፣ የምርትና የማኅበራዊ አገልግሎት ተቋማት በከተሞች መወሰን ሳቢያ ሁለት ዓይነት ትውልድ መፈጠሩ ነው። የከተማና የገጠር።

አብዛኛው ከተሜ የሚኖረው በብዛት በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ከሚገኙት የአብነት ት/ቤቶች ርቆ ሆነ። ከከተሞች ጋር አብረው የተተከሉት አድባራትና ገዳማት የትምህርት አሰጣጥ ስልታቸው በዘመናዊ ት/ቤት እንደሚሰጠው የከተማውን የኑሮ ሁኔታ የጠበቀ አልሆነም። በቃል በመቃብር ቤት፣በየደጀ ሰላሙ ዙሪያና በየዛፉ ሥር የሚሰጠው የአብነት ትምህርት በመጽሐፍ፣ በክፍሉ ውስጥ መምህር ተቀጥሮለት፣ የመማሪያ ቁሳቁስ ተሟልቶለት እንደሚሰጠው ዘመናዊ ትምህርት የከተሜውን ወጣት ሊስበው አልቻለም። ጠዋት ማታ ቁርስና እራት ተዘጋጅቶለት ከወላጆቹ ሳይለይ ዘመናዊ ትምህርት መማር ሲችል፣ የአብነት ትምህርት ለመማር ግን ቤቱን ትቶ አገር ላገር እየዞረ ለምኖ ማደር ግዴታው ነበር። ይህም ሆኖ በጊዜ ጠበቅ የድርቅና የወረርሽኝ ተፈጥሮአዊ ክስተቶች እንደ መንደር ምሥረታ ያሉ የአስተዳደር ዘዬዎች ምእመኑን ከአብነት ት/ቤቶች አካባቢ በማራቁ ተማሪው የችግሮቹ ሁሉ ገፈት ቀማሽ ሆነ። ሁለት ዓይነት ትውልድ፣ሁለት ዓይነት ት/ቤት÷ሁለት ዓይነት ሥርዓተ ትምህርት።

- የጥንት ተማሪ ሲማር ውሎ፣ይበላል ለምኖ፣
- የዛሬ ተማሪ ሲማር ውሎ ይጠብቀዋል ምግብ በስሎ፣
- የጥንት ተማሪ ታሞ ቢተኛ የለው መዳኛ

የዛሬ ተማሪ ቢያጣ ጤና አለው ሕክምና፣
የጥንት ተማሪ የድካሙ ብዛት፣ሲዞር ስንክራተት፣
የዛሬ ተማሪ ከዚህ ሁሉ ነጻ እንዲያው ቀንጸ ቀንጸ

- በጥንቱ ተማሪ ፀሐይ ትገባለች÷ ፀሐይ ትወጣለች፤

በዛሬ ተማሪ ምድር ትዞራለች÷ትንከራተታለች:: /ጥንታዊ የቆሎ ተማሪ÷ገጽ 1/

በሌላ በኩል ደግሞ 10 እና 20 ዓመታትን በአብነት ት/ቤት የተማረው ወጣት ከተመረቀ በኋላ የሚያገኛት ገንዘብ ከእጅ ወደ አፍ እየሆነች መምጣትም ኑሮን ለማሸነፍ ሲል ወደ ዘመናዊ ት/ቤት እንዲጓዝ ገፋፍቶታል:: በዘመናዊው ሥልጣኔ መሠረትነት የተቋቋሙት የአስተዳደር፣ የአገልግሎትና የምርት ተቋማት ለሥራ የሚቀጥሩት በዘመናዊ ሥርዓተ ትምህርት ያለፈውን በመሆኑ የአብነት ትምህርት የተማረው እንኳን ሳይቀር ቤተክርስቲያንን እየተወ ወደ ሌላ ኑሮ የገባበት አጋጣሚ ነበር::

ከዚህ በተጨማሪ ከዘመናዊ ትምህርት ጎን ለጎን የምእመኑ ልጆች በአጥቢያ ቤተክርስቲያን የአብነት ትምህርቶችን ለመማር ይችሉ ዘንድ ከሰዶሚያቸው፣ከኑሮአቸውና ከሥነ ልቦናቸው ጋር የሚሄድ ወጥ የሆነ ሥርዓተ ትምህርት አልተቀረፀላቸውም:: በበቂ ሥነ ዘዴ የሠለጠኑ መምህራን አልተመደቡላቸውም:: ይልቁንም በከተሞች ውስጥ ባሉት የአብነት ት/ቤቶች የሚማሩት አብዛኞቹ ከገጠሩ የሚመጡቱ ብቻ ሆኑ:: እነርሱም ቢሆን በከተማው ወጣት ዘንድ ያለውን ቅንጦትና የኑሮ መሻሻል እየተመለከቱ ወደ ዘመናዊ ትምህርት ያደሉ ነበር::

ሃይማኖትንና ሃይማኖተኝነትን እንደ ኋላ ቀርነት ይቆጥር የነበረው የክሂደተ እግዚአብሔር ትምህርትና በልዩ ልዩ መልክ ወደ አገራችን የገቡ ሚሲዮናውያን መምህራንም ትውልዱ ከሙዓለ ሕፃናት ጀምሮ እስከ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም ድረስ በሥጋዊ ፍልስፍናና በኑፋቄ ጥቁር ወተት አድጐ አምልኮተ እግዚአብሔርን እንዲረሳና ሥነ ምግባር አልባ እንዲሆን አድርገውታል ለቤተ ክርስቲያን ያለውን ፍቅር ለአባቶቹ ያለው ክብር ስለቀነሰ ወደ ጥንቱ ት/ቤት እንዳይገባ ሌላ ምክንያት ሆነበት:: ብሎም በአብዛኛው የጥንቱን ተማሪ የመማሪያ ስልት እንደ ኋላቀርና አድካሚ እየቆጠረው ትምህር ቱንም አብሮ እየሸሸ የውጭ ባሕልን ብቻ ናፋቂና አድናቂ ሆነ:: እኒህ የሥርዓተ ትምህርት ችግሮች የፈጠሩት የኑሮ፣ አመለካከት፣ የባሕል ጽንፈኛ አቅጣጫዎች ለትውልድ ክፍተት ጥንተ ምክንያት በመሆን አንደኛው ሌላውን ባለማወቁ አንዱ ከሌላው የሚያገኘውን ጥቅም አስቀረው:: በውጤቱም የአበው ትምህርት፣ሥርዓት፣ሥነ ምግባር ክርስቲያናዊ ኑሮና ታሪክ ለዚህ ትውልድ እንዲደርስ ታላቅ አስተዋጽኦ ያደረጉት የአብነት ት/ቤቶቻችን በርካታ ችግሮች ሊጋረጡባቸው ት/ቤቶቹ በአቋም ደረጃ ጥንት እንደነበሩት ናቸው፤ የቤቱ አሠራር፣የተማሪዎች የኑሮ ሁኔታ የመምህራኑ ኑሮና ደሞዝ አልተሻሻለም:: ዘመኑ ሲገፋ እነርሱ ባሉበት ይሄዳሉ:: በዚህም ምክንያት መምህራኑ የዕለት ኑሮአቸውን ለማሸነፍ ወደ እርሻ ሥራ አለያም ወደ ከተማ እየፈለሱ ናቸው:: ደቀ መዛሙርቱንም ያለበቂ ሁኔታ የሚያስቀጽሉት በመኖሪያ ቤታቸው ነው:: በእርግጥም የነበረውን የቅብብሎሽ ሥርዓት /ትውፊት/ በእኛ ዘመን የመጣ ያለ መተዋወቅና የመናናቅ ክፍተት ላጲስ ሆኖ እንዳያጠፋው የደጉ ሳምራዊ ርኅራኄ ሊደርሳቸው ይገባል::

ስለሆነም:-

- ከሁሉ አስቀድሞ በየገጠሩ የሚገኙት የአብነት /የምስክር/ ት/ቤቶቻችንና በውስጣቸው የሚገኙ መምህራንና ተማሪዎች በሚገባ ታውቀው ተመዝግበው ተገቢ ቦታቸውን እንዲያገኙ ማድረግ፤
- ለመምህራኑ መተዳደሪያ ለደቀ መዛሙርቱ መደገፊያ የሚበቃ እርዳታ የሚገኝበትን መንገድ ከበጎ አድራጊ ምእመናን ጋር መወያየት፤
- አብነት ት/ቤቶች ያሉባቸው ታላላቅ አድባራትና ገዳማት ይዞታቸው ተጠብቆ በልማት ራሳቸውን የሚችሉበትን መንገድ ማመቻቸት፤
- የአብነት ት/ቤቶችን ነባር ሥርዓተ ትምህርት በማጎልበት፤ በሥርዓተ ትምህርቱ የሚመሩ የመማሪያ መጻሕፍት እየተዘጋጁ መምህራን እንዲያስተምሩባቸው ተማሪዎች እንዲማሩባቸው፣ እንዲያውቋቸው ለተተኪው ትውልድ ሊተላለፉ በሚችሉበት ሁኔታ ማሠራጨትና በቤተ መጻሕፍት እንዲቀመጡ ማድረግ፤
- በየቤተ ጉባኤው የትምህርት ዓይነቶች የተሟላ አቀራረብ እና በቂ ምስክርነት ሊሰጡ የሚችሉ የአብነት ት/ቤቶች በጥናት ተለይተውና ደረጃ ወጥቶላቸው ዘመናዊ ተቋማዊ አደረጃጀት፣ የማዕከላዊ አስተዳደር ተጠየቅ ያለው የበጀት ድልድል የመምህራንና የተማሪዎች ይዞታ እንዲኖር፤ ለሊቃውንቱ የተቀናጀ አገልግሎትና ለደቀ መዛሙርቱ መንፈስ ጠንካራ ተተኪነት ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል:: ለዚህም በአንድ ወቅት የነገረ መለኮት ማዕከላት የነበሩትንና ዛሬ ደግሞ ታላላቅ መካነ አእምሮ ከመሆን የደረሱትን የካምብሪጅና የኦክስፎርድ ዩኒቨርስቲዎችን ዕድገት መመልከት ይቻላል::
- ደቀመዛሙርቱ ከወንበር /የሃይማኖት/ ትምህርታቸው በተጨማሪ የጊዜያቸውን ገጽታ የሚያወቁበትን መንገድ ማመቻቸት፤
- የአብነት መምህራኑና ደቀመዛሙርቱ እንዲሁም የቤተ ጉባኤው ሥርዓተ ትምህርት /የትምህርቱ አሰጣጥና ሂደት/ በድምመጽና በምስል እየተቀረፀ ቢቀምጥ፤
- ወጣቱ ከኑሮው ጋር የሚሄድ፣ በአጭር ጊዜ በአንድ ቦታ ትምህርተ ቤተክርስቲያንን ሊያገኝ የሚችልባቸው ሰንበት ት/ቤቶችም በትምህርት አሰጣጣቸውና በአባላት ይዞታቸው የጥንቱን የአብነት ትምህርት ደረጃ በደረጃ የሚያካትቱበትን መንገድ ቢያመቻቹ፣ይህን ለጀመሩትም ሰፊ አስተዳደራዊና ሙያዊ ድጋፍ ቢደረግላቸው::
- አሁን አሁን በተለይ በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኙ አድባራትና ገዳማት እየተስፋፉ በመጡት የአንደኛ የመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃና የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ዘመናዊ ት/ቤቶች የጥንቱ የአብነት ትምህርት መደበኛ የሥርዓተ ትምህርቱ አካል ሆኖ በተጓዳኝ የሚሰጥበት፣ በዳግማዊ ምኒልክ መታሰቢያ የመምህራንና የቀሳውስት ማሠልጠኛ እንዲሁም ባሳለፍነው ዓመት አጋማሽ የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ በዲፕሎማ ፕሮግራም እንደጀመሩት ያለ በማታውም ክፍለ ጊዜ ዕድሉን አጥቶ ወይም በሥራና በአገልግሎት ምክንያት አላመችብሎት ላልተማረው ትውልድ የአብነት ትምህርቶች ቢሰጡ ባለመንታ ጥቅም ተቋማት ለመሆን ይችላሉ::
- የተሻለ ዘመናዊ ይዞታ /አስተዳደር/ ያላቸውን የቤተ ክርስቲያናችን ማዕከላዊ የካህናት ማሠልጠኛዎች፣ በየአህጉረ ስብከቶች የሚገኙ የራስ አገዝ የካህናት ማሠልጠኛዎች፣ መንፈሳዊ ኮሌጅ እንዲሁም ከፍተኛ መንፈሳዊ ት/ቤት በሰው ኃይል ፣በበጀትና በአቅማቸው /በውስጣዊ ድርጅታቸው/ በበለጠ እየተጠናከሩ፤ በቁጥራቸውም እየተስፋፉ ተልዕኮአቸውን ብሚገባ እንዲወጡ ቢደረግ፤
- በልዩ ልዩ የሞያ ዘርፍ በተበታተነ ሁኔታ ያሉትን ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን እና በበቂ ሥነ ዘዴ የሠለጠኑ የዘመናዊ ትምህርት ምሁራንን በማቀራረብና በማወያየት በተቀናጀ መልኩ ልምዳቸውን የሚለዋወጡበት በሥርዓተ ትምህርት ዝግጅትና ክለሳ ወቅታዊ ሁኔታና ቀጣይነት /የስብከት ዘዴ፣የጽሕፈት ድርሰት ዘዴ/ ላይ የሚወያዩበት መድረክ /ተቋም/ ቢፈጠር ጥንታዊ ሥርዓተ ትምህርታችን በአቋሙ ዘመናዊነትን በመሠረታዊ ጠባዩ ትውፊታነቱን ሊጠብቅና ሊጎናፀፍ ይችላል:: ትውልዱም ከአባቶች እቅፍ ወጥቶ በዘመኑ ፍልስፍናና ጥበብ /ተጥባበ ሥጋ/ ብቻ ተውጦ ከትምህርቱ አበው ከሥነ ምግባርና ከመንፈሳዊ በረከት ውጭ እንዳይሆን ይረዳል::

| ተ.ቁ | ቤት /ፋካልቲ | ክፍለ ቤት /ዲፓርትመንት/ | የትምህርቱ አማካይ የጊዜ መጠን /በዓመት/ | | የመምህሩ /የምስክሩ/ የማዕረግ ስም | የታወቀ የምስክር /አብነት/ ት/ቤቶች | ማስታወሻ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | መማሪያ | ማደላደያ | | | |
| 1. | ንባብ ቤት | • መቁጠር<br>• ማንዛ<br>• የቁጥር ትምህርት<br>• ፊደል ሐዋርያ<br>• ገበታ ሐዋርያ<br>• የጽሕፈት ትምህርት<br>• መሠረተ ትምህርት<br>• ሃይማኖት<br>• የቃል ጸሎት ትምህርት | 3 | | መጋቤ ሐጸናት ወይም መጋቤ ላዕካን | | |
| 2 | ዜማ ቤት | • የዜማ ቃል ት/ት ከውዳሴ ማርያም ዜማ እስከ ምዕራፍ<br>• ምዕራፍ<br>• ጾመድጓ<br>• ዝማሬ መዋሥእት<br>• አቋቋም<br>• ድጓ<br>• ቅዳሴ | 2<br>3<br>1<br>2<br>4<br>3<br>3 | 1<br>4<br>1 | መጋቤ ስብሐት<br>መጋቤ መዝሙር ሐዋዝ ወይም መጋቤ ሐዋዝ ስብሐት<br>መሪጌታ/መራሒ መጋቤ ኅሩያን | ዙር አባ አረጋዊ ሳንካ ጊዮርጊስ ጎንደር /የላይ ቤትና የታች ቤት/ ደ/ታቦር ኢየሱስ | «ሊቀ ምሁራን» የቤተልሔሙ የድጓ ምስክር የክብር ስም ነው::<br>በደቡብ ጎንደር በምዕራብ ጐጃም<br>በደቡብ ጎንደር |
| 3 | ቅኔ ቤት | • የግሥና ነባር ጥናት<br>• የቅኔ ዓይነት<br>• የቅኔ ቤቶች<br>• የቅኔ መንገድ<br>• የቅኔ አገባብ | 4 | 1 | መጋቤ ምሥጢር | ዋድላ ጎንጅ ዋሸራ | ከተጠቀሱት የምስክር ት/ቤቶች በመምህርነት ተመርቀው በተለያዩ ቦታዎች ምክርነት የሚሰጡ ሊቃውንት አሉ |
| 4 | መጽሐፍ ቤት | መጻሕፍተ<br>• ብሉያት<br>• ሐዲሳት<br>• ሊቃውንት<br>• መነኮሳት | 6<br>5<br>6<br>2 | 1<br>1<br>1<br>1 | መጋቤ ብሉይ<br>መጋቤ ሐዲስ<br>መጋቤ ማእምራን<br>መጋቤ ምክር | ዲማ ጊዮርጊስ ሞጣ ጊዮርጊስ ደብረ ሊባኖስ ቦሩ ሥላሴ ጎንደርመድኃኒዓለም በዓታ ለማርያም ገዳም | የሰዋስወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ ከፍተኛ መንፈሳዊ ት/ቤት |

**ማስገንዘቢያ:-** ይህ የጥንታዊ ሥርዓተ ትምህርት ጥቅል ይዘትና ቅደም ተከተል ዝርዝር መሠረት ያደረገው የጠቅላይ ቤተ ክህነት የትምህርትና ማሠልጠኛ መመሪያ ለመንፈሳዊ ት/ቤቶች በ1990 ዓ.ም. ያወጣውን ሥርዓተ ትምህርትና የበርካታ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያንን የቃል አስረጂዎችን ነው::

- የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የማንነቷ መገለጫ የሆኑ ኪነ ጥበባትና ሥነ ጥበባት ማዕከልም እንደሆነች ይታወቃል:: በመሆኑም ብራና ዳምጣ፣ ቀለም በጥብጣ፣ ብርዕ ቀርጻ የፊደልን ጠባይ የሥርዓተ ነጥብን አገባብ የሥነ ጽሑፍን ስልት ጠብቃና ጠንቅቃ በመጻፍ ለክርስትናው ዓለም ያበረከተችው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው:: በመጻሕፍት ገበታና በመጻሕፍት ማኅደር ላይ ከጥራዝ ሥራ በኋላ የሚደረገው ጌጣጌጥ፣ የሚሳበው ሐረግ፣ የድጉሰት ሥራና መሣሪያዎች፣ በመጻሕፍት የውስጥ ገጾች በሕንጻ ቤተ ክርስቲያን የውስጥ ክፍሎችና በምእመናን ቤተ ጸሎቶች የሚሣሉት የቅዱሳን ሥዕላት ረቂቅ ጥበቦችና የሥዕል መሣሪያዎች፣ በልዩ ልዩ የመስቀል ቅርጽ አወጣጦች ሞያ ከፍ ያለ ግምት የሚሰጣቸው ናቸው:: ለምሳሌ ትምህርተ ሃይማኖትን፣ሥርዓተ እምነትንና ትውፊትን ዐውቆና ጠንቅቆ የሚሥል ሠዓሊ በሊቅነት ደረጃ ስለሚቆጠር ሁልጊዜ የሚጠራበት የማዕረግ ስም አለቃ የሚል ነው:: በሥራው ወቅት ከሚደረግለት ልዩ ልዩ መንግሥታዊና ሕዝባዊ ድጋፍ በተጨማሪ የገንዘብ ስጦታ የቀሚስና የድርብ ሸልማትና የመልከኞች ሹመት ያገኝ ነበር::
- ዛሬ እኒህ ሞያዎች እንዳይረሱ ሊቃውንቱን በማሰባሰብና በማበረታታት ቤተክርስቲያን የምታደርገውን ጥረት ማገዝ አገሩን ሃይማኖቱንና ቅርሱን ከሚወድ ዜጋ /ምእመን/ የሚጠበቅ ታሪካዊ ግዴታ ነው::

## ዋቤ መጻሕፍት


- ሀብተ ማርያም ወርቅነህ /ሊቀሥልጣናት/ ፣ጥንታዊ የኢትዮጵያ ሥርዓተ ትምህርት፣ አ.አ፣1962 ዓ.ም
- ዕንባቆም ቃለ ወልድ /ርእሰ ማእምራን/፣ 1966 ዓ.ም.፣ ስለ ቅኔ ትምህርትና ስለ ጥቅሙ፣ pp.117-132. Proceedings of the Third International Conference of Ethiopian Studies. A.A.
- ክፍያለው መራሒ /ቀሲስ/ የቤተ ክርስቲያን አስተዋጽኦ ለኢትዮጵያ ሥልጣኔ፣አ.አ፣ 1986 ዓ.ም.
- ኪዳነ ማርያም ጌታሁን /መምህር/፣ ጥንታዊው የቀለም ተማሪ፣ አ.አ.፣ 1980 ዓ.ም.
- ዘመድኩን በቀለ፣ ቅዱሳን መካናት በኢትዮጵያ፣ /ክፍል1/ ፣አ.አ፣1992 ዓ.ም.
- ማኅበረ ቅዱሳን፣ቤተክርስቲያንህን ዕወቅ፣ አ.አ፣1988 ዓ.ም.
- አክሊለ ብርሃን ወልደ ቂርቆስ /ሊቀ ጠበብት/፣ መርሐ ልቡና፣አ.አ.፣ 1945 ዓ.ም
- ትንሣኤ መጽሔት፣ቁ.62፣1975 ዓ.ም.
- መለከት መጽሔት፣1ኛ ዓመት ቁ.2፣ 1985 ዓ.ም.
- ሐመር መጽሔት፣5ኛ ዓመት ቁ.5፣ 1990 ዓ.ም.
- ሐመር መጽሔት ፣5ኛ ዓመት ቁ.3 1990 ዓ.ም.
- ስምዐ ጽድቅ፣3ኛ ዓመትቁ.2፣1988 ዓ.ም.

**ይህ መጠይቅ የሐመር መጽሔትና የስምዐ ጽድቅ ጋዜጣን አጠቃላይ ተነባቢነት ለመገምገም የቀረበ ነው**

ሀ. ጥያቄዎቹን ሲመልሱ ያስምንም ፍርሃትና ይሉኝታ ይሁን

ለ. መልስዎን በተሰጠዎት ቦታ ብቻ ያስቀምጡ:: በመልስዎ አንጻር ባለው ሳጥን የ «X » ምልክት ያስቀምጡ

ሐ. በሁለቱም ገጽ የቀረቡትን ጥያቄዎች ከሞሉ በኋላ ወረቀቱን ቆደው በአካል ወይም በፖስታ ሳጥን ቁጥራችን /80078/ ይላኩልን

1 **ሐመር መጽሔትን የሚያነቡት**

- ☐ ተውሼ ነው
- ☐ ገዝቼ ነው
- ☐ ሲያጋጥመኝ ብቻ ነው

2. **እርስዎ በሚኖሩበት አካባቢ የሐመር መጽሔት**

- ☐ በወቅቱ ይደርሳል
- ☐ በመጠኑ ይዘገያል
- ☐ በጣም ይዘገያል
- ☐ ጭራሽ አይደርስም

3. **መጽሔቱን የማግኘት ችግር ላለባቸው ምእመናን ለማዳረስ የሚያደርጉት ጥረት**

- ☐ አለ
- ☐ የለም

4. **ካለ እንዴት?**

1. ____________________
2. ____________________
3. ____________________

5 **ከመጽሔቱ ዓምዶች የሚወዷቸውንና ወደፊትም ሊቀጥሉ ይገባቸዋል የሚሏቸውን በምርጫዎ ቅደም ተከተል ቢዘረዝሩልን?**

1. ____________________
2. ____________________
3. ____________________
4. ____________________

6. **ከመጽሔቱ ዓምዶች የማያስፈልጉ የሚመስሉዎትን እና ቢቀሩ የሚሏቸውን በቅደም ተከተል ቢዘረዝሩልን?**

1 ____________________

2 ____________________

3 ____________________

7. **መጽሔቱ ሊያካትታቸው ይገባል የሚሏቸው አዳዲስ ዓምዶች ካሉ ቢያስፍሩልን?**

1. ____________________
2. ____________________
3. ____________________
4. ____________________

8 **የመጽሔቱ አጠቃላይ ይዘት**

- ☐ የሚገባውን ያህል መንፈሳዊ ነው
- ☐ መንፈሳዊነቱ መካከለኛ ነው
- ☐ መንፈሳዊ ይዘቱ ደካማ ነው
- ☐ ሌላ

9 **የመጽሔቱ የቋንቋ አጠቃቀም**

- ☐ በጣም ከባድና ለጥቂት አንባብያን ብቻ የሚገባ ነው
- ☐ መካከለኛ በመሆኑ ለአብዛኛው አንባብያን ግልጽ ነው
- ☐ መንፈሳዊ /ኦርቶዶክሳዊ/ ላህይ የለውም
- ☐ ሌላ

10 **በመጽሔቱ ለንባብ የሚቀርቡ ጽሑፎች አቀማመጥ /format/**

- ☐ ጥሩና ተነባቢ ነው
- ☐ መካከለኛ ነው
- ☐ ዐይን የማይስብና ሲነበብም አሰልቺ ነው

11 ጥሩና ተነባቢ ካልሆነ እንዴት ቢስተካከል ይመክሩናል?

1. ____________________
2. ____________________
3. ____________________

13 **አጠቃላይ የመጽሔቱን ይዘትና ዝግጅት በሚመለከት ያለዎትን አስተያየት ቢገልጹልን?**

____________________

____________________

____________________

***እግዚአብሔር ይስጥልን***

1 ስምዐ ጽድቅ ጋዜጣን የሚያነቡት
- ☐ ተውሺ ነው
- ☐ ገዝቼ ነው
- ☐ ሲያጋጥመኝ ብቻ ነው

2. እርስዎ በሚኖሩበት አካባቢ የስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ
- ☐ በወቅቱ ይደርሳል
- ☐ በመጠኑ ይዘገያል
- ☐ በጣም ይዘገያል
- ☐ ጭራሽ አይደርስም

3. የስምዐ ጽድቅ ጋዜጣን የማግኘት ችግር ሳለባቸው ምእመናን ለማዳረስ የሚያደርጉት ጥረት
- ☐ አለ
- ☐ የለም

4. ካለ እንዴት?

1.____________________

2.____________________

3.____________________

5. ከጋዜጣው ዓምዶች የሚወዷቸውንና ወደፊትም ሊቀጥሉ ይገባቸዋል የሚሏቸውን በምርጫዎ ቅደም ተከተል ቢዘረዝሩልን?

1.____________________

2.____________________

3.____________________

4.____________________

6. ከጋዜጣው ዓምዶች የማያስፈልጉ የሚመስሉዎትን እና ቢቀሩ የሚሏቸውን በቅደም ተከተል ቢዘረዝሩልን?

1 ____________________

2 ____________________

3 ____________________

7. ጋዜጣው ሊያካትታቸው ይገባል የሚሏቸው አዳዲስ ዓምዶች ካሉ ቢያስፍሩልን?

1.____________________

2.____________________

3.____________________

4.____________________

8 የጋዜጣው አጠቃላይ ይዘት
- ☐ የሚገባውን ያህል መንፈሳዊ ነው
- ☐ መንፈሳዊነቱ መካከለኛ ነው
- ☐ መንፈሳዊ ይዘቱ ደካማ ነው
- ☐ ሌላ

9 የጋዜጣው የቋንቋ አጠቃቀም
- ☐ በጣም ከባድና ለጥቂት አንባብያን ብቻ የሚገባ ነው
- ☐ መካከለኛ በመሆኑ ለአብዛኛው አንባብያን ግልጽ ነው
- ☐ መንፈሳዊ /አርቶዶክሳዊ/ ላህይ የለውም
- ☐ ሌላ

10 በጋዜጣው ለንባብ የሚቀርቡ ጽሑፎች አቀማመጥ /format/
- ☐ ጥሩና ተነባቢ ነው
- ☐ መካከለኛ ነው
- ☐ ዐይን የማይስብና ሲነበብም አሰልቺ ነው

11 ጥሩና ተነባቢ ካልሆነ እንዴት ቢስተካከል ይመክሩናል?

1.____________________

2.____________________

3.____________________

13 አጠቃላይ የጋዜጣውን ይዘትና ዝግጅት በሚመለከት ያለዎትን አስተያየት ቢገልጹልን?

____________________

____________________

____________________

____________________

____________________

*እግዚአብሔር ይስጥልን*

# ግማደ መስቀሉ ከሄኖም እስከ ግሸን ማርያም

*አባ ገብረ መስቀል ተስፋዬ ዘገነተ ማርያም*

የ«ተ» ፊደል ቅርጽ ባለው መስቀል ዓለምንና በውስጡ የሚገኘውን ሁሉ ፈጥሮ የሚገዛውን አምላክ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ቤተ እሥራኤል በቀራንዮ ላይ በሰቀሉት ጊዜ ከመከራው ጽናት የተነሣ ደሙ ወርዶ የተሰቀለበትን መስቀል አለበሰው። ከዚያም የማይሞተው አምላክ ሞተ በኋላም ከመስቀሉ አውርደው ቀበሩት። በ3ኛውም ቀን ተነሣ። ተሰቅሎበት የነበረው የእንጨት መስቀል ሌት ተቀን በሙሉ ሳያቋርጥ እንደፀሐይ ሲያበራ፣ በተጨማሪም አጋንንት ሲያባርር፣ ድውይ ሲፈውስ፣ ሙታንንም ሲያስነሳ ቤተ እሥራኤል አይሁድ ቀንተው በዓዋጅ ትልቅ ጉድጓድ ቆፍረው በመቅበር የቤት ጥራጊና አመድ ጠቅላላ የቆሻሻ መከማቻ እንዲሆን ወሰኑ፡ ከዚያ ዘመን ጀምሮ እስከ ሦስት መቶ ዘመን ድረስ የተከማቸው ቆሻሻ እንደተራራ ሆነ።

ከዚያ በኋላ የታላቁ ቆስጠንጢኖስ እናት እሌኒ ንግሥት የተባለች ደግ ሴት የክርስቶስን መስቀል በ3 መቶ ዓ.ም መስከረም 17 ቀን በዕጣን ጢስ ምልክት ቁፋሮ አስጀምራ መጋቢት 10 ቀን አግኝታ በማውጣት ታላቅ ቤተ መቅደስ ጐልጎታ ላይ ሠርታ በክብር አስቀመጠችው። ይህ መስቀልም ከዚያ ዕለት ጀምሮ እንደፀሐይ እያበራ ድውይ እየፈወሰ አጋንንት እያባረረ ልዩ ልዩ ተአምራትን እየሠራ ሙት እያስነሳ ዕውር እያበራ ተአምራቱን ቀጠለ።

ይህንን ታላቅ ዝና የሰማው የፋርስ ንጉሥ መስቀሉን ማርኮ ፋርስ ወስዶ አስቀመጠው። በዚህ ጊዜ የኢየሩሳሌም ምዕመናን የሮማውን ንጉሥ ሕርቃልን ዕርዳታ በመጠየቅ እንዲመለስ አድርገው በኢየሩሳሌም ብዙ ዘመን ሲኖር እንደገና ኃያላን ነገሥታት ይህን መስቀል እኔ እወስድ እኔ እወስድ እያሉ ጦርነት ፈጠሩ።

በዚህ ጊዜ የኢየሩሳሌም፣ የቁስጥንጥንያ፣ የአንጾኪያ፣ የኤፌሶን፣ የአርማንያ፣ የግሪክ፣ የእስክንድርያ የመሳሰሉት የሃይማኖት መሪዎች በመካከል ገብተው ጠቡን አበረዱት። ከዚህም አያይዘው በኢየሩሳሌም የሚገኘውን የክርስቶስን መስቀል ከአራት ከፍለው በዕጣ አድርገው በስምምነት ተካፍለው ከሌሎቹ ታሪካዊ ንዋያት ጋር በየሀገራቸው ወስደው በክብር አስቀመጡት። የቀኝ ክንፉ የደረሰው ለአፍሪቃ ስለነበር ከታሪካዊ ንዋየ ቅድሳት ጋር በግብጽ የሚገኘው የእስክንድርያ ፖትርያርክ ተረክቦ ወስዶ በክብር አስቀመጠው።

ይህ ግማደ መስቀልም ለብዙ ዘመን በእስክንድርያ ሲኖር በግብጽ እስላሞች እየበዙ ኃይላቸው እየጠነከረ ሔደ። በእስክንድርያ የሚኖሩትን ክርስቲያኖች «ለግማደ መስቀሉ አትስገዱ፡ የክርስቲያንን ሃይማኖት አጥፉ» እያሉም ሥቃይ ያጸኑባቸው ጀመር። ክርስቲያኖቹም አንድ ሆነው መክረው ለኢትዮጵያዊው ለዳግማዊ ዓፄ ዳዊት እንዲህ የሚል መልእክት ላኩ «ንጉሥ ሆይ! በዚህ በግብፅ ያሉ እስላሞች ለክርስቶስ መስቀል አትስገዱ የክርስቲያንንም ሃይማኖት አጥፉ እያሉ መከራ ስለአፀኑብን 10 ሺህ ወቄት ወርቅ እንሰጥሃለንና ኃይልህን አሳሥተህ አስታግሥልን» ብለው ጠየቁት። በዚህ ጊዜ ዳግማዊ ዓፄ ዳዊት ለመንፈሳዊ ኃይማኖት ቀንተው የክርስቶስ ፍቅር አስገድዶአቸው 20 ሺህ ሠራዊት አስከትለው ወደ ግብፅ ዘመቱ። የዐባይን ውሃም ለመገደብ ይዘጋጁ ጀመር። በዚህ ጊዜ በግብፅ ያሉ ፈሩ። ተሸበሩ። ንጉሡ ዳግማዊ ዳዊትም እንዲህ የሚል መልዕክት ለእስላሞች ላኩ «በተፈጥሮ ወንድሞቻችሁ ከሆኑት ክርስቲያኖች ጋር ካልታረቃችሁ ሀገራችሁን መጥቼ አጠፋዋለሁ» የንጉሡ መልዕክትም ለእስላሞች እንደደረሳቸው ፈርተው እንደጥንቱ በየሃይማኖታቸው ጸንተው በሰላም እንዲኖሩ ከክርስቲያን ወንድሞቻቸው ጋር ታረቁ። ይህንንም ዳግማዊ ዳዊት ሰሙ። በዚህም ጉዳይ ንጉሡ በጣም ደስ አላቸው። እግዚአብሔርንም አመሰገኑ። ከግብጽ የሚኖሩ ክርስቲያኖችም ከ12 ሺህ ወቄት ወርቅ ጋር ደስታቸውን በኢትዮጵያዊው ንጉሥ ለዳግማዊ ዳዊት በደብዳቤ አድርገው ላኩላቸው። ንጉሡም የደስታውን ደብዳቤ ተመልክተው ደስ አላቸው ወርቁን ግን መልሰው በመላክ እንዲህ የሚል ደብዳቤ ጻፉ በግብጽ የምትኖሩ የክርስቶስ ተከታዮች ሆይ እንኳን ደስ አላችሁ። የላካችሁልኝን 12 ሺህ ወቄት ወርቅ መልሼ ልኬላችኋለሁ። የእኔ ዓላማ ወርቅ ፍለጋ አይደለም። የክርስቶስ ፍቅር አስገድዶኝ በተቻለኝ ችግራችሁን ሁሉ አስወገድኩላችሁ እንጂ። አሁንም የምለምናችሁ በሀገሬ ኢትዮጵያ ረሀብና ቸነፈር ድርቅ ስለወረደብኝ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተሰቅሎበት የነበረውን መስቀልና የቅዱሳንን አጽም ከሌሎች ክቡራን ዕቃዎች ጋር እንድትልኩልኝ ነው» የሚል ነበር።

በእስክንድርያ ያሉ ምእመናን ይህ መልእክት እንደደረሳቸው ከሊቃነ ጳጳሳቱና ከኤጲስ ቆጶሳቱ ጋር ውይይት በማድረግ «ይህ ንጉሥ ታላቅ ክርስቲያን ነው። ስለዚህ ልቡን ደስ እንዲለው የፈለገውን የጌታችንን ግማደ መስቀል ከቅዱሳን አጽምና ንዋየ ቅዱሳት ጋር አሁን በመለሰው 12 ወቄት ወርቅ የብር የንሐስ፡ የመዳብና የወርቅ ሣጥን አዘጋጅተን እንላክለት» ብለው ተስማሙ። በክብር በሥነ ሥርዓት በሠረገላና በግመል አስጭነውም ስናር ድረስ አምጥተው አስረከቧቸው። ያንጊዜ ንጉሡና ሕዝባቸው በእጃቸው እያጨበጨቡ በእግራቸው እያሸበሸቡ በግንባራቸው እየሰገዱ በክብር በደስታ ተቀበሉት ይህም የሆነው መስከረም 21 ቀን ነው። በኢትዮጵያም ታላቅ ብርሃን ሌት ተቀን 3 ቀን ሙሉ ሲበራ ሰነበተ። ይህንም ወሬ የግብጹ ንጉሥ ሰምቶ በመቆጣት የእስክንድርያውን ሊቀ ጳጳሳት አባ ሚካኤልን አሠራቸው። ኢትዮጵያው ንጉሥ ዳግማዊ ዓጼ ዳዊትም የሊቀ ጳጳሱን መታሠር ሰምተው አዘኑ። ለግብፁ ንጉሥ ሊቀ ጳጳሱን አባ ሚካኤልን እንዲፈቷቸው መልእክት ላኩ። ንጉሡም መልእክቱን ተቀብሎ እምቢ አልፈታም የሚል መልእክት መለሰ። ጸፌ ዳግማዊ አጼ ዳዊትም የግብፁን ንጉሥ እንቢታ ተመልክተው የዐባይ ውሃ ወደ ግብጽ እንዳይወርድ መገደብ ጀመሩ። የግብፁ ንጉሥም ይህን ጉዳይ ሰምቶ ፈራ፡ ተሸበረ። ጉዳዩ የሊቀ ጳጳሳቱ መታሠር መሆኑን አውቆ ከእሥራቸው ፈታቸው። ንጉሡ ዳግማዊ አጼ ዳዊትም ጠላታቸውን ድል ስለአደረጉ ደስ አላቸው። በዚህ መካከልም ግማደ መስቀሉ ወደ መካከለኛው ኢትዮጵያ ሳይደርስ ዓፄ ዳዊት ስናር ላይ በድንገት አረፉ። ግማደ መስቀሉም የግድ በዚያው በስናር ቆየ። ከዚህ በኋላ የሚቼ የዳግማዊ ዳዊት ልጅ ዘርአያዕቆብ እንደነገሡ ወደ ሥናር ሔደው ግማደ መስቀሉን ከሌሎቹ ንዋያተ ቅዱሳት ጋር አምጥተው በመናገሻ ከተማቸው በደብረ ብርሃን ላይ ቤተመቅደስ ሠርተው ለማስቀመጥ ሲደክሙ በሕልማቸው «አንብር መስቀልየ በዲበ መስቀል፡ መስቀሌን በመስቀለኛ ቦታ ላይ» አስቀምጥ የሚል ሕልም አዩ። ንጉሡም በኢትዮጵያ አውራጃዎች ሁሉ መስቀለኛ ቦታ በመፈለግ ከብዙ ቦታ ላይ አስቀምጠውት ነበር። ለምሳሌ በሸዋ በመናገሻ ማርያም በወጨጫ በሜጫ መስቀሉን አሳርፈውት ነበር። ነገር ግን የመጨረሻውን ቦታ ያላገኙት በመሆኑ በራዕይ እየደጋገመ «መስቀሌን በመስቀለኛ ቦታ ላይ አስቀምጥ» እያለ ይነግራቸው ነበር። በመጨረሻም ዓፄ ዘርአያዕቆብም ለ7 ቀናት ያህል ሱባዔ ገቡ በዚያም እግዚአብሔር ተገልጦላቸው መስቀለኛውኑ ቦታ የሚመራህ ዓምደ ብርሃን ይመጣል አላቸው «እርሳቸውም ከዚያ እንደወጡ መስቀለኛውን ቦታ የሚመራ ዓምደ ብርሃን ከፊታቸው መጥቶ ቆመ። በዚያ መሪነት ወሎ አንባሰል አውራጃ ውስጥ ግሸን ከምትባል ቦታ መርቶ አደረሳቸው። በርግጥም ግሸን የተባለች አንባ ጥበበኛ ሰው እንደቀረጻት የተዋበች መስቀለኛ ቦታ ሁና ስለአገኟት የልባቸው ደረሰ። ደስም አላቸው በዚችም አንባ ታላቅ ቤተ መቅደስ ሠርተው መስቀሉንና ሌሎች ንዋየ ቅዱሳቱን በየማዕረጋቸው የክብር ቦታ መድበው አስቀመጧቸው ዘመኑም በ14ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ነው።

ከእስክንድርያ ሀገር ከመስቀሉ ጋር በልዩ ልዩ ሣጥን ተቆልፈው የመጡትም ዝርዝር ስማቸው የሚከተለው ነው። ጌታ በዕለተ ዓርብ ለብሶት የነበረው ቀይ ልብስ ከሮም የመጣ ከለሜዳ፡ ከአፍርጊ ሀገር የመጣው ሐሞት የጠጣበት ሰፍነግ ዮሐንስ የሣለው የኩርዓተ ርእሱ ሥዕል፡ ሉቃስ የሣላቸው የእመቤታችን ሥዕሎች አስርቱ ቃላት የተጻፈበት የእመቤታችን ጽላት (ታቦት)፡ የሐና አጽምና የራስ ጠጉር፡ የአርሴማ ቅድስት አጽም፡ የያዕቆብ እሁሁ አጽም፡ የበርተሎሜዎስ ሐዋርያ አጽም፡ የቶማስ ሐዋርያ አጽም፡ የቅዱስ ጊዮርጊስ ሰማዕት አጽም፡ የቅዱስ መርቆሬዎስ አጽም፡ የቅዱስ ገላውዴዎስ አጽም፡ ሄሮድስ ያስፈጃቸው የቤተልሔም ሕፃናት አጽም፡ የቅዱስ ዲዮስቆሮስ ሊቀ ጳጳሳት አጽም፡ በኢየሩሳሌም ግብፅ ውስጥ ከልዩ ልዩ ቅዱሳት መካናት የተቆነጠረ የመሬት አፈር፡ የዮርዳኖስ ውኃ ናቸው። የነዚህንም ዝርዝር ለኢትዮጵያ ሕዝብና ግሼን ካህናት በጽሑፍ መስከረም 21 ቀን ላይ ተናገሩ። በመጀመሪያም ይህ ግማደ መስቀል ከእስክንድርያ ስናር የገባው መስከረም 21 ቀን ነው። ወደ ኢትዮጵያም የገባው በመስከረም 21 ቀን ነው። አሁንም በመጨረሻ ግሸን አንባ የገባው መስከረም 21 ቀን ሲሆን ቤተመቅደስ ተሠርቶ ቅዳሴ ቤቱ የተከበረውና አፄ ዘርዐ ያዕቆብ ለመላው ኢትዮጵያ የመጡትን ዕቃዎች በጽሑፍ በመዘርዘር የገለጹበትም መስከረም 21 ቀን ነው። ስለዚህ በዚህች በግሸን ደብር የክርስትና እምነት ያላቸው የኢትዮጵያ ምእመናን ከመስቀሉና ከቅዱሳን አጽም በረከት ለማግኘት በየዓመቱ መስከረም 21 ቀን ቦታው ላይ በመገኘት ያከብራሉ። በዚያም ዘመን የነበሩት የኢትዮጵያ ጳጳሳት አባ ሚካኤልና አባ ገብርኤል የተባሉ ከንጉሡ ከዓፄ ዘርአያዕቆብ ጋር ሁነው የምህረት ቃል ኪዳን ለመቀበል በዚህች በግሸን ደብር ሱባዔ ገቡ። በሱባዔአቸውም መጨረሻ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተገልጾ ይህች ቦታ እኔ ተወልጄ ያደኩባትን ኢየሩሳሌምን ትሁን፡ የተቀበርኩባትንም ጐልጐታን ትሁን፡ በዚች ቦታ እየመጣ የሚማፀነውን ሁሉ ቸርነቴ ትጐበኘዋለች፡ ጠለ ምህረቴንም አለይባትም፡ ከሩቅም ሆነ ከቅርብ መጥቶ የተቀበረ ኢየሩሳሌም እንደተቀበረ ይሁን» የሚል የምህረት ቃል ኪዳን ሰጣቸው። ይኸንንም በዚያ ለተገኙት ምዕመናን ሁሉ በጽሑፍ ካስሙ በኋላ ጠቅላላ የግማደ መስቀሉንና የሌሎቹን ታሪካውያን ንዋያተ ቅዱሳትንም ዝርዝር ታሪክ የያዘውን መጽሐፍ መጽሐፈ ጤፉት ብለው ሰይመው ድንጋጌውን ሁሉ በመዘርዘር ለግሸን እግዚአብሔር አብ ሰጡ። አፄ ዘርአያዕቆብም በዚህ ብቻ ሳይወሰኑ እሌኒ የተሰኘችው እህታቸው በእመቤታችን ማርያም ስም ቤተመቅደስ እንድትሠራ አዘው የእመቤታችን ማርያም ቤተክርስቲያን ከእግዚአብሔር አብ ቤተክርስቲያን አጠገብ ታንጾ ጥር 21 ቀን ቅዳሴ ቤቱ ተከበረ። ዓፄ ዘርአያዕቆብም ይህችን ደብር ደብረ ከርቤ ብለው በመሰየም እንኳንስ ሰው የሠረገ ቆቅ የበረረ ወፍ እንዳይገደል ዳሯ እሳት መሀሏ ገነት ትሁን ብለው በጤፉት መጽሐፍ ውስጥ አጽፈዋል። በዚህ ምክንያት በየጊዜው የነገሡ የኢትዮጵያ ነገሥታትና የተሾሙ ጳጳሳት መሳፍንትና መኳንንት ልዩ ልዩ ንዋያተ ቅዱሳትና መጻሕፍትን የወርቅና የብር ጻሕል ጽዋ መስቀል የመሳሰሉትን እየሰጧት ዛሬ ይህች ታላቅ ደብር የቱሪዝም መደብር ሁና ትገኛለች። የመኪና መንገድም በደሴ በኩል ተነሥቶ ግሸን ከአንባው ሥር ድረስ ይገባል። ምዕመናንም በየዓመቱ መስከረም 21 ቀን በግሸን ማርያም በመገኘት ከዓመት ወደ ዓመት እየበረከቱ ሔደዋል። በ1950 ዓመተ ምህረት ላይ የጐንደር ሊቀ ጳጳስ የነበሩት ብፁዕ አቡነ ሚካኤል በግሸን አንባ ላይ የዮርዳኖስ ጸበል በብዛት አስመጥተው በእግዚአብሔር አብ ቤተክርስቲያን አጠገብ በሚገኘው የድንጋይ ገንዳ ጉድጓድ አስሞልተውታል የውሃ ምንጭም በመጠኑ በግቢው ይገኛል፡ ደብሩ የሴትና የወንድ ተብሎ ተለይቶ ተወስኗል። ለምሳሌ እግዚአብሔር አብ ቤተክርስቲያን የሚገቡት ወንዶች ብቻ ናቸው።

ይህች ደብር ዛሬ የምትተዳደረው በምዕመናን ድጋፍና አስተዋጽኦ ነው ስለዚህ የኢትዮጵያ ምዕመናን የሆናችሁ ሁሉ ከበረከተ መስቀሉ ለመሳተፍ ወደ ግሸን ገሥግሱ። ሰላመ እግዚአብሔር አይለየን፨



# የአድኑኝ ጥሪ

ከ600 ዓመታት በላይ ሕልውናው ተጠብቆና ታሪክን አቅፎ ያቆየው ገዳም የሚደረግለት እንክብካቤ በቂ ስላልነበረ እየፈራረሰ ነው። በ1993 ዓ.ም የደረሰበት አደጋ ካሁን በፊት ከነበሩት ሁሉ የከፋ ነው። ቅኔ ማኅሌቱንና ቅድስቱን ያቀፈው ሕንፃ በአንድ በኩል ሙሉ በሙሉ ሲፈራርስ ሌላው አካሉም ብዙ እንደማይቆይ ተገምቷል።

የክልሉ መንግሥት ቴክኒካዊ ድጋፍ ከማድረግ ውጭ ጥገና ለማካሄድ አቅሙ አይፈቅድለትም። እንደ ጉንዳጉንዶ ዓይነት ሕዝባዊ ሀብቶች መጠበቅ ያለባቸው ደግሞ በእምነቱ ተከታይ ሕዝብና በተቆርቋሪ ዜጎች ነው። በቅርቡ ሁኔታውን ለማጥናት ወደ ስፍራው የተላከው ባለሙያ ቤተክርስቲያኑ ሙሉ በሙሉ ከመፈራረሱ በፊት ሊደረግለት ስለሚገባው ሥራ ዝርዝር መግለጫ አቅርቧል። ለዚህ የተገመተው የገንዘብ መጠን ወደ ግማሽ ሚሊዮን ብር የሚጠጋ ነው።

ስለዚህ ቅርስን ከጥፋት ለማዳን በቡድን ተደራጅተው ሆነ በግል የሚንቀሳቀሱ ኢትዮጵያውያን ይህን ገዳም ከጥፋት ለማዳን አፋጣኝ እርምጃ እንዲወስዱ ጥሪያችንን እናቀርባለን። የቅርቡ ባለሀብት የሆነው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ባለሥልጣናትም ትኩረት እንዲቸሩት ልናሳስብ እንወዳለን።

ለበለጠ መረጃ በስልክ ቁጥር 04/40 10 32 /መቀሌ/ ቢደውሉልን
በፋክስ ቁጥር 04/041032 ቢልኩልን እናስተናግድዎታለን።
የትግራይ ባሕል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ
(ክብ ማኅተም አለው)

ዋጋ ብር 3.00

ሜጋ ማተሚያ ኢንተርፕራይዝ

©ማኅበረ ቅዱሳን

ይህን መጽሔት ያለ ማኅበረ ቅዱሳን ፈቃድ በከፊልም ሆነ በሙሉ ማሳተም ፣እንዲሁም በማንኛውም መልኩ ለሽያጭ ማዋል በህግ የተከለከለ ነው፡፡